
# አንደኛው አስደናቂ ታሪኮች


NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች፤

እንዴት ከረማችሁ?

ደኅና መሆናችን ደኅና ነገር ነው።

ይሄን አንደኛውን የአስደናቂ ታሪኮች መጽሐፍቶቼን የመጀመሪያውን አስደናቂ ታሪክ አቀረብኩላችሁ።

እግዚአብሔር ተርፎ ከሚቀር ዕድሜ ካልነፈገን ሁለተኛው የዚህ ተከታይ መጽሐፍ እስትንገናኝ እስከዚያው ደህና ሁኑ።

# ማውጫ


ድንቆቹ....................................................................................4

የሂሳቡ ሊቅ ............................................................................7

የሚያዩት በዓይንዎ ብቻ ነው? ..................................................13

የውሀ ጥንቆላ ..........................................................................15

የራስ ምታት ዓይነቱ 47 ነው። ..................................................43

ትልቅ እንቁላል የሚወልድ አሣነባሪ ብቻ ነው።................................63

የሞተ ሰው እንደገና ይወለዳል?....................................................64

እንቁራሪት የምትሰማው በዓይኗ ነው። ...........................................72

ኤሮፓውያን በአዞ የሚሳብ ጋሪ ለልጆቻቸው ይሠሩ ነበር።..................80

የግብጽ አገር በጎች ጆሮ የአህያ ያህላል። .........................................84

ዘጠኝ..................................................................................101

ከወፍ ዘር ጥሩ ድምፅ ያለው ወንዱ ነው። .....................................106

ከባህር ዛፍ ዘር ረጃጅሞቹ ጃራህና ካሪ የተባሉት ናቸው። ..................107

ስለደራሲው በጥቂቱ......................................................................120

..........................................................................................121

# ድንቆቹ

በቻይና አገር የስምንትና የዘጠኝ ዓመት ልጆች ተጋብተዋል። ልጅ ወልደዋል። ስዕሉ ከትክክለኛ ፎቶ ግራፋቸው ላይ ተቀድቶ የተሳለ ነው።

የእነዚህ ልጆች ወልላጆች በቻይና አገር አሞይ በተባለ አገር ገበሬዎች ነበሩ። እነዚህ ልጆች ልጅ የወለዱት በ1910 ዓ.ም ጥር ስምንት ቀን ነው።

የዚያን ጊዜ የእናትዮዋ ዕድሜ ስምንት ዓመት ሲሆን የአባትዮው እይፂ ዕድሜ ዘጠኝ ዓመት ነበር።

በካሊፎርኒያ የወይዘሮ ማሊክ ድመት አራት ራስ ያላት አንዲት ድመት ወልዳለች አራቱም ለየብቻ ይጠባሉ። ድመቶቹ አንድ ጭራና አራት እግሮች ብቻ አላቸው። ታዲያ በቁጥር አራት ይባላሉ ወይስ አንድ ድመት።

ማርጋሬት ገስት የተባለች ልጅ በአሜሪካ አገር በካንሳስ ውስጥ በቤከር ዩኒቨርሲቲ ሙዚቀኛነት ተምራ ዲግሪዋን አግኝታለች። ዲግሪዋን ባገኘችበት ጊዜ ዕድሜዋ ሦስት ዓመት ብቻ ነበር።

በቴክሳስ ውስጥ ናቫሶታ በሚባል ከተማ የሚኖሩት አቶ ላሲ ደርሲ ፊርማቸው እንደዚህ እንደ ስዕሉ ነበር።

ሙዝሚ በአሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜዋ አያት ለመሆን በቅታለች። ሙዝሚ በአፍሪካ የካላባት የደሴት ባላባት የክሪ ተወዳጅ ሚስት ነበረች በዚያ ደሴት ሙምዚን የሚያህል ቆንጆ እንዳልነበረ ይነገራል። ታድያ በዚሁ በቁንጅናዋ ምክንያት ስምንት ዓመት ሳይሞላት አቶ አሙምዚ በተወለደች በስምንት ዓመት ከአራት ወርዋ ሴት ልጅ ወለደች የተወለደችው ልጅ ደግሞ በተወለደች በስምንት ዓመትዋ እንደ እናትዋ ልጅ ወለደች።

አቶ ሁጎ እና አቶ ሄንስ ጋስጃ ታስረው ከኖሩበት እስር ቤት ኅዳር 24 ቀን 1923 ዓ.ም ተፈቱ የተፈቱ ዕለት ኢሴን ከተባለች የባቡር ጣቢያ መንደር

ውስጥ ትልቅ ደስታ አደረጉና ከመጠጥ ቤት ገቡ። ከዚያም መጠጥ ቤት እየተጋበዙ አሥራ ሰባት ሰዓት ሙሉ ሲጠጡ ቆዩ።

እነኚህ ጀርመኖች የሚጠጡት ቢራ ብቻ ነበር። ከቀኑ አሥር ሰዓት መጠጣት ጀምረው ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ጠግበው ወጡ። በጠቅላላው ሁለቱ ብቻ የጠቱት 352 ጠርሙስ ቢራ ነበር።

ጀርቦአ ትባላለች። ከአይጥ ትንሽ ነው ከፍ የምትለው። ታዲያ በአንድ ጊዜ ከሦስት ሜትር በላይ አግድም መዝለል ትችላለች።

እኚህ ሰውዬ በሕንድ አገር የህኑማን መቅደስ መነኩሴ ናቸው። ድንክዬ ናቸው። ቁመታቸው አንድ ሜትር ወይም ሁለት ክንድ ብቻ ነው። እኚህ መነኩሴ ከቁመታቸው የበለጠ ጠጉር ነበራቸው። የጠጉራቸው ርዝመትም ሦስት ሜትር ወይም ስድስት ክንድ ነበር።

አቶ ፊንስ ጋጅ የተባለ ሰው በ፳፫ ዓመት ዕድሜው ከሩትላንድ እስከ በርሊንግተን ባለው የባቡር ሐዲድ ሥራ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። በ1847 ዓ.ም መስከረም 13 ቀን አንድ ኃይለኛ ዲማሚት ፈነዳና ብዙ ነግሮችን በታተነ። ከተበታተኑት ብረታ ብረቶች መሐል ሁለት ሜትር ተኩል ርዝመትና የውፍረቱ ዙርያ ክብ አንድ ኢንች ከሩብ የሆነ ብረት ከዳነበት ሲመለስ በቀጥታ የጋጅን ጭንቅላት ቀዶ ገባ። ብረቱ እይገባው በግራው በኩል ነው። ዓይኑ ውስጥ አፍሎ በዓይኑ ሥር ጫፉ ወጣ።

በዚያ የነበሩ ሰዎች ከወደቀበት አንስተው አንድ ማይል ርቀት ወዳለው ሆቴል ወሰዱት። ከሆቴሉ እንደ ደረሰ ያለ ምንም ደጋፊ ከሆቴሉ ገብቶ ያን በራሱ እንደ ተሸከመ ከተያዘለት ክፍል ከፎቅ ወጣ።

ከምሽቱ 12 ሰዓት በሆነበት ጊዜ ሐኪም ተጠርቶ ዶክተር ሐርሎው የተባለ ሐኪም ደረሰ። ሐኪሙ ሲደርስ የቁስለኛው አልጋና መሬቱ ሁሉ በደም ተበክሎ ነበር። ብረቱን ለማውጣት ተሞክሮ ነበር ግን የብረቱ አዘላለቅ ረጅም ስለ ነበረ ወደ የትም ለመነተት አልተቻለም። ባጭሩ ተባለና ከላይና ከታች

ተቆረጠ። ብረቱ የሰውየውን ጭንቅላት የቀደደው ቀዳዳ ስፋቱ ሦስት ኢንች ተኩል ዲያሜትር ነበር። ከለሊቱ አራት ሰዓት ሲሆን አቶ ጋጅ የቁስሉን ነገር ረሳና ስለ ሥራውና ስለ ጓደኞቹ ማውራት ጀመረ። ብረቱን ለማውታት ስላልተቻለ ከዚያው ይቅር ተብሎ ቀረ። ጋጅም ብረቱ በፊቱ እና በራሱ ላይ ጫፍና ጫፎቹ እንደ ወጡ ሥራውን ጀመረ።

ጋጅ ይህ አደጋ ከደረሰበት ከሦስት ዓመት በኋላ ፕሮፌሰርን ቢግሎው የተባሉ የሕክምና ሊቅ መረመሩት። ፕሮፌሰሩ በሰጡት ሪፖርት ጋጅ በብረቱ አወጋግ የፈሰሰው ዓይኑ ከመታወሩ ሌላ ሕሊናው ምንም ያልተበላሸና አካሉም ጤነኛ መሆኑን ተናገሩ። በኋላ ለብዙ ጊዜ ቆይቶ ጋጅ ሞተ። በሞተም ጊዜ ጭንቅላቱ ተወስዶ ዛሬ በሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በሕክምና ሙዚየም ውስጥ አጽሙ ከነብረቱ ተቀምጦ ለሕዝብ ይታያል።

በስፔይን ግዛት በማድሪድ አውራጃ ውስጥ ሴርቬራ የተባለች አምባ አለች። የአምባይቱ ነዋሪዎች በሙሉ የእግርና የእጅ ጣቶቻቸው ስድስት ስድስት ናቸው።

በኮሎራዶ አውራጃ ዴንቬር በተባለ ከተማ አንዲት ላም ተወልዳ ነበር። ላሚቱ እንደማንኛይቱም ላም ደንበኛው ጡት አላት። ከነዚያ ደንበኞቹ ጡቶችዋ ሌላ በጀርባዋ ላይ አራት ጡቶች አሉዋት። የሚያስደንቀው ነገር ላሚቱ በጀርባዋ ላይና ከታች ባሉት ጡቶችዋ በሁለቱም በኩል ወተት ትታለባለች።

በአሜሪካ አገር በቴክሳስ ክፍለ አገር ኢስት ላንድ በተባለው ከተማ አንድ የፍርድ ቤት ሕንፃ በ1897 ዓ.ም መሠረቱ በተጣለ ጊዜ አቶ ውድ የተባሉ ሰው አንድ ቀንዳማ ገበሎ በመሠረቱ ድንጋይ ሥር አኖሩ። ከሰላሳ አንድ ዓመት በኋላ በ1928 ዓ.ም የካቲት 17 ቀን ያ ገበሎ የነበረበት ድንጋይ ቢከፍት ገበሎው ሳይሞት በሕይወት ተገኘ። ከዚያ በኋላ ለሁለት ዓመታት ያህል ቆይቶ በ1930

ዓ.ም በጥር ወር ሞተ። ሐኪሞች ሬሳውን መርምረው የሞተው በብርድ በሽታ ነው አሉ።

# የሂሳቡ ሊቅ

በፈረንሳይ አገር ኦርማቲያር በተባለች ቀበሌ ፍሎወሪ የተባለ እውር ልጅ ተወለደ። ወላጆቹ በእውሩ ልጃቸው ዕድል ሲያዝኑ ፍሎውሪ በአጋጣሚ የሂሳብ ሊቅ ሆኖ ተገኘ። የፍሎውሪ የሂሳብ ሊቅነት በሕዝቡ ዘንድ እየተጋነነ ወሬው ተስፋፋ።

ከኤሮፓ የተውጣጡ 12 የሂሳብና የሳይንስ ሊቃውንት ተሰብስበው የፍሎሪውን የሂሳብ ሊቅነት መመርመር ጀመሩ። ሊቃውንቶቹ ለዕውሩ ልጅ ጥያቄ አቀረቡ። «64 ሳጥኖች አሉ። በመጀመሪያው ሳጥን አንድ ጥሬ ተቀምጧል፤ በሁለተኛው ሳጥን ሁለት ጥሬዎች አሉ በሦስተኛው ሳጥን የሁለተኛው ሳጥን አጠፌታ አለ፤ በአራተኛው ሳጥንም የሦስተኛው ሳጥን ውስጥ ያሉት ጥሬዎች አሉ። እንደዚሁ በአጠፌታ እየሆኑ ጥሬዎቹ 64ኛው ሳጥን ድረስ ይደርሳሉ። እንግዲህ በስልሳ አራቱም ሳጥኖች ውስጥ ያሉት ጥሬዎች ስንት ይሆናል» አሉት። ፍሎውሪ በግማሽ ደቂቃ ውስጥ መስሉ 9 223 372 836 854 775 808 ጥሬዎች ናቸው ብሎ ትክክለኛውን መልስ ሰጠ። ቁጥሩ ሲነበብ በአሜሪካኖቹ አነባበብ ኳንቲሊዮን 223 ኳድርልዮን 372 ትሪሊዮን 251 ቢሊዮን 603 ሚሊዮን 140.608 ነው።

ለፍሎውሪ ብዙ ጥያቄዎች ቀርበውለት ሁሉንም በትክክል በመመለሱ ታላቁ የእግዚአብሔር ተአምር ተባለ።

በሩሲያ ውስጥ እብኪየቭ ከተማ አቶ ሚቻልኮና አቶ ዋሲል ቤዝ ቦረንድንይ የተባሉ ሰዎች በጥፊ የመማታት ውድድር አድርገው ነበር። ውድድሩ በተጀመረበት ዐልት ሲጠፋጠፉ ውለው አሽናፊ ጠፋና እንደ ገና

ለሊቱን ቀጠሉ። በአጭሩ 36 ሰዓት ሙሉ በጥፊ ተደባደቡና አሸናፊው ሳይለይ በመቅረቱ ተመልካቹ ሕዝብ ለሁለቱም አጨብጭቦላቸው ዳኞች ገላገሉዋቸው።

በ1904 ዓ.ም የሩሲያና የጃፓን ጦርነት እንደ ተጀመረ መስኮባዊው ነጋዴ አቶ ሉማኪን «ከሐምሌ 1 ቀን 1904 ዓ.ም በፊት ጃፓኖች ሰላም እንዲሆን ይጠይቃሉ» ብሎ ተወራርዶ ነበርና ተረታ።

ስለተረታም የውርርዱ ጭብጥ የነበረውን ጫማውን ቀቅሎ እንዲበላ ተደርጎ በላ።

R.U.N የተባለው የእንግሊዝኛ ቃል 832 ትርጉም እንዳለው ሊቃውንት ይናገራሉ።

ኢጣልያዊው የኔፕልስ ነዋሪ ጁሴፔ ዲ ማይ ሁለት ልቦች ነበሩት። የለንደን የሕክምና አካዳሚ ጆሴፔ ዲ ማይ ሲሞት ሬሳውን ለመውሰድ ተዋዋሉና በቅድሚያ 37.500 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ተከፈለውና በ1894 ዓ.ም ሬሳውን አካዳሚው ወሰደው።

በአሜሪካ አገር በሚቺጋን ግዛት በሳንዴት ርይት የሚኖር አቶ አልፍሬድ የተባለ ሰው በዓይኑ መተንፈስ ይችል ነበር። የበራ ሻማ በእጁ ይዞ ያለ ምንም ችግር በዓይኑ ነፍስ በማውጣት ሻማውን ማጥፋት ይችል ነበር።

በፈረንሳይ አገር የናቴስ ነዋሪ የሆነው ፒየር የተባለ ሰው የቴያትር ቤት ተጨዋች ነበር። ይህ ሰው የራሱን ላይ ጠጉር በምንም ሳይነካ ቀጥ አድርጎ ማቆም ይችል ነበር። ፒየር የራሱን ጠጉር ብቻ ሳይሆን በአካሉ ላይ ያለውን ጠጉር ሁሉ የማዘዝ ኃይል የነበረው። ጠጉሮቹን ማቆም ብቻም ሳይሆን ቢፈግል ወደ ግራ ቢፈልግ ወደ ቀኝ ሊያስተኛው ይችል ነበር።

በአሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ (ከዛሬ 300 ዓመታት በፊት) በሩስያ ይገባያዩ የነበሩት ከቆዳ በተሠራ የጠፍር ገንዘብ ነበር።

ጆሴር ከስፐር የተባለ ኢጣልያዊ የበለኛሰው 114 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ይናገር ነበር ከዚህም ውስጥ ሰባ ሁለቱን ቋንቋዎች ከነፊደላቸው ጭምር ያውቃል።

ሳምዲ የተባሉ የሕንድ ጎሳዎች በሂንዱ ሃይማኖት እምነታቸው ጥንቁቆች ናቸው። በሚጾሙበት ጊዜ መጥፎ መናገር፤ ከማየትና ከመስማት ጭምር ይጾማሉ። ይህ የምታዩት ስዕል ከዮጊ ፎቶ ግራፍ ላይ የተቀዳ የምታዩት በሶም ጊዜ ተዘቅዝቆ ራሱን በጭቃ ውስጥ በመቅበር ለዘጠኝ ሰዓት ያህል ይቆያል። የዮጊን ፎቶ ግራፍ ለዓለም ያበረከቱት ጀርመናዊው ተጓዥ አቶ ፓውል ዶሴን ናቸው።

በአሜሪካ አገር ክላቬላንድ በተባለ ቦታ ወይም ከተማ በ1911 ዓ.ም ብሊፐር እና ትሬምብላይ የተባሉ ሰዎች ነፃ ትግል መታገል ጀምረው ያለማረፍ ሰባት ሰዓት ከ43 የትግል ጊዜ ውስጥ አንዱም አንደኛውን አልጣለም።

በአለባባማ ግዛት ነዋሪ የሆኑ አንድ ሰው ነበሩ። ስለእኚህ ሰው ወይዘሮ ፔሪ የተባሉ እመቤት ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል። «.......ጉሮሮአቸው በበሽታ ምክንያት ስለተበላሸ እንደማንኛውም ሰው ቆመው መናገር አይችሉም ነበር። ለመናገር በሚፈልጉበት ጊዜ በጀርባቸው ተንጋለው መተኛት አለባቸው......» 111.111.111 እነዚህ ቁጥሮች በራሳቸው በ11. 111. 111. ሲባዙ ውጤታቸው 12345678654321 ይሆናሉ። ካላመኑ አባዝተው ይሞክሩ፤ ወይም ያረጋግጡ፡

ፋኪር አጊስትያ ይባላሉ። በሕንድ አገር የቤንጋ ነዋሪ ነበሩ። በሂንዱ ሃይማኖት አማኝ ነበሩ አብጽአት ብለው ለጥቂት ጊዜ እጃቸውን ወደ ሰማይ ለመዘርጋትና ለመቆየት በ1902 ዓ.ም ለፈጣሪ ቃል ገቡ። እኚህ አማኝ

እጃቸውን ሦስት ወር ያህል ካቆሙ በኋላ ወደ ታች ልመልስህ ቢሉት እምቢ አለ። ተገትሮ ቀረ በኋላም አንዲት ለማዳ ትንሽ ወፍ በእጃቸው ላይ ጎጆ ሠራችበት። የፋኪር እጅ እንደተገተረ እስከ 1912 ዓ.ም ድረስ ለአሥር ዓመታት ቆየ።

በ1598 ዓ.ም የንጉሥ ሄንሪ ፫ኛ ልጅ በአራት ዓመት ዕድሜው ፍራንክቼስ ዶ ሎሬን የተባለችውን የሦስት ዓመት ልጅ በታላቅ ሥነ ሥርዓት በሚስትነት አግብቷታል።

ጀርመናዊው ሄንሪክ ሄይኔኬን በተወለደ በሁለት ወሩ መናገር ቻለ። በአሥራ ሦስት ወሩ ዕድሜው መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር በቃሉ የነበው ጀመር።

በአይርላንድ ውስጥ ቱላሞር በተባለች አምባ አቶና ወይዘሮ ሚካኤል ኩግላን የሚባሉ ባልና ሚስት ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ሰማንያ ዓመት ሙሉ በጋብቻ አብረው ኖረዋል። የሚያስደንቀው በዚህ የጋብቻ ዘመናቸው አንዲት ቀን እንኳን ተጨቃጭቀው አያውቁም።

በአሜሪካ አገር በሚቺጋን በአቶ ሐርሎው ክላርክ ግቢ የበቀለው ዛፍ ልክ ባርኔጣ አድርጎ ከዘራ የያዘ ሰው ይመስላል።

በጀርመን አገር በሀኖቨር ከተማ አንድ መቃብር አለ። በመቃብሩ ላይ የተጻፈው ጽሑፍ «ይህ መቃብር ለምን ጊዜም አይከፈትም» ይላል። ግን አንድ ዛፍ ከውስጥ በቅሎ ወጥቶ የመቃብሩን መከደኛ ድንጋይ ከፍቶታል።

እንግሊዛዊው አቶ ማክ ካቫና በ1831 ዓ.ም ተወልደው በ1889 ዓ.ም ሞቱ። አቶ ማክ ሲወለዱ እጅም እግርም አልነበራቸውም። እንዲያው ድብልብል ብለው ነው የተወለዱት ይላሉ አቶ ማክ ግን እጅና እግር ያላቸው ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር። ፈረስ መጋለብና አደን ማደን ይችሉ ነበር። ዓለምን በሙሉ ዞረው ያዩ ናቸው። በተለይም «ውቢቱ እጅ» በሚል አርእስት የጽፉት ድርሰት በታም ታዋቂና ዝነኛ አድርጓቸዋል በእንግሊዝ

ፓርላማም ገብተው ከ1866 እስከ 1880 ዓ.ም ለአሥራ አራት ዓመታት አገልግለዋል። ሕንድ አገር ሂደው ነብር አድነው ገለዋል። በስዕል አሳሳላቸውም የታወቁ ነበሩ። አንዲት ቆንጅዬ አግብተው ሰባት ልጆች አስወልደዋል።

በኒውዮርክ ከተማ ዳንኤል ፎርኑቶ የተባሉ ሰው ፓስታሹታ የምትባል አንዲት ኤሊ ነበረቻቸው የቦሒሚያን ወታደሮች መሪ የነበረው ሄጂትማን ሄጂ ትማን ጄኔራል ማለት ነው ጃንዚዝካ በ1376 ዓ.ም ተወልዶ በ1424 ዓ.ም ሞተ። ይህ ጄኔራል ከመሞቱ በፊት «ቆዳዬን ገፋችሁ የወታደሮች መሰለፊያ ከረቦ (ታምቡት) አድርጉት።» ብሎ ስለ ነበር ሲሞት ቆዳው ተገፎ ከረቦ ተበጀና በሕይወቱ ጊዜ ይመራቸው የነበሩትን ወታደሮች ሞቶም በቆዳው ይመራቸው ጀመር።

በሞሮኮ ውስጥ ሜክናስ የተባለች አገር አለች። በሜክናስ የሚያስደንቅ ታሪካዊ ሕንፃ አለ። ሕንፃውን ያሠራው የዘመኑ የአገሪቱ ንጉሥ የነበረው ሙላይ እስማኤል ነው። ሙላይ ሃምሳ ሺ ኤሮፓውያን የፈረንጅንጅ ባርያዎቹ ክርስቲያኖች ስለነበሩ ሙላይ ጠልቷቸው ያን ሕንፃ እንዲሠሩለት አዘዘና ሥራው በሃያ ዓመት ውስጥ አለቀ። በዚህም የሥራ ዘመን ውስጥ ማንኛውም የነጭ ባርያ ሲሞት ሬሳው ከድንጋይ ጋር አብሮ እንዲገነባ አዝዞ ስለነበር የሕንፃው ግማሽ ክፍል በሰው ሬሳ የተገነባ ነው። የሙሌይን ሌላ ታሪክ ከፈለጉ የ888 ልጆች አባት ነው።

ብታምኑም ባታምኑትም ይህን ሕንፃ ብቻቸውን የሠሩት እኚህ እውር ሰውዬ ናቸው። ምንም ማየት የማይችሉ ናቸው። እኚህ ፍራንሲስ አ ቡርዴት የተባሉ ሰው በአሜሪካ አገር የሠሩት ቤት ሰባት ክፍሎች ያሉት ፫ ፎቅ ነው። መታጠቢያ ቤቱ ሁሉ የተሟላ ነው። ቡርዴት የአናጢነት ሥራ ችሎታ አልነበራቸውም። ሁለቱም ዓይኖቻቸው የጠፉት በአምሳ ዓመት ዕድሜያቸው ነው። ዓይኖቻቸው በጠፋ በአሥራ ሦስት ዓመት በ63 ዓመት ዕድሜያቸው ቤቱን መሥራት ጀመሩ። መሰላል እንኳን የሚያቀርብላቸው ሰው ሳይዙ

ብቻቸውን መሰላል በማቅረብ በመውጣትና በመውረድ በሁለት ዓመት ከመንፈቅ ቤቱን ሠርተው ጨረሱ። ቤቱ አሁን የሕዝብ ኤግዚብሽን ሆኗል።

የጃፓን ነገሥታት ለአምስት መቶ ዓመታት ያህል የውል ማኅተማቸውን ያትሙ የነበረው የተቆረጠ የሰው መዳፍ በሰው ደም እየነከሩ ነበር።

ወይዘሮ ቴሬዛ ቫጉን ቫጉን የተባለች የሃያ አራት ዓመት ሴት በ1922 ዓ.ም በታኅሣሥ ወር በእንግሊዝ ፖሊሶች ተከሳ ከእንግሊዝ ፍርድ ቤት ቀርባ ነበር። የተከሰሰችበት ዋናው ምክንያት ከ62 ወንዶች ጋር በባልና ሚስትነት በሰማንያ ተፈራርማ በመገኘትዋ ነው። ሚስቴ ነሽ እያሉ የፈረሙላት ሰዎች በእንግሊዝ አገር፤ በጀርመንና በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚኖሩ ነበሩ። ፍርድ ቤት ስትቀርብም የ62 ባሎችዋ ፍሪማ አብሯት ቀርቧል።

በአራዊት ዓለም ውስጥ በጣም ትልቅ አንጎል ያለው ጉንዳን ብቻ ነው። ይሄውም የሁሉም አንጎል ከየአካሉ ጋር ሲመዛዘን ነው።

በኒውዝላንድ ውስጥ ቴኩ በተባለች መንደር በ1928 ዓ.ም አስደናቂ የባቄላ ሰብል ተገኝቶ ነበር። አንዱ ባቄላ (የፍሬው ስልቻ) ሁለት ሜትር ያህል ርዝማኔ ነበረው። የዚያ ባቄላ ገበሬ አቶ ሮቢንሰን ይባላሉ።

ከ246 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው እስከ 210 ዓመት ድረስ ቻያንን ይገዙ የነበሩት ግርማዊ ቺን ሺ ሁአንግቲ 13.140 ሚስቶች ነበሩዋቸው። ከእነኚሁ ሚስቶቻቸው 2.800 ልጆች አስወልደዋል። በቤተ መንግሥታቸው አሥር ሺ የመኝታ ክፍሎች ስለ ነበሩዋቸው በያንዳንዱ ክፍል አንዳንድ ቀን ብቻ በማደር ሃያ ሰባት ዓመታት አሳልፈዋል። ግርማዊ ቺን ሺ ሁአንግቲ እስከ ዛሬ ዝነኛ የሆነውን የቻይናን ግንብ ያስገነቡ ናቸው።

አሁን በዓለም ላይ ያሉ ነገሥታቶች ሲናገሩ «እኛ» እያሉ ነው። ይህንንም «እኛ» ማለትን የጀመሩ እኚሁ ንጉሠ ነገሥት ናቸው።

እስከ ዛሬ በዓለም ተወዳዳሪ ያልተገኘለት የእንግዳ አቀባበል በሕንድ አገር ለካሽሚሩ መሐራጃ የተደረገው ነው። አሥራ ስምንት ሰዎች በተዘረጋ ገመድ ላይ የሚል WEL COME ጽሕፈት ሆነው ተቀበሉዋቸው።

# የሚያዩት በዓይንዎ ብቻ ነው?

ዶክተር ሴሳሬ ሎምብሮሶ የተባሉ ሊቅ «ከሞት በኋላ» በሚለው መጽሐፋቸው ያጋጠሙዋቸውን ብዙ ነገሮች ጽፈዋል። ከጻፉዋቸው ብዙ ነገር አንዱ «......አንዲት የ፲፬ ዓመት ልጅ ታማ ወደኔ ዘንድ መጣች። ሐመምዋን በመድሐኒት እየተከላከልኩ ሳከማት ቆየሁ። ሕመምዋ ግን እየጠናባት ሄደ። በተቅማጥና በትውከት ስለተሰቃየች ፈሳሽ ምግቦችን እንድትመገብ አደረግሁ። ይህም ቢሆን ክብደቷ እየቀነሰና እየከሳች ሄደች። ሕመሙ በጀመራት በሦስተኛው ወር ዓይንዋ ፈጽሞ ታወረ።

«ዓይንዋ ፈጽሞ መታወሩን ለቤተሰቦችዋ ነግሬ እንዲህ በመሆኑ እኔም አዘንሁ። ልጅቱ ሁሉን ነገር እንደድሮዋ ማየት ጀመረች። በምንዋ እንደምታይ መመርመሬን ቀጠልሁ። ሌሎች ሐኪሞችን ጨምሬ ስንመረምራት ልጅቱ ማየት የቻለችው በአፍንጫዋ ጫፍና በግራ ጆሮዋ ጫፍ መሆኑን አረጋገጥን። የዓይንዋን አካባቢ በወፍራም ጨረቅ ሸእፍነን ልንፈትናት የሰጠናትን ጽሑፍ አነበበች የምታየውንም ሁሉ ነገረችን።

«ከጆሮዋ ላይ ብዙ ብርሃን ስናበራባት ብርሃኑን ትሸሻለች። ጣታችንን ወደ አፍንጫዋ ጫፍ ስናስጠጋ ‹ልታሳውሩኝ ነው እንዴ› ብላ ወደ ኋላ ታፈገፍጋለች።

«አፍንጫዋ ማየዋ እንጂ ማሽተቻዋ አልነበረም። የሚሰነፍጥ ሽታ ያለውን ጠንካራ አሞኒያ ወደ አፍንጫዋ ስናስጠጋላት ልጅቱ ምንም ስሜት

አታሳይም። ግን አሞኒያውን ወደ አገጭዋ ሥር ሳንደርገው ስነፈጠኝ ብላ ትጮሃለች።......» በማለት ያጋጠማቸውን ብዙ ሐተታ ጽፈዋል።

በ1818 ዓ.ም በኢጣልያ አገር በታተመው ኤሌክትሪኬት ኣኒማሌ በሚባለው መጽሐፍ ዶክተር ፔቴቲን ባቀረቡት ሪፖርት በጣታቸው ማየት የሚችሉ ስምንት ሴቶች ያጋጠሙዋቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በ1840 ዓ.ም በተባለው በታተመው ጆርናሌ ዴል አካዴሚካ ዲ ሜዲቺና በተባለው ጋዜጣ አንድ የሕክምና ሊቅ አንዲት በእጅዋ መዳፍ ማየት የምትችል ልጅ መኖርዋን ጽፈዋል።

በአትላንታ ከተማ የቅዱስ ፊሊፕስ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ራይሙንዶ ዳ አቪስ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሊነሳ ሲል በጻፉት ሪፖርት በቤተ ክርስቲያኑ ከሚኖሩ መሐል አንደኛው ዕውር በማጅራቱ ማየት እንደሚችል ገልጸዋል። ዕውሩ ሰው አንድ ነገር ለማየት ሲፈልግ እጁን ማጅራቱ ላይ ያደርግና ማንኛውም ዓይናማ ሊያይ የሚችለውን ማየት ይችላል ብለዋል።

በቱርክ አገር በእስታንቡል ከተማ በቅድስት ሶፊያ መቅደስ ውስጥ ካሉት የሕንፃው ምሰሶዎች አንደኛው ለአምስት መቶ ዓመታት ያህል አልቅሿል። ከተማይቱ በቱርኮች በተያዘች ጊዜ የመቅደሱ ምሰሶ ውሃ ማንጠባጠብ ጀምሮ ሳያቋርጥ ፭፻ ዓመታት ስለሆነ አልቃሻው ምሰሶ ይባላል።

ኖቮልዩስ ቶርካቱስ የተባላ ኢጣልያዊ የሚላኖ ሰው ባንድ ጊኤ ትንፋሹን ሳያቋርጥ ሦስት ጋሎን የወይን ጠጅ ይጠጣ ነበር። ይህንንም ችሎታውን ከንጉሥ ጥቤርዮስ ፊት ቀርቦ አሳይቷል።

በዓለም በትልቅነቱ ተወዳዳሪ የሌለውን መጽሐፍ ቅዱስ የሎስ አንጀሎስ አሜሪካዊ አቶ ሉዊስ ዋጅ ሜል በእጃቸው ጽፈዋል። የመጽሐፍ ቅዱሱ ቁመት አንድ ሜትር ተኩል ሲሆን ጎኑ ደግሞ አንድ ሜትር ነው። የገጹ ብዛት 8043 ነው። ክብደቱ አምስት መቶ ኪሎ ነው። የተጻፈው የላስቲክነት ጠባይ ባለው ወረቀት መሳይ ነገር ነው።

አቶ ዮሴፍ በርንሐርድ በጀርመን አገር በሙኒክ ከተማ ያለው የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ዲሬክተር ነበሩ። የሞቱት በ1828 ዓ.ም ነው። እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ ጸሐፊዎቻቸውን በአንድ ጊዜ በዘጠኝ ቋንቋዎች ስለ ዘጠኝ ጉዳዮች በዘጠኝ ዓይነት ፊደሎች ዘጠኙን ጸሐፊዎቻቸውን በቃላቸው እየነገሩ ያጽፉ ነበር። ከዚህም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስን ከብሉይ ኪዳን እስከ ሐዲስ ኪዳን፤ ከሐዲስ ኪዳን እስከ ብሉይ ኪዳን ወደ ፊት ወደ ኋላ በቃላቸው ያንበለብሉት ነበር።

# <u>የውሀ ጥንቆላ</u>

በፈረንሳይ አገር ከኦርሊንስ መሥፍን አሽከሮች አንዱ በ1699 ዓ.ም አንዲት ልጅ ወለደ። ልጅቱ ስምንት ዓመት ሲናት በውሀ ውስጥ እያየች ትንቢት መናገር ጀመረች። ይህ ነገር በአሽከሮችና በገረዶች ወሬው ስለ ተስፋፋ መሥፍኑ ልጅቷን በ1707 ዓ.ም ከእሱ ዘንድ እንድትቀርብ አድርጎ «ልጄ ሁሉ ነገር የሚታይሽ ከሆነ ታላቁ የፈረንሳይ ንጉሥ ነገሥት ሉዊስ ፲፬ኛ ሲሞቱ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸመው እንዴት ነው? ከእሳቸው በኋላስ በዙፋናቸው ላይ የሚቀመጠው ማነው? » አላት።

ልጅቱ በብርጭቆ ተሞልቶ ከተሰጣት ውሀ ውስጥ እየተመለከተች እያንዳንዳንዱን ሁኔታ እየዘረዘረች ትናገር ጀመር። ሬሳው የት እንደሚተኛ፤ አጃቢዎቹ ምን እንደሚለብሱ፤ መልካቸው ሁሉ ምን እንደሚመስል ዘርዝራ ተናገረች። ልዑሉ «ሌላስ የሚታይሽ ነገር የለም» አላት። «የብርጎኒ ልዑልና ልዕልት ይታዩኛል፤ የቤሪ ልዑልም ይታዩኛል፤ ግን በቀብሩ ቦታና ጊዜ የሉም» አለች። ይሄው የልጅቷ ንግግር በወረቀት ተጽፎ ለትዝብቱ ያህል ለትልልቅ ሰዎች ተሰጠ።

በ1638 ዓ.ም የተወለዱት ግርማዊ ሉዊስ ፲፬ኛ በ1715 ዓ.ም ልጅቱ በተነባች በስምንት ዓመት ሲሞቱ የተናገረችው ሁሉ በትክክል ደረሰ። በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ አይታዩኝም ያለቻቸው ልዑሎች ሁሉ ከንጉሡ በፊት ሞቱ።

የኖርዌይ ዳግማዊ ንጉሥ አላቭ በ995 ዓ.ም ተወልደው በ1030 ዓ.ም ሞተዋል። እኚህ የኖርዌ ንጉሥ ዳግማዊ አላቭ ሰንበትን በጣም የሚያከብሩ ታላቅ ሰው ነበሩ። በሰንበት ቀን ተሳስተው ወይም ረስተው አንዲት ቅጠል ቢበጥሱ እጃቸውን በእሳት ያቃጥሉት ነበር።

ፈረንሳዊው ሣልሣዊ ንጉሥ ሄንሪ ምግብ በሚመገቡበት ጊዜ እጃቸውን የሚነካካአው ወጥ በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉትን ነጭ የሀር ጌጥ እያበላሸ ስላስቸገራቸው አንድ ዘዴ ፈለጉ። አፍና እጃቸውን በሩቁ የሚያገናኝ ድልድይ አበጁ። ድልድዩም ሹካ ነው። ንጉሡ የሹካን ጠቃሚነት ስላወቁ ለሕዝቡ ሁሉ እንዲዳረስ አስበው በ1582 ዓ.ም ትልቅ ድግስ አስደግሰው ተጋባዡ ሁሉ በሹካ እንዲበላ አደረጉ። ከዚያ ወዲህ የሹካ ጠቃሚነትና ተፈላጊነት እየበዛ ሄደ።

እንግዲህ ሹካን ለዚህ ሕዝብ ያበረከቱ የሹካ ፈልሳፊ ንጉሥ ሄንሪ ናቸው። ሣልሳዊ ንጉሥ ሄንሪ በ1551 ዓ.ም ተወልደው በ1589 ዓ.ም የሞቱት የፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት ናቸው።

እርሶዎ 65% ኦክስጂን ነዎት

የእንግሊዙ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ሪቻርድ በመሐረብ መጠቀምን የፈጠሩ ናቸው የዳግማዊ ሪቻርድ ሌላው ታሪካቸው ደግሞ በ1396 ዓ.ም በተወለዱ 29 ዓመታቸው የፈረንሳይዋን ልዕልት በሰባት ዓመት ዕድሜዋ አግብተዋታል። አሁን ወደ መሐረቡ እንመለስና ዳግማዊ ሪቻርድ የግቢ ሚኒስትራቸውን «......ንጉሡ ዓይኑን የሚጠርግበት አፍንጫውን የሚያጠዳበት በእጁ የሚይዘው ቁራጭ ጨርቅ እየተዘጋጀ እንዲሰጠው......»

ብለው ስላዘዙ ከዚያ በኋላ ሕዝቡ ንጉሡን እያየ በመሐረብ መጠቀምን ጀመረ።

በቻይና አገር በሀንግቺው መታሰቢያ መቅደስ አንድ አልጋ አለ። በ514 ዓ.ም በዚያ ገዳም የነበረ ፓአቺህ የተባለ መነኩሴ ሲሞት «እመለሳለሁና የመነኩሴ አሽከሮችና የእነሱ ተከታዮች ፓኦ ቺህ ከዛሬ ነገር ይመጣል እያሉ አልጋውን ዘወትር እያነጠፉ ይጠብቁታል። የሚያስደንቀው ደግሞ የአልጋው ልብስ የቀኑ ይለወጣል። እንዲህ እየሆነለትም አምሳ ሰባት ትውልድ አልፏል። ፓኦ ቺህ እመጣለሁ ካለ 1400 ዓመታት አለፉ። አልጋው ግን እስከዛሬ ድረስ ይነጠፋሉ። እሱ ግን አልመጣም።

በ1949 ዓ.ም በሚያዝያ ወር አንድ ሌባ በፓሪስ ከተማ ያለውን የአራዊት ማሳያ (ዙ) በሩን ሰብሮ ገብቶ አንበሳውን ከነቤቱ ተሸክሞ ሰርቆት ሄድዋል።

በአንድ ብርጭቆ ወተት ውስጥ ከሚገኝ ውሀ ይልቅ በአንድ ቲማቲም ውስጥ የሚገኝ ውሀ ይበልጣል።

በሰሜን አፍሪካ አማስዋዚ የተባለች አገር አለች። የሀገሪቱ ነዋሪዎች ሴቶች የድሮ ባላቸውን ፈተው ወይም በሌላ ምክንያት ባል ለማግባት ሲፈልጉ ጥሩ ዓይነት ወጥ ወይም ገንፎ ይሠራሉ። ያን የሠሩትን ምግብ በጣባ አድርገው ራሳቸው ላይ ያስቀምጡና በአደባባይ መሐል ይቀመጣሉ።

በምግቡ ውስጥ ሁለት ማንኪያዎች ያስቀምጣሉ ሚስት ፈላጊ የሆነ ወንድ ሲመጣ ከዚያ ምግብ ዛቅ እያደረገ ይቀምሳል። ሞያዋን ለማወቅ አልፈለገ እንደሆነ በማንኪያው ከምግቡ ዛቅ ያደርግና ከመሬት አፍስሶ ያልፋል።

በእንዶኔዚያ አገር በሱማትራ አጠገብ ኢንታላንግ የተባለች ደሴት አለች። የደሴቲቱ አለቃ ወይም ባላባት የሚለየው በጠጉሩ አሠራር ነው። የጠጉሩ ዙርያ ክብ አንድ ሜትር ተኩል ያህል አድርገው ጠጉሩን የሚሠሩት አምስት ሰዎች ዙርያውን ከበው ነው። የጠጉሩ ሥራ አራት ቀንና አራት ለሊት ከተሠራ በኋላ ያልቃል፡

በሕንድ አገር የጃይፑር መሐራጃ ማንሲህ አንድ ሺ አምስት መቶ ሚስቶችና አራት ሺ ልጆች ነበሩዋቸው። ማሐራጃው ከ1592 ዓ.ም እስከ 1614 ዓ.ም ድረስ ጃይፑርን ገዝተዋል።

ኢጣልያዊው ፍራንቼስኮ ማርያ ግራፖልዶ የታወቁ ቅኔ ደርዳሪ ነበሩ። እስከዛሬ ድረስ ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው ገጣሚ ናቸው። በሁለት ብዕሮች፤ በሁለት አጆቻቸው እየጻፉ በአንድ ጊዜ በሁለት ቋንቋዎች ግጥም መግጠም ይችሉ ነበር። በፍራንቺስኮ በ1464 ዓ.ም ተወልደው በ1515 ዓ.ም ሞቱ።

በኢጣልያ አገር ሚላኖ ከተማ አጠገብ ቪላ ሲሞኔታ የሚሉት ቤት አለ። በዚያ አካባቢ አንድ ነገር ቢጮህ

በኢጣልያ አገር ሚላኖ ከተማ አጠገብ ቪላ ሲሞኔታ የሚሉት ቤት አለ። በዚያ አካባቢ አንድ ነገር ቢጮህ ማሚቶው (የድምፅ ማስተጋባቱ) ስልሳ ጊዜ ይሰማል።

የማዳጋስጋር ንግሥት በ1878 ዓ.ም ሞተው ሲቀበሩ የመቀበሪያቸው ሣጥን የተበጀው ሰላሳ ሺ ጥሬ ብር ተገጣጥሞ ተሠርቶነው።

በ1024 ዓ.ም እስከ 1066 ዓ.ም ድረስ እንግሊዝን የገዙት ንጉሥ ኤድዋርድ ከሰው የተለየ መልክ ነበራቸው። ዓይናቸው በርበሬ የመሰለ ቀይ ነው። ቆዳቸው ወተት የመሰለ ነጭ ነው። የራሳቸው ጠጉርና ጢማቸው ደግሞ እንደ በረዶ የነጣ ነበር።

በለንደን የአውሬዎች ማከማቻ ቦታ (ዙ) ውስጥ መነጥር የሚያደርግ እባብ ነበር።

ከ37 ዓመተ ምሕረት እስከ 41 ዓመተ ምሕረት ድረስ ሮማን የገዙት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ካሊጉላ ጢማቸው ወርቅ ነበር። የዘመኑ ማምለኪያ የጁፒተር ሐውልት ከወርቅ የተሠራ ስለ ነበረ ንጉሡም እንደ ጠጉር፤ ከቀጠኑ

የወርቅ ሽቦዎች ጢማቸውን አሠርተው ለሕዝብ የሚታዩ በወርቅ ጢማቸው ነበር።

ሎርድ ሐልዳን የተባሉ የእንግሊዝ ጦር ሚኒስቴር ጸሐፊና ከፍተኛ አማካሪ የነበሩት አንድ ቀንም ያለ ማቋረጥ አርባ ስምንት ዓመታት ሙሉ ለእናታቸው ደብድቤ ጽፈዋል። በ1877 ዓ.ም አባታቸው እንደ ሞቱ ለእናታቸው ደብዳቤ መጻፍ ጀምረው እናትዮዋ በሙቶ ዓመታቸው በ1925 ዓ.ም እስከ ሞቱ ድረስ አንዲት ቀንም ደብዳቤ መጻፋቸውን ባለማቋረጥ 17.532 ደብዳቤዎችን ጽፈውላቸዋል። ሎርድ ሐልዳን የሞቱት በ1928 ዓ.ም ሲሆን የተወለዱት በ1856 ዓ.ም ነበር።

በአፍሪካ ውስጥ በሴራሊዮን ግዛት ሜንዲ የተባለ ጎሣ አለ። የጎሣው ሴቶች በጠጉር ሥራ በዓለም ተወዳዳሪ የላቸውም። ማንኛይቱም ሴት በየቀኑ ከዚያ በፊት ባልታየ የጠጉር ሥራ ጠጉርዋን መሥራት አለባት። በሜንዲ ጎሣ ውስጥ አንድ ጊዜ የተሠራ ጠጉር የሚያገለግለው ለአንድ ቀን ብቻ ነው። ለሌላ ቀን ሌላ ዓይነት የጠጉር ሥር መፈጠር አለበት። አንዷ ባገኘችው የጠጉር ሥራ ሌላዋ በዚያ ዓይነት መጠቀምም ፈጽማ አትልችም።

በሕንድ አገር ብሒል በተባለ ጎሣ ዘንድ ልጅን መታቀፍ ወንጀል ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ከ150 ዓመታት በፊት የሀገሪቱን ንግሥት ልጅ እንቃቀፋለን ብለው ታቃፊዎቹ ስለጣሉት ከዚያ ወዲህ ልጅ ተይዞ ስለሚኬደው በስዕሉ እንደምታዩት ተደርጎ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ ዲንካ ጎሣ ሴቶች ጠጉራቸውን የሚሠሩት እንደ ባርኔጣ እያደረጉ ነው።

ፕሬዝዳንት ጀምስ ኤ ጋር ፊድል ባንድ ጊዜ ባንድ እጃቸው በላቲን ቋንቋ በሌላው እጃቸው ደግሞ በግሪክ ቋንቋና ፊደል መጻፍ ይችሉ ነበር።

የኮንታንቲኖፐል ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ግርማዊ ዳግማዊ ባልድዊን ይፈጅባቸው ነበር የፊርማችውን አጋማሽ አንድ ቀን ሙሉ ሲፈርሙ ይውሉና ጉራጁን ፊርማ ደግሞ ከሃያ አራት ሰዓት በኋላ ሙሉ ቀን ሲኩሉ ውለው ይጨርሳሉ። እኒህ ንጉሠ ነገሥት እንዲህ የሚያደርጉት የኩራት ነው እንጂ ባንዴ መጨረስ አቅቷቸው አይደለም። እኒህ ንጉሠ ነገሥት በ1217 ዓ.ም ተወልደው 1273 ዓ.ም ሞቱ።

በአፍሪካ ውስጥ አሩሳ የሚባል ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ሰዎች በፀሐይ ጊዜ ከቤታቸው ውጪ ሲሄዱ የሚያደርጉት ባርኔጣ የቤታቸውን ጣሪያ ነው።

በ1812 ዓ.ም ናፖሊዮን ሩቢያን በወጋ ጊዜ ሩስያውያኖች የፈረንሳዩን ወታደር ካፒቴን ለቫይን የተባሉትን ማረኳቸው። ምርኮኛው ካፒቴን በሳራቶቭ ወህኒ ቤታ ታሠሩ። በኋላም ነገሩ በሰላም ተጨርሶ ምርኮኞች ወደየአገራቸው ሲመለሱ ካፒቴኑ አልመልሰስም ብለው ከሶቪየት ቀሩ። እኒህ ምርኮኛ ልክ በተማረኩ በመቶ ዓመት ከአንድ ቀን በ1912 ዓ.ም ሞቱ። በሞቱበት ጊዜ ዕድሜያቸው 144 ዓመት ነበር። እኚህ ከመሞታቸው በፊት ወደፊታቸው እንዳይወድቁ ከዘራ የሚመረኮዙት በአንገታቸው ነበር።

1072 ዓ.ም የሞቱት ሡልጣን መሐመድ ኢብን ዳውድ ከሞት ተነስተው ይመጣሉ እየተባለ እስከ ዛሬ ድረስ እየተጫነ ይጠብቃቸዋል። ሡልጣኑ ኢራንን የሚገዙ ነበር። በዘመናቸው ኢራን «ወርቃማው የኢራን ዘመን» ይባል ነበር። ሡልጣኑ እንደ ሞቱ ነብይ ነን የሚሉ «ሡልጣኑ ከመቃብር ቤታቸው ወጥተው በፈረስ ተቀምጠው ከቤተ መንግሥታቸው ይገባሉ፤ ከዚያም ወዲያ ኢራንን በመንፈሳዊ አስተዳደር እየገዙ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያደርስዋታል። እያሉ ስለተነበዩ በየቀኑ በንጉሡ ኮርቻ የተጫነ ፈረስ የሡልጣኑ መቃብር ባለበት በኮርሳን አውራጃ በኩቻን መስጊድ ደጅ ይጠብቃቸዋል።

ቾንግ ዴን ቹንግ የተባለ ቻይናዊ የሽፍታ መሪ ስቹአን የተባለችውን አውራጃ ከ1643 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1648 ዓ.ም ድረስ በገዛበት እስከ 1648

ዓ.ም ድረስ በገዛበት በአምስት ዓመታት ጊዜ ውስት አርባ ሚሊዮን ሰዎች ገድሏል።

ከገደላቸውም ሰዎች ውስጥ ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሰዎች የስቹአን ሰላምዊ ዜጎች ናችው። የተቀሩት 32.310 ተማሪዎች 5.000 ወታደሮች፤ 27.000 የቡዲስት ቄሶች፤ 600.000 የቼንግቱ (የዋናው ከተማ) ነዋሪዎች፤ 280 የራሱን ሚስቶች፤ 400.000 የወታደኦቹን ሚስቶች ሴት ልጅጆችና እህቶቻቸውን ነው።

የፖርቱጋል ንጉሥ የነበሩት ጆአአ ፬ኛ ለሁለት ቃላት 585 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ሒሳብ ከፍለዋል። ቃላቶቹ «ሬይዴሊስሞ» ናቸው። ትርጉሙ «ታላቁ ታማኝ ንጉሥ« ማለት ነው። እንዲህ ላላቸው ሁሉ ሲቸሩ ቆዩና 1741 ዓ.ም የሰቱት ገንዘብ ቢታሰብ በዛሬው የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ከግማሽ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር በላይ ሆነ። በኋላ እኚህ በ1689 ዓ.ም የተወለዱት ንጉሠ ነገሥት 1750 ዓ.ም ቢሞቱ ለመቀበሪያቸው በግምጃ ቤታቸው ገንዘብ ስለጠፋ ሕዝቡ የገንዘብ መዋጮ ተጠይቆ ተቀበሩ።

አቶ አን ሉዊስ ጊሮዴት የተባሉት ፈረንሳዊ የታወቁ ስዕል ሳይ ነበሩ። በተለይ ከስዕል ሳዮች ሁሉ የሚለዩበት አንድ ጠባይ ነበራቸው። ስዕል የሚስሉት ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ነው። ለመሳል ሲነሱ ባርኔጣችወን ያደርጋሉ። ባርኔጣቸው አርባ ሻማዎች ይሸከማል። ሻማዎቹ ሁሉ ይለኮሱና በነዚያ ብርሃን እያዩ ብሩሻቸውን መቧጠጥ ይጀምራሉ።

በ13ኛው መቶ ዓመት የጀርመን መሪ የነበሩት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቻርለስ 4ኛ በአራት ነገሮች የተከበቡ ነበሩ። እራሳቸው አራተኛ ቻርለስ ናቸው። በቀን አራት ጊዜ ይመገባሉ፤ እያንዳንዳቸው አራት አራት ክፍሎች ያሏቸው አራት መኖርያ ቤቶች ነበሯቸው። በያንዳንዱ ክፍሎች ያሏቸው አራት መዝጊያዎች፤ 4 ጠረጴዛዎች አሉ። ዘውዳቸው 4 መዓዘን ሆኖ የተሠራ ነው።

የሚለብሱት ልብስ 4 ቀለማት ያለውን ነው። አራት ቋንቋዎች መናገር ይችላሉ። አራት ጊዜ ሚስት አግብተዋል። ሰረገላቸው በአራት ፈረሶች የሚጎተት ነበር። አገራቸውን በአራት አውራጃዎች ከፋፍለው ነበር። የጦር ኃይላቸው በአራት ክፍል የተመደበ ነበር። ንጉሡ ታመው ለሞት በሚያጥሩበት ጊዜ አራት ሐኪሞች ይጠብቁዋቸው ነበር። ኅዳር 29 ቀን 1378 ዓ.ም አራት ጊዜ «ደህና ሁኑ» ብለው አራት ሰዓት ከአራት ደቂቃ ሲሆን ሞቱ። ንጉሡ የተወለዱት በ1316 ዓ.ም ነበር።

በኒውዚላንድ ውስጥ ሱዚርላንድ የሚሉት ፏፏቴ አለ የውሃው አወራረድ ትክክለኛ የመስቀል ቅርጽ ይዞ ነው። የዚህ ፏፏቴ ርዝመት 1904 ጫማ ነው። በፏፏቴ ርዝመትም በዓለም አራተኛ ደረጃ የያዘ ነው።

በላኦስ የኢንዶ ቻይና ሰዎች ኪዋ የተባለው ጎሣ ልጃገረዲቱ ባል አጥታ ቆማ አጠገብ ትወስድና በውሀው ውስጥ ጥላዋን እንድታይ ትደረጋለች። የጥላዋን ማየትም እንደ ጋብቻ ስለሚቆጠርላት ልጅቱ ቆማ ቀረች ከሚባል ሐሚታ ትድናለች።

ፈረንሣዊ ሰዓሊ ማርሴል ደ ለኩለር በ1875 ዓ.ም አንዲት ሴት ወደደ፤ ጠፈ አበደ። አዘውትሮ የፍቅሩን መግለጫ ደብዳቤ ይጽፍላት ጀመር። ደብዳቤው ሲጀምር «ማግዳሊን ደ ቪላቶር» ይላል። ከዚያ በኋላ የሚቀጥለው ቃል «እወድሻለሁ» የሚል ብቻ ነው። ማርሴል በደብዳቤው ላይ 5.625.000 እወድሻለሁ እያለ ጽፏል።

ጆሴ ሲልቫ የተባለ በቦሊቪያ የነበረ እረኛ ሕንዶች ዓይነስቡን በቀስት ወጉት። በዓይኑ አቅጣጫ የገባው ቀስት እንዲወጣለት ቢጠየቅ አሻፈረኝ ብሎ የቀስቱን ጦር እንደ ተሸከመ አሥራ አንድ ዓመታት ሙሉ ኖሮ ሞተ፡

ጀምስ ሆማን የተባለ የእንግሊዝ መኰንን በባሕር ኃይል ውስጥ ይሠሩ ነበር። ይህ መኰንን በተወለደ በ24 ዓመት ዕድሜው ዓይኑ ታወረ። ዓይኑ

የታወረው በ1810 ዓ.ም ነው። ሆልማን ከታወረ ወዲህ በሠራው ሥራ በዕውር ታሪክ ውስጥ እስከ ዛሬ በመላው ዓለም የሚወዳደረው አልተገኘም። ፈረንሳይን፤ ኢጣልያንን ጀርመንን ስዊዘርላንድ ሆላንድን፤ አስትሪያን፤ ሩሲያን፤ ብራዚልን ኢየሩሳሌምን ጎብኝቷል። የጎበኘውም መሪ ሳይዝ ብቻውን ነው። በተለይ የሚደነቅለት ስለጎበኛቸው አገሮች ሁሉ የጻፈው የጉብኝት መጽሐፉ ነው። ሆልማን በተወለደ በ71 ዓመቱ በ1857 ዓ.ም ሞተ። ሆልማን ሕይወቱን በሙሉ እንደ እውርነት ኑሮ አልኖረም።

በአፍሪካ ውስጥ ብትን በርበሬ በአፍንጫ ውስጥ ጨምሮ ሳያስነጥሱ የመቆየት ውድድር ተደርጎ ነበር። በዚህ ውድድር ሞባካ የተባለች አፍሪካዊት አሸናፊ ሆናለች። ሞባካ በርበሬውን በአፍንጫዋ ውስጥ ይዛ ሳታስነጥስ አሥራ አንድ ሰዓት ቆይታለች። በዚህም የዓለም ሻምፒዮን ተብላለች።

ቤንጃሚን ኮንስታንት የተባለ ፈረንሳዊ ደራሲና የፖለቲካ ሰው አምስት ቮልዩም ሆኖ ነው በጠቅላላው 25000 ገጾጽ ያሏቸውን መጻሕፍት ጽፏል። የነዚህን መጻሕፍት ረቂቅ የጻፈው በመጫወቻ ካርታዎች ጀርባ ላይ ነው። ቤንጃሚን ኮንስታንት በ1767 ዓ.ም ተወልዶ በ1830 ዓ.ም ሞተ።

በድሮ ጊዜ በእንግሊዝ አገር አገጭዋ የረዘመባት ሴት ወደ ቁንጅና ማስተካከያ ቤት ትሄድና የረዘመ አገጭዋ እንዲስተካከልላት ትጠይቃለች። አስተካካዮቹ ሴትዮዋን ከባድ ብረት በእጇ ያስይዙና አገጭዋን ወድረው ወደ ላይ በመሳብ አንጠልጥለው ያቆዩዋታል።

ዮን ቶንግ የተባለ የቡዲስት ሃይማኖት አማኝ ቻይናዊ በሃያ ሁለት ዓመት ዕድሜው ለጸሎት ተቀመጠ። ከዚያች ከተቀመጠበት ቦታ ሳይነሳ ስልሳ ሁለ ዓመት ሙሉ እንደተቀመጠ ቆይቶ በ1760 ዓ.ም ሬሳው ተነሳ።

በመካከለኛው ሕንድ በባስታር አውራጃ ፖርጃ የተባለ ጎሣ አለ። በጎሣው ልማድ መሠረት ለሠርግ የተሠሩ ሰዎች ወደ ሠርጉ ቤት በሄዱ ጊዜ የግድ መጨፈር አለባቸው። የሚጨፍሩትም አሥራ ሁለት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው

ስድስቱ ከመሬት ቆመው ክንድ ለክንድ ይያያዛሉ። ስድስቱ ደግሞ ከእነኛ ትከድሻ ላይ ወጥተው ይጨፍራሉ። እንደ ገና ደግሞ ከላይ የነበሩት ይወርዱና ከመሬት ሆነው ክንድ ለክንድ ከተያያዙ በኋላ መጀመሪያ መጀመሪያ ከመሬት የነበሩት በተራቸው ከእነኛ ትከሻ ላይ ወጥተው ይጨፍራሉ። በጭፈራ በሚቆዩበት ጊዜ እንደተጠሩበት እንደ ሥርጉ ቤት ወዳጅነት ነው። እነኚህ ጎሣዎች አንድ እምነት አላቸው። በያንዳንዲቱ የጭፈራ ሰዓት ሙሽሮቹ ለአሥር ዓመታት በሰላም ይኖራሉ ብለው ያምናሉ።

በጀርመን አገር ይኖሩ የነበሩ ታላቁ ራቢ ጂዳህ ሚህለር በሳምንት ስድስቱን ቀን ምናምን ሳይቀምሱ ይጽሶሙ ነበር። በተወለዱ በሃምሳ ዓመት ዕድሜያቸው መጾሙን ጀመሩ።

ቅዳሜ ማታ መጾም ይጀምሩና አርብ ማታ ድረስ ምንም ሳይቀምሱ ይቆያሉ። አርብ ለሊትን ቅዳሜ ቀን ለሃያ ደቂቃ አራት ሰዓት ብቻ አይጾሙም። ታዲያ በእንዲህ ያለ ኑሮ አርባ አንድ ዓመት ሙሉ ያለማሳሳት ጾመዋል። እኚህ ታላቅ ሰው የተወለዱት በ1660 ዓ.ም ሲሆን የሞቱት በ91 ዓመታቸው በ1751 ዓ.ም ነው።

በስሜን ምዕራብ አሜሪካ ኦሪኮን የተባለ አገር አለ። በዚያ አገር በ1852 ዓ.ም የጨውና የወርቅ ዋጋ እኩል ነበር። በሌላ አነጋገር ጨውና ወርቅ እኩል ለእኩል ይለዋወጡ ነበር።

በምዕራብ አፍሪካ ፉላህ የሚባል ነገድ አለ። የነገዱ ቆነጃጅት በደንብ አጊጠው ለመታየት ሲፈልጉ የንብ ቀፎ ከነንቦቹ በራሳቸው ላይ እንደባርኔጣ አድርገው ወደ ገበያ ብቅ ይላሉ።

ኒኮላስ ኤድ መርት የተባለው ፈረንሳዊ ደራሲ 203 ዓይነት መጽሐፍት ደርሶ አሳትሟል። ከእነዚህ ወስጥ አንድ መቶ አምሳ ሁለቱ ከማንኛውም ሌላ መጽሐፍት የማይመሳሰሉ አዲስ ታሪኮች ናቸው። ኤድመርት መጻሕፍቶቹን ያሳተመው በወረቀት ላይ ረቂቅ አውጥቶ አይደለም። በቀጥታ ከማተሚያ ቤት

እየሄደ ለማተሚያ ቤቱ ሠራተኛ (ፊደል ለቃሚ) በቃሉ በመንገር ነው። በዚህ ምክንያት እስከ ዛሬ እንኤድመርት ያለ ደራሲ አልተገኘም።

በፓኪስታን አገር በላሆር ከተማ አከማን የተባለ ሰው 62 ዓመት ሙሉ ቫዚር ካን ከተባለ መቅደስ ደጃፍ በመቀመጥ ዕድሜውን ጨርስዋል። አከማን ከድሀ ቤተሰብ የተወለደ በመሆኑ በአምስት ዓመት ዕድሜው ወላጆቹ ከመቅደሱ ደጃፍ ከደረጃው ላይ አስቀምጠውት ሄዱ። ከዚያ የሚያነሳው አጥቶ በዚያው መኖርን ስለለመደ ከዚያች ቦታ በዝናብም ሆነ በፀሐይ ሳይነሳ እንዲችው እንደተጎለተ በ67 ዓመት ዕድሜው በ1913 ዓ.ም ሞተ።

የስውዲኑ ንጉሥ አዶልፍ ፍሬደሪክ (በ1710 ዓ.ም ተወልደው በ1771 ዓ.ም) ሰባት የሚያፈቅሩዋቸው ሴቶች (ቁባቶች) ነበሩዋቸው። ሁለቱ ቁባቶቻቸው አንዳንድ ዓይኖቻቸው እውር ነው። የሁለቱ ደግሞ አንዳንድ እግራቸው ቆራጣ ነው። የሁለቱ ደግሞ አንዳንድ እጆቻቸው ቆራጣ ነው። አንዱዋ እስከ ጭራሹ ሁለቱም እጆችዋ የተቆረጡ ናቸው። ታዲያ ንጉሡ እነዚህን ጎዶሎቻቸውን ከመጠን በላይ ያፈቅሩዋቸው ነበር።

የዳኒ ለንደን የተባለ ሰው ሲወለድ ጆሮው የማይሰማ ዲዳ ሆኖ ተወለደ። ካደገ በኋላ የቦክስ ጨዋታ አጥንቶ ቦክሰኛ ሆነ። በ1929 ዓ.ም በአጋር ቦክስ በብሮላይን መንደር ከተወዳዳሪው ጋር ቦክስ ሊገጥም ተሰለፈ። ከመጋጠሚያው ሥፍራ ወጥቶ ውድድሩ ተጀምሮ ተወዳዳሪው በደህና ጡጫ የዳኒን ራስ ቢደልዘው የዳኒ ጆሮ ሰማ። በአፉም መናገር ቻለ።

ሁአንግ ኧርን ናን የተባለ ቻይናዊ ስዕል ሳይ ስዕል የሚስለው በምላሱ ነበር። ቀለሙን በአፉ ውስጥ ይይዝና የመሳያው ጨርቅ ከተነጠፈበት ጠረጴዛ ላይ ተጋድሞ በአፉ ውስጥ የያዘውን ቀለም ቀስ በቀስ በመልቀቅ በምላሱ ይስላል። ይህንንም አሠራር እንደሚወደው ይናገር ነበር።

በ1840 ዓ.ም በግብጽ አገር ወታደር መሆን የተጠላ ነበር። በዚያ ዘመን መሐመድ አሊ የተባለው የግብጽ ወታደር «አንድ ዓይና የሆነ ወታደር

ኢያስፈልገኝምና ከሠራዊቱ ይሰናበት» ብሎ በማወጁ ሁለት ሬጂሜንት ወታደሮች ከውትድርና ለመሠናበት ሲሉ አንዳንድ ዓይናቸውን በገዛ እጃቸው እያወለቁ ጣሉት።

የደቡብ አሜሪካዊቷ ወይዘሮ ቪያል በ1941 ዓ.ም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በኤሮፓ ለሚዋጉት ወታድሮች ስንቅ ለመላክ 150 ጥብኛ (ኬክ) ጋገረች። ጋግራ እንደ ጨረሰች የጋብቻ ቀለበትዋን ከእጅዋ ላይ አጣችው። ሊጥ ስታቦካ ወልቆ በሊጡ ውስጥ መቅረቱን አወቀች። መቶ አምሳውን ጥቢኛ እያፈራረሰች ለመፈለግ ስለተቸገረች ከጥብኛዎቹ ጋር ወደ ጦሩ ሜዳ ደብዳቤ ላከች። ዳቦውን ሲበላ የጣት ቀለበት የሚያጋጥመው ወታደር እንዲመልስላት ነበር። እንዳለችው ሆነና ዳቦው ወደ ጦሩ ሜዳ ተልኮ የቀለበቱ ጉዳይ እየተነገረ ዳቦው ለወታደሮች ታደለ። ቀለበቱን ፶ አለቃ ሮኒ ቪያል በደረሰው ዳቦ ውስጥ አገኘው። ፶ አለቃ ሮኒ፤ ዳቦ የላከችው የወይዘሮ ቪያል ልጅ ነው።

በአሜሪካ አገር በካንሳስ ከተማ አቶ ስቹልዝ የተባሉት ሰው የሚነዱት አውቶሞቢል ከመሬት 27 ሜትር ያህል ወደ ሰማይ ተነስታ ከፊት ለፊቷ ከነበረ ፎቅ ቤት ከሁለተኛው ፎቅ ውስጥ በመስኮት ገብታለች።

በአሜሪካ አገር በሙዚሪ ነዋሪ የነበሩት አቶ ሮበርት ሞሪል በ1931 ዓ.ም ጥቅምት 16 ቀን ካሊበር 22 ሽጉጥ ይዘው ለአደን ወጣ አሉ። በጫካ ውስጥ ሲዘዋወሩ አዳለጣቸውና ወደቁ ሽጉጡ ባርቆ ሆዳቸውን መታቸው። ጥይቲቱ ለብዙ ጊዜ ይሰቃዩበት የነበረውን በሽታቸውን ትርፍ አንጀታቸውን በጥሳው ወጣች ሐኪሞች በቁስሉ ላይ ባደረጉት ምርመራ የትርፍ አንጀቱ አቆራረጥ ሐኪሞች እንደሚሠሩት ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጠው የሆዳቸውን ቀዳዳ ሰፉላቸው።

በፓሲፊክ ውቅያኖስ ባሉ ደሴቶች አሜሪካና ጃፓን ይዋጉባቸው በነበረ ጊዜ የካሊፎርኒያው ተወላጅ ፶ አለቃ ሜይሮን በዚያ ጦር ሜዳ ሆኖ ሲዋጋ እንጥሉ ወርዳ በሕመሙ ተጨንቆ ሳለ አንዲት ከጃፓኖች የተተኮሰች ጥይት

ጉሮሮውን መታችው። ጥይቲቱ ሌላ ጉዳት ሳታደርስበት እንጥሉን ቆርጣ ወጣች።

የታወቀው ታላቁ እንግሊዛዊ ደራሲ ዊልያም ሼክስፒር በጁልየስ ቄሳር ድርሰቱ ውስጥ ካስየስን ሲያናግረው «ሰዓቱ ሦስት ጊዜ ደወለ» ያሰኘዋል። የሚደውል ሰዓት የተፈጠረው ከጁልየስ ቄሳር አንድ ሺ ዓመታት በኋላ ነው። በጁልየስ ቄሳር ዘመነ መንግሥት የሚደውል ሰዓት አልነበረም።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሜሪካና ጃፓኖች ሲዋጉ ቢያክ በተባለ ደሴት ላይ ከሁለቱም በኩል የተተኮሱት ጥይቶች ከመድፋቸው አፍ እንደወጡ በመንገድ ላይ ተጋጭተው ተጓርሰው ተገኝተዋል።

በቻይና አገር በሃይናን አንዲት ሴት ባጠፋች ጊዜ የሚቀጣው ባልዋ ነው።

ይህ ስዕል በሕንድ ውቅያኖስ ላይ ያለችው ኮማሮ የተባለችው ደሴት ገዥ የነበረው የሡልጣን ሰይድ አሊ ፊርማ ነው። ሡልጣኑ ሲፈርሙ እባቡንና ጊንጡን ሁሉ ሲኩሉ ይውሉ ነበር።

ሻይ በተገኘ ጊዜ በተገኘበት በቻይና አገር እንደ ሰላጣ ቅጠል የሚበላ ነበር።

ደም ከውሀ ስድስት ጊዜ ይበልጥ ይወፍራል።

ሱዳኖች ሞትን ለማስፈራራት የእህል ጎተራቸውን አስፈሪና አስቀያሚ ጭንቅላት አስመስለው ይሠሩታል።

የስፔይኑ ንጉሥ ፊሊፕ 5ኛ (1621 – 1665) በአርባ አራት የአገዛዝ ዘመናቸው ለቤታቸው ማስጌጫ በዛሬው በኛ ብር ሂሳብ አምሳ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሦስት ሺ ብር ወጪ አድርገዋል። ከዚህ ገንዘብ ውስጥ 36.095.000 $ ለቤት ዕቃቸው ማስጌጫ ብቻና መለወጫ ብቻ የዋለ ሲሆን የተቀረው 15.048.000 $ ለቤቱ ማስጌጫ ሻማ የተዛበት ነው።

የሩስያ ንግሥት በ1693 ዓ.ም ተወለዱ በ1730 እስከ 1740 ዓ.ም (እስከ ሞቱ ድረስ ማለት ነው) ሩስያን ገዝተዋል። እኚህ ንግሥት በዕድሜያቸው እንኳን ገላቸውን ፊታቸውንም ታጥበው አያውቁም። ብቻ እጅና ፊታቸውን የቀለጠ ቅቤ ይቀቡ ነበር።

በኬንያ ውስጥ የሉምብዋ ነገድ የሆነ ሰው ሚስት ሲያገባ ሚስቱን በቆሎ እንድትዘራ ያደርጋታል። ያቺ አዲሱ ሚስት ቶሎ ቶሎ ብላ በቆሎዋን ዘርታ ታደርስና በሰላሳ ስልቻ በቆሎ ለባልዋ አዲስ ሚስት ትገዛለታለች።

የሩስያ መሪ የነበሩት ቀዳማዊ ሲዛር ኒኮላስ (1825 — 1855) ወታደሮቻቸው በሰልፍ በሚሄዱበት ጊዜ ውልምጥ ውልምጥ ሳይሉ ቀጥ ብለው እንዲራመዱ አዘዋል። አንድ ወታደር ለሥራው ብቁ መሆኑን ሲፈትኑም በባርኔጣው ላይ በብርጭቆ የተሞላ ውሀ ያደርጉና እንዲመራ ያዛሉ። ወታደሩ ቀጥ ብሎ ርምጃውን አሳምሮ መሄድ አለበት። በራሱ ላይ በብርጭቆ የያዘው ውሀ መፍሰስ ቀርቶ በባርኔጣው ላይ የተንጠባጠበ እንደሆነ በእያንዳንዷ ነጠብጣብ ልክ አንዳንድ ዓመት ከባድ ሥራ እንዲሠራ ይደረጋል።

በስዊዘርላንድ አገር ግሪንስስ በተባለ ቀበሌ የሚኖሩ ሰዎች በየመኝታ ቤታቸው ከአልጋቸው ራስጌ አንዳንድ ፉካ (ትንሽ መስኮት) ይደረጋል። ምክንያቱንም ሲናገሩ ሲሞቱ ነፍሳቸው የምትወጣበት እንድታጣ ነው ይላሉ።

ከአራዊት ሁሉ 4 ጉልበት (የጉልበት ሎሚ) ያለው ዝሆን ብቻ ነው።

ቱርቦ ጀት የሚባለው አይሮፕላን ለአንድ ሰዓት የሚጓዝበት ቤንዚን ከአንድ ሺ እስከ ሁለት ሺ ጋሎን ድረስ ነው። ለአውቶሞቢል ቢሆን የዓለምን ዙሪያ አንዴ ዞሮ እንደገና የዓለምን ግማሽ ያስኬዳል።

በአሜሪካ አገር የቴክሳሱ ነዋሪ ዲክ አለን ጆሮ ከነምልክቱ እንኳ አልፈጠረበትም። ዲክ ማንኛውንም ነገር የሚሰማው በአፉ ነበር። ዲክ የታወቀና በመላው ቴክሳስ ዝናው የገነነ ሙዚቀኛ ነበር።

የጥንት ሮማዋያን በግብዣ ላይ ከአንዲት ሴት ጋር በተገናኙ ጊዜ ለሴቲቱ ጤንነት ጥዋቸውን ያነሳሉ። በዚህም ጊዜ በሴቲቱ ስም በያንዳንዱ ፊደል ልክ አንዳንድ ብርጭቆ መጠጥ መጠጣት አለባቸው። ለምሳሌ እኔ የያኔዎቹን አይደለሁም እንጂ ለሚስቴ ጤንነት ጥዋዬን ባነሳ ሰባት ብርጭቆ መጠጣት አለብኝ። ስምዋ አዳነች ታደሰ ስለሆነ ነው። በፈረንጅኛው አዳነች ታደሰ አጻጻፍ ከሆነ አሥራ ስድስት ብርጭቆ መጠጥ መጠጣት አለብኝ ማለ ነው።

የእንግሊዙ ንጉሥ ዳግማዊ ሄንሪ (1133 – 1180) ሕይወታቸውን ሙሉ ምግባቸውን ይበሉ የነበሩት ቆመው ነበር። ንክ ቢጤ (ነርቭስ) ነበሩ።

በጅፍሪ ሐድሰን (1619 – 1682) የእንግሊዝ ወታደሮች የፈረሰኛ ክፍል ሹም ነበር። ቁመቱ ልክ አንድ ክንድ ወይም 18 ኢንች ነበር።

በባቲካን ያለው የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር በመቶ ዓመት አንድ ጊዜ ለሕዝብ ይታያል። እስከዚያ ድረስ የሚኖረው በአንድ ክፍል ውስጥ ተቆልፎበት ነው።

በኢንዶ ቻይና ሒኖይ ውስጥ በአንድ እግር የቆመ መቅደስ አለ። መቅደሱን ያሠሩት ንጉሥ ሊታይ ቶን ናቸው። የተሠራው በ1049 ዓ.ም ነው ንጉሡ መቅደሱን ያሠሩበት ምክንያት አንድ እግር የሆነ ሰው በሕልማቸው ስለታያቸው ያኔ አምልኮ ይበዛ ነበርና አንድ እግር የሆነች ቆራጣ ሴት አግብተ ንግሥት አሰኙዋት። መቅደሱንም ሠሩ። ችሎቱ ሁሉ በአንድ ሰው እንዲመራ አደረጉ።

በእንግሊዝ አገር በቅዱስ ሊዎናርዶ ቤተ ክርስቲያን መጋዘን ውስጥ በደንብ የተደረደረ አንድ ሺ አንድ መቶ የሰው ጭንቅላትና ስምንት ሺ የሰው አጥንቶች አሉ።

በአሜሪካ አገር በዋሽንግተን ከተማ ነዋሪ የነበረው አቶ ጅጆን ግሪፍዝ በአንድ ሳምንት 2720 ኪሎ ሜትር መንገድ በእግሩ ይጓዝ ነበር።

በአይርላንድ አገር ኮልዌን በተባለ ሠፈር የሚኖረው አቶ ማርታህ ማግኔሲ ታምረኛ ድምስጽ ነበረው። ካርሊንግ ፎርድ ከሚባለው ሐይቅ አጠገብ ቆሞ ደንበኛ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ድምፁ እስከ አራት ኪሎ ሜትር ተኩል ርቀት ድረስ አልፎ ከሐይቁ ባሻገር ከማዶ ይሰማ ነበር።

በሉሉ ደሴት የወይዘሮ ሚቼል ድምስት የዶሮ እንቁላል ቃቅፋ ሃያ አምስት ጫጩቶች ፈልፍላለች።

ቱታ ፒያዝ የተባለ ኢጣልያዊ (1879 – 1948) ዘጠኝ ሺ ጫማ ርዘምት ያለውን ተራራ የአምስት ዓመት ልጁን አዝሎ እየቧጠጠ ወጥቷል። በከፍተኛነታቸው የሚያስደንቁና መያዣና መጨበጫ የሌላቸውን ቋጥኛማ ተራራዎችን በሚያስገርም ሁኔታ እየወጣቸው የተከበረና የታወቀ ተራራ ወጪ ነበር። እንዲያውም የአልፐ ተራራ መሪ የሚል ቅጽል ተሰጥቶት ነእብር። በመጨረሻው በ1948 ዓ.ም ከብስክሌት ወድቆ ሞተ።

ዓይንን ሳይጨፍኑ ማነጠስ ፈጽሞ አይቻልም።

በሮም ያለው የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚቀደስበት።

በሕንድ አገር የቁና ሰዎች ሲቆጥሩ ሰላሳ አንድ ላይ ሲደርሱ ቁልኩ ኢንካምበጉይካካኡኩኢንሳክ ይላሉ። ስላለ አንድ ማለት ነው።

የታወቀው እንግሊዛዊ ስዕል ላይ ጆን ካርተር ከአንገቱ በታች ያለው አካሉ ጥምልምል ስለነበረ ስዕል የሚስለው ብሩሹን በጥርሱ እየያዘ ነበር።

በእንፋሎት የሚነዳ ጀልባ ከሙቅ ውሃ ውስጥ ይልቅ በቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ የበልተ ይሮጣል።

በኒውዮርክ ነዋሪ የነበሩት አሜሪካዊቷ ወይዘሮ ኤልሳቤጥ በርት በጎናቸው የተጣበቁ ሁለት አሣዎችን ከባሕር ውስጥ አጥምደው ይዘዋል።

በእንግሊዝ አገር በዊንቸስተር ካቴድራል ንግሥት ሜሪ ባል ሲያገቡ የተቀመጡበት ወንበር 400 ዓመታት ሙሉ ከነበረበት ሥፍራ ሳይነቃነቅ በክብር ተቀምጦ ኖርዋል።

በሕንድ አገር ፑና የተባለው ቀበሌ አገረ ገዥ የነበሩት ሰር ሮበርት ሲሞቱ በቤቱ በራፍ አንዲት አይጥ ወጣች። ከዚያን ጊዜ ማለት ከ1838 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1863 ዓ.ም ድረስ ሃያ አምስት ዓመታት ሙሉ ከገዥው በኢት ለሚወጡ አይጦች ከደጅ የሚቆሙት ዘበኞች ተገቢውን የክብር ሰላምታ ለአይጥ ይሰጡ ነበር። ማንኛውም አይት የሰር ሮበርት መንፈስ ወይም ነፍስ ናት ተብላ ትታሰብ ነበር።

አንዲት ቃል ስንናገር ሰባ ሁለት ጡንቻዎች ይነቃነቃሉ።

የፌንጣ ደም ነጭ ነው።

ዶሜኒኮ ባሌስትሬሪ የታወቀ ግጥም ገጣሚ ነበር። ኢጣልያዊ ነው። በ1741 ዓ.ም ሁለት መቶ ሰማንያ ገጽ ያለው የግጥም መጽሐፍ በግሪክ በላቲን በፈረንሳይ፤ በኢጣልያና በአረብኛ ቋንቋዎች ጽፏል። በነዚህ ሁሉ ቋንቋዎች ግጥሙ የተጻፈበት ዋናው ምክንያት ስለሞተችው ድመቱ ሙገዛ ነበር።

የግመል ጀርባ አጥንት ቀጥ ያለ ያልተወላገደ ነው።

በኢጣልያ አገር ከክርስቶስ ልደት በፊት 88ኛው ዓመት ላይ የሲሲሊ ገዥ የነበሩት ማንሊውስ አክሊውስ ጥፋተኞችን የሚቀጡት ወርቅ በእሳት ያቀልጡና እንደ ውሃ የሆነውን ወርቅ ከፍላቱ የተነሳ ሲፍለቀልቅ ያን ውሃ የሆነው ወርቅ በማጠጣት ነበር።

ኰሎኔል ጆን አሊ በአንዲት የእንግሊዝ ቤሳ ተወራርደው ከአይርላንድ እስከ ዳንዳ ልክ ያለውን የሃምሳ ሦስት ማይል ርቀት አሥር ሰዓት ሙሉ በእግራቸው ተጉዘው ስለጨረሱ ውርርዱን አሸነፍው ቢሳዋን ተቀብለዋል።

የፈረንሳይ አገር በፓሪስ ከተማ በ1935 ዓ.ም መስከረም ፳፪ ቀን አንድ ፋብሪካ ቤት ተቃጠለ። ፋብሪካው በሙሉ አመድ ሲሆን አንድ መጽሐፍ ብቻ ሳይቃጠል ተገኘ። የመጽሐፉ ስም «ለፈ» ይባላል። ትርጉሙ «እሳቱ» ማለት ነው።

በአሜሪካ አገር በማሣቹሴትስ ነዋሪ የነበሩት እመት አንባሌባ በዘጠና ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው ያለመነጥር መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡ ነበር። እመት ባሌባ መጽሐፍ ቅዱስን ሰማንያ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር በንባብ ወጥተውታል። እመት ባሌባ በ1758 ዓ.ም ተወልደው የሞቱት በዘጠና ሁለት ዓመታቸው በ1850 ዓ.ም ነው።

በአፍሪካ ውስጥ በኒጀር አገር ዝርማ የሚሉት አንድ ጎሣ አለ። የጎሣው ሴቶች አፍንጫቸው ላይ የተቆለፈ ቁልፍ በማንጠልጠል ያጌጣሉ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ አንድ የጠላት ወታደር ለመግደል የተደረገው ወጪ 362.500 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ነው። ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት በጠቅላላው የተደረገው ወጪ ሁለት ሺ ቢልዮን የኢትዮጵያ ብር ሲሆን ከ1939 – 1945 ዓ.ም ድረስ የተገደሉት ወታደሮች 3.579.000 ናቸው።

በአትላንቲክ ውቅያኖስ ባለው ሐይቅ ብሬይድስ ደሰኢት የሚኖሩ ሴቶች የጋብቻ ቀለበታቸው የሚታሰረው ሬሳቸው ላይ ነው።

በ1870 ዓ.ም የፓራጓይ ፕሬዝዳንት ከነበሩት ካቶ ለፔዝ ቤት አንድ ፓኬት ሲጃራ ጠፋ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከእነኚህ በሦስቱ ወታደሮች የሲጃራው ባዶ ፓኬት ሲጫወቱበት በመገኘቱ በሞት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸው በ1870 ዓ.ም ተገደሉ። ለመስረቃቸው ግን ምንም ማስረጃ አልተገኘም ነበር።

እንግሊዛዊው የኪልክ ሀምፕተን ነዋሪ የነበረው አቶ ጆን ግሪንቪል በተወለደ በ16 ዓመቱ ኒውበሪ ላይ በተደረገው ጦርነት በጥይት ተመትቶ

ከያዘው ከጦሩ ሜዳ ተቀበረ። የጆን ውሻ ይህን ታሪክ ያይ ነበርና መቃብሩን ቆፍሮ ጌታውን አወጣው። ጆን አልሞተም ነበር። ከመቃብር ከወጣ በኋላ 57 ዓመት ኖረ በ73 ዓመት ዕድሜው እውነተኛውን ሞት ሞቶ ለመጨረሻው ተቀበረ።

በፈረንሳይ አገር ካርካሶን በተባላ ከተማ የነበረ አንድ ሰው ሰራሽ ፏፏቴ ከ1830 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1848 ዓ.ም ድረስ አሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ በሰንበትና በበዓላት ቀን በውሀ ፈንታ ወይን ጠጅ ያፈስ ነበር።

በኢጣልያ አገር በኔፕል የዕቃ መጫኛ ጋሪ ብዙውን ጊዜ የሚጎትተው ፈረስ፤ በሬና አህያ አብረው ተጠምደው ነው።

እንግሊዛዊው የባትል ነዋሪ ኢሳቅ ኢንጋል (1676 – 1798) በአንድ መቶ ሃያ ስምንት ዓመት ዕድሜው ውስጥ አንዱን መቶ ዓመት ያሳለፈው ያንድ ቤተሰብ አሽከር በመሆን ነበር።

በሕንድ አገር በጃይፑር ቤተ መንግሥት ልዑላኖች የሚይዙት ሰይፍ በሐር ጨርቅ እየተጠቀለለ ነው። ምክንያቱም ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ዝርያቸው በሰይፍ እጁን ስለተቆረጠ የዚያን ጊዜ የተደነገገውን ይዘው ነው።

በብራዚል ሚናዝ ጄሪዝ አውራጃ አንድ ተራራው ድንጋይ እንደወፍራም ላስቲክ ሳይሰበር ይተጣጠፋል።

በአሜሪካ አገር በቴኒስ አቶ ዳዊት ትዌት የተባሉ ሰው ድመታቸውን ከጥርስ ሐኪም ዘንድ ወስደው ሰው ሠራሽ ጥርስ አስገቡላት። ከዚያ በኋላ ድመቷ በቆሎ ከቆረቆንዳው እየጋጠች ትበላ ጀመር።

በማሳቹሴትስ ነዋሪ የሆኑት አቶ ጆን በውርስ ከአንድ ጓደኛቸው ጋር ተወራረዱ። ውርርዱ «እኔ አንተ ከምትበላው ቁርስ የበለጠ ውድ የሆነ እበላለሁ ቢሉ ጓደኝዮው «አትበላም አለ። አሥር አሥር ብር አስይዘው

ተወራረዱ። ከዚህ በኋላ አቶ ጆን የመቶ ብር ኖት በዳቦ ውስጥ አድርገው በሉና ውርርዱን አሸነፉ።

ሡልጣን አብደል አዚዝ በ1830 ዓ.ም ተወልደው በ1876 ዓ.ም ሞቱ። ሡልጣኑ ቱርክን ከ1861 ዓ.ም እስከ 1876 እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ገዝተዋል። ሡልጣኑ ዘወትር የሚበሉት ያንድ ጊዜ ቁርስ ስልሳ እንቁላል እየተቀቀለ ነው።

በ1830 ዓ.ም በፈረንሳይ ሬቮሊሽን ጊዜ የፓሪስ ከተማ ዘበኞች የሚይዙት ጠመንጃ ከላዩ ዣንጥላ ይታሰርበት ነበር። ለዝናብና ለፀሐይ መከላከያ እንዲሆናቸው ተብሎ ነው።

ጋብርኤል ደ አኑንዚዮ (1863 – 1938) የተባለ ኢጣልያዊ ደራሲ 560 ገጾች ያሉትን «የሕይወት ነበልባል» የተባለውን ዝነኛ መጽሐፉን በ፳ ቀንና በ፳ ለሊት ጽፎ ጨረሰው። በነዚህ በሚጽፍባቸው ቀናት በሩን ቆልፎ ያለ ምንም ረፍት ሳይበላ እና ሳይጠጣ ጽፎ ጨረሰ ብቻ በየሁለት ሰዓት አንዳንድ ሲኒ ቡና ይጠጣ ነበር።

ዝንጀሮ ያላት አንጎ ሁለት ነው። አንዱ አንጉልዋ ሌላውን አካል ሲቆጣጠር አንዱ አንጎልዋ ደግም ጭራዋን ይቆጣጠራል።

አንድ መንፈሳዊ የሆነ የሕንድ ልጅ ከፉ እንዳይናገር በማለት ምላሱን አፉ ውቺ አውጥቶ በጦር መሣይ መርፌ ቆልፎት ይውል ነበር።

ጆን ኮንታሲው ፍጹም እውር ሆኖ የተወለደ ነው። በፈረንሳይ አገር ሉሾ በተባለ ቦታ በተባለ ቦታ ለሚሄዱ ቱሪስቶች ሁሉ ሰላሳ ዓመት ሙሉ የቀበሌው አስጎብኚ ሆኖ ሠርቷል።

የሮማው ንጉሠ እንገሥት ሐድሪያን የሮማን ወታደሮች በሙሉ እያንዳንዳቸውን ከነ ስማቸው ያውቁዋቸው ነበር። ንጉሡ በ78 ዓ.ም ተወልደው ሞቱ።

በእንግሊዝ አገር እንዲህ ዓይነቱን የጥፋተኞች መሠሪያ ጆን ማሥን የተባለ ሰውዬ በ1825 ዓ.ም ሠሪው። ሠሪው ጆን በነበረበት ተከሰሰና ሳይከፍል በመቅረቱ በሠራው መሣሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ታሠረበት።

ፈረንሳዊ ሻምበል ጀምስ አስቱዋርት ከ1754 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1804 ዓ.ም ድረስ አምሳ ዓመት ሙሉ ጢሙን ይላጭ የነበረው በየቀኑ አሥራ ሦስት ምላጮች እየለወጠ ነበር።

በቲክሳስ ግዛት በዳላስ ውስጥ ወይዘሮ ጆርጅ ሬይኖልድስ ድመትና አይጥ አርብተው ድመትና አይጥ በጓደኝነት አብረው ሲአልፉ ይውሉ ነበር።

በዌልስ ቋንቋ «እውርዋን በግ ግደል» ለማለት ‹ልላድድ ዳፍድ ድዳልል› ነው።

የግብጽ እረኞች በእረኝነት ቦታቸው እንቁላል የሚቀቅሉት በወንጭፍ ገመዳቸው ውስጥ በማሽከርከር ነው።

አሜሪካን ያገኘው ክርስቶፈር ኮሎምቦስ በሰላሳ ዓመት ዕድሜው ጠጉር እንደበረዶ የነጣ ነበር።

19ነኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሔይስ 4 ዓመት በኮሌጅ 4 ዓመት በምክር ቤት 4 ዓመት በአገረ ገዢነት አገልግለዋል 4 ዓመት በሲቪል ጦርነት ተዋግተዋል 4 ዓመት ቆስለዋል፤ 4 ዓመት የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሆነዋል።

ካናዳዊው ካሪ ሶላር እጅና እግሩን ታስሮ አምስት ማይል ርቀት በውሀ ውስጥ እየዋኘ ሄድዋል።

በአፍሪካ በዞሉ ጎሣ ሴት ባል ስታገባ ጠጉርዋን በማር እያጣበቀች በዚህ ስዕል እንደሚታየው ዓይነት አድርጋ ትሠራዋለች። ይህም የሙሽርነት ጊዜዋ እስቲያልቅ እስከ ስድስት ወር ድረስ ይቆያል። ከዚያ ዓይነቱ ሥራ ጠጉርዋ ተላቆ የበነነ እንደሆነ ጊዜውም ባይደርስም የሙሽርነት ጊዜዋ ይፈጸማል።

በ1785 ዓ.ም ግንቦት 20 ቀን በስኮትላንድ ጋሎዌዝ በተባለ ከተማ አቶ ጀምስ መስማን በስቅሳት እንዲቀጣ ተፈርዶበት ተሰቅሏል። የተገኘበትና ያስፈረደበት ወንጀል ፭ኛ የስኮትላንድ ጎረቤት አገር ዜጋ በእምህኑ፤ ፪ኛ ያለምክንያት በመንገድ ላይ በመዞሩ ነው።

በእንግሊዝ አገር ሐንገር ፎርድ ውስት ለስምንት መቶ ዓመታት ሲሠራበት የኖረ አንድ ባህል በር። በያመቱ በፋሲካ ሐሙስ ለቤተ ክርስቲያን መጠነኛ ገንዘብ ይለመናል። ገንዘብ የሚለመነው ወንድ ለገንዘብ ሰብሳቢዋ አንዲት ቤሳ ሰጥጦ እሷን መሣም አለበት።

በመካከለኛው አፍሪካ ሙን የተባለ ተራራ አለ። በዚያ ተራራ ላይ የሚኖሩ ሰዎች ወንዶቹ ሚስት በሚያገቡበት ጊዜ ረጅም ቧት ጫማ ያደረጉ ለመምሰል እግራቸው ላይ በቀለም ስዕል ይሠራሉ። ይህም የሙሽራው መለያ ምልክቱ ነው።

በአፍሪካ ከቻድ ውስጥ የሚነሳ ሻሪ የሚባል ወንዝ አለ። በዚያ ወንዝ አካባቢ የሚኖር ሴቶች ከባሎች ጋር በአንድ ጀልባ እንዳይሄዱ ክልክል ነው። ከገበያ መልስ ባልዮው ወንዙን በጀልባ ሲያቋርጥ ሚስቲቱ ሸቀጥዋን በራስዋ ተሸክማ በእግርዋ ወንዙን ታቋርጣለች።

በአውስትራሊያ ያሉ የአቦርጂን ሰዎች ለመለያ መታወቂያቸው ከጢማቸው አንዱን ጎን ብቻ ይላጫሉ። ግማሽ ፊቱ የተላጨ ሁሉ የእቦርጂን ጎሣ ሰው ነው።

በ1816 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር ልዩ ፒያኖ ተፈልስፎ ነበር። ፒያኖው አልጋ፤ ቁምሳጥንና ጠረጴዛ ነበረው። ፒያኒስቱ በመሸበት ቦታ ከዚያው ከፒያኖው ውስጥ ያድራል።

በስዊዘርላንድ አገር ኒድዋልደን በሚባል ቀበሌ የሚኖሩ ሴቶች ያለ ወንድ ብቸኛ መሆናቸውን የሚያስታውቁበት አንድ ጌጠኛ መርፌ ቢቴ ጠጉራቸው ላይ ከወደኋላቸው ያደርጋሉ።

በሉታንያ የእናት መቃብር የሚያጌጠው በልብ ቅርጽ በተበጃጁ ድንጋዮች ነው።

በሕንድ የአቦርስ ጠጉር አስተካካዮች በደንበኛቸው ጠጉር ሥር ቢለዋ ያደርጉና ቢለዋው ላይ ያረፈውን ጠጉር በሌላ ነገር መታ እምታ እያደረጉ ይቆርጣሉ።

የእስኮትላንዱ ሰር ጆን ካስካርት ሰባት ሚስቶቻቸውን ከሚስሎኝ ከተባለ ገደል ላይ እየገፈተሩ ከገድሉ ሥር ካለው ባሕር ውስጥ በመጨመር ከዚያችው ገደል ላይ እሳቸውን ገፍታ ሰባት ሚስቶቻቸው ከሞቱበት ባሕር ውስጥ ጨምራ ገደለቻቸው።

በዓለም ካሉት ወንበሮች ሁሉ ትልቁ የሚገኘው በቺጋጎ የቤት ዕቃ ማጠራቀሚያ አዳራሽ ውስጥ ነው። ወንበሩ ወደ ላይ ከፍታው አራት ሜትር ተኩል ሲሆን የመሐል መቀመጫው ሥፋት ሦስት ኪሎ ይሆናል።

በሀገራችን በጎሙጎፋ ጠቅላይ ግዛት በኮንሶ ውስጥ አንድ ሰው የሚገልድ ጀግና ሰው ሞቶ ከተቀበረ በኋላ በመቃብሩ ላይ የገደላቸው ሰዎች ምስል እየተቀረጸ ይቆማል።

በአፍሪካ ኢ.በ.በ.ዩ የተባለ አንድ ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ሴት ስትሞት ከተቀበረች በኋላ በቤትዋ ትሠራባቸው የነበሩት ዕቃዎችና ትራስዋ ጭምር በመቃብርዋ ላይ ይደረጋሉ።

በዓለም ዝነኛ ከሆኑት ተራራ ወጪዎች አንዱ ሰር ፍራንሲስ ጆሴፍ ነው 15.771 ርዝመት ያእልውን ሞንትብላ ንክን፤ 13.645 ጫማ ርዝመት ያለውን ጀንግፍራው፤ 14.690 ጫማ ርዝመት ያለውን ማተርሆርን የተባሉትን ተራራዎች ሁሉ ወጥቷል። ጆሴፍ ከተወለደ ከአራት ዓመት ዕድሜው ከ1836 ዓ.ም ጀምሮ ፍጹም የማያይ እውር ሰው ነበር። ጆሴፍ የሞተው በ1914 ዓ.ም ነው።

በእንግሊዝ አገር ቴክስበሪ ገዳም ውስጥ አባ ዮሐንስ ዌክማን ለመቀበሪያቸው ማለፊያ የመቃብር ቤት አሠሩ። መቃብር ቤቱን ካሠሩ በኋላ በመጥፋታቸው ምክንያት መቃብር ቤቱ ማንም ሳይቀበርበት 431 ዓመታት አልፈዋል።

በቱርክ አገር ኢስኒክ በተባለ ቀበሌ የሐኒባል መቃብር በሁለት ዛፎች መካከል ይገኛል ዛፎቹ ሐኒባል በተቀበረበት ጊዜ ማለት 2144 ዓመታት በፊት የተተከሉ ናቸው።

አርችቦልድ ካምፐቤል የተባሉ ሀብታም በ1876 ዓ.ም ለመሞት በሚያጣሩበት ጊዜ ገንዘባቸውን ሰብስበው ሲቆጥሩ አምሳ ብር ጎደለ። ቤተሰቦቻቸውን ተቆጥተው «ይቺን አምሳ ብር ካልሞላችሁ አልሞትም« አሉ። ቤተሰቦቹ የሽማግሌውን ቁጣ ፈርተው ያን የጎደለ አምሳ ብር ሲሞሉላቸው ካምፐቤል በሰላም ሞቱ። አሜሪካዊው ካምፔብል በ1797 ዓ.ም ሬኖይልድስቪል በሚባል አምባ የተወለዱ ናቸው።

የኮርያ ሰዎች ሁለቱንም እጆቻቸውን ነፃ ለማድረግ ዝናብ ውስጥ በሚሄዱበት ጊዜ አገጫቸው ላይ የሚታበት ዣንጥላ ያደርጋሉ።

በአፍሪካ የባሌክ ነገዶች መሪያቸው ወይም ባላባቶቻቸው ሞቶ ሲቀበር ከሬሳው አፍ ላይ ረጅም ሸንበቆ ያደርጉና አንደኛው ጫፍ ከመቃብሩ ውጪ እንዲውል ያደርጋሉ።

ከዚያ በኋላ በየሳምንቱ አርብ አርብ በዚያ በሸንበቆ ውስጥ የወይን ጠጅ ያፈሳሉ። ሲናገሩም የሟቹ መንፈስ እንዳይጠማ ብለን ነው ይላሉ።

በጃይማክ በ1907 ዓ.ም ጥር 14 ቀን ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ ደርሶ ብዙ ቤቶችን አፈራርሶ ነበር። ከአንደኛው የቤት ፍራሽ ውስጥ በመሬት መንቀጥቀጡ ምክንያት የተወላገዱ አንድ ጠርሙስና አንድ ብርጭቆ ተገኝተዋል።

በአሜሪካ ጎሽ አዳኞች ጎሽ ለማደን ሲሄዱ የነጭ ተኩላ ቆዳ ለብሰው ተኩላ መስለው ነው። ምክንያቱም ጎሾቹ ነጭ ተኩላ ስለማይፈሩ ወዳጅ መስለው ከመሐል ይገቡና ሆዳቸውን በጩቤ እየዘነጠሉ ጎሾቹን ይፈጇዋቸዋል።

ሙታን ይነሳሉ?

በአሜሪካ አገር በፊላደልፊያ ከተማ ነዋሪ የነበሩት ሟቹ ዶክተር ኤስ ዌር ሚቼል ለአሜሪካ የሕክምና ዶክተሮች ማኅበር የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል። ዶክተር ሚቼል በአሜሪአክ የኒኦሮሎጂካል ማኅበር ፕሬዝዳንት ነበሩ። የዶክተር ሚቼል ጽሑፍ እንዲህ ይላል።

«......ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል ሲሆን የመጨረሻውን በሽተኛ አክሜ አሰናበትኩት። ከወጥ ቤት ገብቼ አንድ ብርጭቆ ወተት ጠጣሁና ከማንበቢያ ክፍሌ ሆኜ መጽሐፍ ሳነብ የበሩ ደወል ተደወለ።

«በሩን ከፈትሁት። የማላውቃትን አንዲት ልጃገረድ አየሁ ስስ ልብስ ለብሳለች። ካፖርትም አልደረበችም። በዚያ በረዶ በሚወርድበት ለሊት እንዲህ ሁና በመምጣቷ ገርሞኝ ስመለከታት እግርዋ ላይ ብቻ ባለ ብዙ ቁፍል ኮፍ ጫማ አድርጋለች። ከቤቴ እልፍ ብሎ ካለው ኮረብታ ግርጌ ካሉት ድሆች ሰዎች የመጣች መሆንዋን ገመትሁ።

«በዚህ በረዶ እንዲህ ሁነሽ ለምን መጣሽ አልኳት። ልጅቱ በራፍዋን ገባ ብላ እናቴ በጣም ታማብኛለች፤ የሕክምና ርዳታ የሚያስፈልጋትም ልክ አሁን ነውና እባክህ እንሂድ፤ ቶሎ በል አለችኝ። «በረዶው እንደዶፍ ሲወርድ እንዴት አድርገን እንሄዳለን? ከቤትሽ አቅራቢያ ሐኪም የለምን? አልኳት። የለም ለማለት ራስዋን ስትነቀንቅ በቆብዋ ላይ ያለው በረዶ ከመሬት ተራገፈ። «ምንም ሐኪም የለም፤ እናቴ ልትሞትብኝ ነውና እባክህ እንሂድ» ብላ እንባዋን ዘረገፈችው።

«የሕክምና መሣሪያዎቹን ይዤ ልጅቷ መንገዱን እየመራች እኔ እየተከተልኳት ወደ እናትዋ ቤት እንጓዝ ጀመር። ልጅቷ በምንጓዝበት ጊዜ አንዴም አላነጋገረችኝም። እስትነአካቴው ወደኋላዋ እንኳን ዞር ብላ አላየችኝም። በዚያ በለሰለሰ በረዶ ላይ ኮቴዋን ሳታሰማ ከፊቴ ትሽቀነደር ጀመር።

«ድሆቹ የፋብሪካ ሠራተኞች ከሚኖሩበት ሠፈር ደረስን። ከአንድ ቤት አጠገብ ስንደርስ ልጅቱ መዝጊያውን ከፈተችልኝ ገባሁ። እስዋ በሩን ለኔ ለቃ ከጎን ቆመች። በቤቱ ውስጥ ፋኖስ በርቷል። ከቤቱ በአንደኛው ማዕዘን ግድግዳ አጠገብ አንዲት መካከለኛ ዕድሜ ያላት ወይዘሮ ተኝታ ስታቃስት ሰማሁ። ከዚያም ሥራዬን ጀመርኩ። ወሴትዮዋ የታመመችው ኒሞኒያ ነው። ልጅቷ እንደነገረችኝም በርግጥ ሴትዮዋ በጣም ታማለች። አስፈላጊውን አስቸኳይ መድሐኒት ከሰጠኋት በኋላ ነገ ደግሞ መጥቼ እንደማያት ለሴቲቱ ነገርኳት። በምድጃው ያለው እሳት ጠፍቶ ቤቱ እንደ ውሻ አፍንጫ ቀዝቅዞ ስለ ነበረ እሳት እንድታነድ ለመንገር ያቺን ያመጣችኝን ልጅ ፈልግኳት። አጣኋት። እንዲያውም ልብ ብል ከዚያ ቤት ከገባሁ ጀምሮ ልጅቷና ፈጽሜ አላየኋትም። በየሥርቻው ውስጥ ሁሉ ያቺን ያመጣችኝን ልጅ ፈለግሁኋት። መዝጊያውም ስገባ ክፍቱን እንደተውኩት አሁንም እንደተከፈተ ነው።

«በኋላ ከዚያው ከአጠገቤ ልጅቷ ልትጠራኝ የመጣች ጊዜ ለብሳው የነበረው ቀሚስና አድርጋው የነበረውን ጫማ ከዕቃ ላይ ተቀምጦ ተመለከትሁ። ምንም ዓይነት ኮሽታ አልሰማሁም ነበርና ይቺ ልጅ እንዴት ልብስዋን እንደለወጠችና ወዴት እንደጠፋች ማወቅ አቃተኝ።

«እየተንጎራደድሁ ፈለግኋት። ልብስዋ ከተቀመጠበት አጠገብ ሄጄ እመለከት ጀመር። ያቺ በሽተኛ የልጅቱ እናት በዓይንዋ የማደርገውን ሁሉ ታይ ነበርና ያ በረዶ የወረደበትን ልብስ ደረቅ በመሆኑ ስገረም አይታ «እሱ እኮ እይልጄ ልብስ ነው አለችኝ።

«አዎ የልጅሽ ልብስ መሆኑን አውቃለሁ፤ ስታመጣኝም ለብሳው ነበር፤ አሁን ከልጅሽ ጋር ለመነጋገር ስለምፈልግ የት ነው ያለችው» አልኳት። ያቺ በሽተኛ ሴት ዝም ብላ ቆእይች። ቀስ ብላም ፊትዋን ወደኔ አዞረችና «ከልጄ ለመነጋገር ትፈልጋለሁ? » አለችኝ።

«አዎን አልኳት።

«እሱን ልብስ ትለብስ የነበረችው ልጄ ከሁለት ወር በፊት ሞታለች።» አለችኝ። ከዚያችም ከሞተችው ልጅ ሌላ ልጅ እንደሌላት ነገረችኝ።

ወደዚያች በሽተኛ ሴት ቤት የወሰደኝ የሞተችው የበሽተኛይቱ ሴት ልጅ መንፈስ ኖርዋል» በማለት እይዶክተር ሚቹል ሪፖርት ሐተታውን ይጨርሳል።

ቶምስ ብራውስ የተባለ እንግሊዛዊ በ1743 ዓ.ም ዲቲንገን በተባለ ሥፍራ በተደረገው ጦርነት አፍንጫውን ተቆርጦ ጉምድ ሆነ። ከጊዜ በኋላ ፎናና ሆኖ እንዳይቀር የወርቅ አፍንጫ አሠርቶ አደረገ።

በፔሩ እንዲህ እንደስዕሉ ያለመጠጫ ነበራቸው። መጠጡ ከመጠጫው ውስጥ ሲያልቅ መጠጫው እያፏጨ አሳላፊውን ይጠራል።

በሕንድ አገር በቦምቤይ ከተማ የትራፊክ ፖሊሶች የዝናብና የፀሐይ መከላከያ ዣንጥላ ያደርጋሉ። እጆቻቸው ዣንጥላውን በመያዝ እንዳይቸገሩ ዣንጥላው በወገብ ላይ ታስሮ በደረት የሚደገፍ ነው።

በኔፓል ያሉ ሰዎች የሂማልያን ተራራ በሚወጡበት ጊዜ መርፌና ክር አይለያቸውም። ከጉዞው ብዛት የተነሳ የውስጥ እግራቸው ቆዳ ሲቀደድ በመርፌና በክር ሰፍተው ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ።

በቦርንዮ ውስጥ ባሁዳያክ የተባለ ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ሴቶች ልጆቻቸውን ሲያስተኙ በጨርቅ ጠቅልለው እንደዥውዥው በሚያጫውት ገመድ አስረው ከዛፍ ላይ ይሰቅሉዋቸዋል።

ማሩታንያ ውስጥ ኔሜዲ የተባለ ጎሣ አለ። የጎሣው ሰዎች ለሚስት ማጫ ጥሎሽ የሚሰጡት ሁለት ውሾችን ነው።

የዝንብ ክፍል በአንድ ደቂቃ 19.800 ጊዜ ይርገበገባል።

በኢራንድ አንድ ሙሽራ የሚያገባትን ልጅ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያያት የሥርጉ ዕለት በመስተዋት ውስጥ ነው። ከዚያ በፊት ፈጽመው አይተያዩም።

በቲቤት ውስጥ ያሉ ጠንቋዮች ከሰው አጥንት እየተቀረጸ የሚሠራ ተክሊልና ጌጥ ያደርጋሉ።

ኮርያኖች ለአባት ሞት ኀዘን ሦስት ዓመት ሙሉ ነጭ ባርኔጣ ያደርጋሉ። ለእናት ሞት ሁለት ዓመት ያደርጋሉ። ለሚስት ሞት ግን ፈጽመው አያደርጉም። ምክንያቱንም ሲያስረዱ ሚስት በቀላሉ ልትተካ የምትችል ናት ይላሉ።

የሞሮኮ ሴቶች አብዛኛዎቹ ጫማና የእግር ሹራብ የእጅ ሹራብም ጭምር ያደረጉ እንደሚመስሉ እግርና እጆቻቸውን በሚያምር ሁኔታ ይነቀሱታል።

ኤልሳቤጥ ኬልሴይ የተባለች ሴት ዮናታን ቲቱስ የተባለውን ሰው ስታገባ የጋብቻ ስነ ሥርዓትዋ በ1826 ዓ.ም ስልስበሪ ውስጥ የተፈጸመው በወንድሟ ሳልስበሪ ውስጥ የተፈጸመው በወንድሟ መቃብር አጠገብ ነው ወንድምዋ ጋብቻውን ሳያይ በመሞቱ በጣም አዝና ነበርና መቃብሩን ክፈቱልኝ ብላ ከተከፈተ መቃብሩ አጠገብ በቄሱ ፊት ምላ ጋብቻዋን ፈጸመች።

የአፍጋኒስታን አህዮች በጣም አጫጭሮች ናቸው። በአህዮቹ ላይ ተቀምጠው የሚሄዱ ሰዎች አህያይቱ በደከማት ጊዜ ከላይዋ ላይ ሳይወርዱ በእግራቸው መሄድ ይችላሉ።

በእግሊዝ አገር ብራድሌይ በሚባል ቀበሌ ይኖር የነበረ ሪቻርድ ዳውሰን የተባለ ሰው በ1625 ዓ.ም ለመሞት ሲያጣጥር ከቤት ወጥቶ ከመቃብር

ሥፍራ መቃብሩን ቆፍሮ ጨረሰና ከውስጡ ተኝቶ ሞተ። ይህን ያደረገበት ምክንያት ሰውየው 150 ኪሎ ገደማ ይከብድ ስለ ነበረ «ሬሳዬን የሚሸከሙ ሰዎች መቸገር የለባቸውም» ብሎ ነው።

በ17ኛው መቶ ዓመት በኤሮፕ ውስጥ የነበሩ ጥርስ ሐኪሞች የሚያክሙት በፈረስ እየተዘዋወሩ ከመንገዱ ከፈረሳቸው ሳይወርዱ ነበር።

# የራስ ምታት ዓይነቱ 47 ነው።

በእንግሊዝ አገር ሶሀም በተባለ ቦታ የሚኖሩ አንድ ገበሬ አንድ ዕለት ማታ ተኝቶ በሕልሙ ያያትን ልጅ ለማግኘት አንድ ወር ሙሉ ሌላ ሥራ ሳይሠራ በየቤቱ እየዞረ ሲፈልጋት ከርሞ አገኛት። ከዚያም በኋላ ያቺኑ ልጅ አግብቶ አርባ ዓመት ሙሉ በሰላም ኖረው በ1764 ዓ.ም ሞተ።

በሱዳን አገር በአባይ ዳርቻ የሚኖሩ ሰዎች ደንበኛ ጌጥ ሲያጌጡ ጠጉራቸውን በአባይ አፈር በመቀባት እንደ ባርኔጣ ይሠሩታል።

በአፍሪካ አካፒ የተባለ አውሬ አለ። አንገትና ጭንቅላቱ የቀጭኔ ሲሆን ሌላው አካሉ የሜዳ አህያ ነው።

በፈረንሳይ አገር ኲል ደ ላስክልየ በተባለ ሥፍራ ብቻ የተሠራ አንድ ድልድይ አለ።

በኒንግሃም የነበሩት ጀርመናዊቷ ወይዘሮ ባርባራ ሽምዘሪን 53 ልጆች ወልደዋል።

በቦርኒዮ የአገሩ ተወላጅ የሆነው አንሣ የተባለ ሰው በአዞ አዳኝነቱ እስካሁን ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነው። በጦር በመውጋት ብቻ አሥር ሺ አዞዎችን ገድሏል።

በኮንጎ 800 ማይል ርዝመት ያለው አርዊሚ የሚባል ጅረት አለ። የጅረቱ ስም የተሰየመው የዳቪድ ሊቪንግስተን ነው። ሊቪንግስተን ከወንዙ አጠገብ ደርሶ አንዱን ባላገር በእንግሊዝ ቋንቋ «የዚህ ወንዝ ስም ማን ይባላል? » ብሎ ጠየቀው። አሩዊሚ ማለት «ምን ይላል ይህ ሰው? » ማለት ነው። ሊቪንግስተን ግን የወንዙን ስም የነገረው መስሎት የወንዙን ስም አሩዊሚ ስላለው እስከ ዛሬ የወንዙ ስም አሩዊሚ ተብሎ ቀረ።

ዊሊያም ማትሎክ የተባለ ሰው ገንዘቡን በዶንያ ሙሉ ይሸከምና ከባንክ ያገባል። ይህን ያዩ አጎብጓቢዎች «ሀብታም ሆኖ እስቲ በአሸከርና ቢያሸከመው ምናለበት? ምን ያለው ስስታም ነው? » እያሉ ሲያሙት ሰማና አንድ ቀን ያን ሸክሙን ከመሬት አስቀምጦ «አንስቶ መውሰድ የሚችል ሰው ገንዘቡን በሙሉ ለራሱ ይውሰደው» ብሎ አወጀ። ባለጉልበታም ሁሉ ተሰብስቦ ያን የብር ዶንያ ለማንሳት ሞከሩ። ግን አንድም ንቅንቅ የሚያደርገው ጠፋ።

እንግሊዛዊው አቶ ዳኒስ አትሌይ ከሚስታቸው ጋር ሁለት ዓመት ሙሉ አብረው ሲኖሩ በየቀኑ ከቤታቸው ሲወጡ በሚስታቸው ላይ እየቆለፉ ነበር።

በአውስትራሊያ ማዶ የሚሉት አሣ አለ። አሣው ማዶ ተብሎ የሚጠራው በወገቡ ላይ MADO የሚል የተፈጥሮ ጽሑፍ ስላለበት ነው።

በ1889 ዓ.ም በአውስትራሊያ አገር ሸፍፊልድ በተባለ አምባ የዓመቱ የዛፍ ቆረጣ ውድድር ተደርጎ ነበር። በዚህ የዛፍ ቆረጣ ውድድር አሸናፊ ሆኖ የተሸለመው አንድ እጁ ቆራጣ የሆነው ኒኪ ዊልያም የተባለ ሰው ነው።

ጋና እዚሁ አፍሪካ ውስጥ ባሉ አውቶብሶች ላይ ከኋላቸው «ለመልካም መጨረሻችን ጸልዩ» የሚል ጽሑፍ ይጻፍባቸው ነበር። አሁን ቀርቶ እንደሆን አላውቅም።

ጀርመናዊው ሄርማን ኡንታን እጅ ፈጽሞ አልተፈጠረለትም ነበር። ያለ እጅ በዓለም የታወቀ ቫይለን (ማሲንቆ) መቺ ሆንዋል። ቫይለኑን የሚከረክረው

በእግሩ ነው። ከዚህም ሌላ በእግሩ በረጅም እንጨት እንቾት ላይ የተሰካ ምላጭ ይዞ ጢሙን መላጨት ይችል ነበር። በአንደኛው እግሩ እርሳስ ይዞ ሌላው እግሩ በያዘው ምላጭ እርሳስ ይቀርጻል ሄርማን በ1848 ዓ.ም ሲወለድ ያለ ምንም እጅ ተወለደ። ዕድሜውን ሙሉ ማናቸውንም ሥራ ሲሠራ ኖሮ በ1928 ዓ.ም ሞተ።

በፊጂ ደሴት የሚገበያዩበት የገንዘብ ቀበሮ መንጋጋ ነው።

ፈረንሳዊው አንቷን ደልቫን ሚስቱ ሞታ ተቀበረች። ሚስቲቱ በሕይወቷ በነበረችበት ጊዜ ፖልካ የተባለውን ዜማ ትወድ ስለ ነእብረ ደልቫን 23 ዓመታት ሙሉ ያለማቋረጥ በየቀኑ በመቃብሯ ላይ እየቆመ ፖልካ የተባለውን ዜማ አዚሞላታል።

በአሜሪካ አገር በኒውጀርሲ ውስጥ ቲኔክ በተባለች አምባ ይኖሩ የነበሩት አቶ ጀምስ ሆኪንግ የተባሉ ሰው ጀምስ ሆኪንግ የተባሉ ሰው በ92 ዓመት ዕድሜያቸው 64 ኪሎ ሜትር መንገድ ሳያርፉ ተጉዘው በዘጠኝ ሰዓት ጨርሰውታል።

በሕንድ ውቅያኖስ ስኮትራ በተባለች ደሴት አንድ ሌባ ሲያዝ እጁ ይቆረጥና ለሕዝብ እንዲታይ በአደባባይ ይሰቀል ነበር።

በኒውጊያን ግዛት ዋጊፋ በተባለች ደሴት የሚኖሩ አሣ አጣማጆች ጀልባ የሚሠሩት ሳጎ የሚሉትን ቅጠል ቀጣጥለው እየሰፉ ነው።

በጀርመን አገር ሎንዶርፍ በተባለች ቀበሌ ይኖር የነበረ ጆሐን ቾአቺም ሩቤል የተባለ ሰው ትንባሆ ባፓፒ በሚጠጣበት ጊዜ በየቀኑ አንዳንድ ፒፓ ያቃጥል ነበር። በ1706 ዓ.ም ተወልዶ በ1786 ዓ.ም የሞተው ሩቤል በ80 ዓመት ዕድሜው ስልሳውን ዓመት ትንባሆ ሲያጨስ በዚህ ዘመን 21.916 ፒፓዎች አቃጥሏል።

በሕንድ አገር አሪስ ውስጥ ጁናግ የተባለ ጎሣ ሰዎች በጣም ጥሩ የሆነ መኖሪያ ቤት ይሠራሉ። በዚያ ቤታቸው ሰዎቹ አያድሩበትም። ሰዎቹ የሚያድሩት ከውጪ ነው። ቤቱን ግን ለፍየሎች ማደሪያ ያደርጉታል።

በሱዳን አገር ወላጅ እናቶች ልጃቸውን ያዝሉና በራሳቸው ላይ ውሀ ተሸከመው ውሀውን በማንቦጫቦጭ እያፈሰሱ ልጅቸውን ያጥባሉ።

አንድ የስዊስ ወታደር በፈረንሳይ አገር በፓሪስ ከተማ ተገደለና በ1830 ዓ.ም ጥር 29 ቀን ተቀበረ። የጌታውን ሬሳ አጅቦ የሄድው ውሻ በጌታው መቃብር ላይ ለሊትና ቀን ሳይለይ በዘብ ሥራ ቆይቶ በጌታው መቃብር ላይ በረሃብ ሞተ።

በቻይና አገር ያሉ ወላጆች የሚያደርጉት፤ ባርኔጣ ከነታዘለው ልጃቸው ጋር የሚበቃ ነው። የሚሠራውም ለሁለቱም እንዲበቃ እየተባለ ነው።

በስኮትላንድ አገር በ1688 ዓ.ም ኮፊንግተን የተባሉ ሰው ሞቱና ክፍት በሆነ የመቃብር ቤታቸው አኖሩዋቸው ለቀስተኛው ተመልሶ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የልጅ ልጃቸው ለመጨረሻ ስንብት ከአያትዋ ሬሳ ዘንድ ሄዳ የሬሳውን ጢም ስትደባብስ ሰውዬው አነጠሱ። ሐኪም ተጠርቶ መረመሩዋቸውና ያልሞቱ ሆኑ። ከዚያ በኋላ 12 ዓመት ኖረው ሞቱ።

የቲቤት ፖሊሶች የሚለብሱት ልብስ የመነኮሳት ልብስ የሚመስል ነው።

ቲቤታውያን ይህን ሕንፃ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሬት ላይ ወይም በዓለም ላይ የተሠራው ይላሉ።

ከመሬት የሚደርሰው የፀሐይ ሙቀት ሦስት አሥር ሺ ሚሊዮንኛ ነው። ከሙቶ እጅ አምስቱ የሚደርስ ቢሆን ኖሮ ሕይወት አይገኝም ነበር።

የቲቤት መንፈሳውያን ሰዎች ምጽዋት የሚቀበሉት በሰው ጭንቅላት አጥንት ነው።

በ1740 ዓ.ም ተነስቶ ለነበረው ቀዝቃዛ ጦርነት ለሩሲያ ንግሥት ሁለት መድፎች ተሥርተውላቸው ነበር። በመድፎቹ የበረዶ ጥይት ተተኩሶባቸዋል።

ባሊ በተባለች ደሴት እንደ ሀገራችን እንደ ላሊበላ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ዓይነት ከተፈጥሮ ድንጋይ እየተቦረቦሩ የተሠሩ ዘጠኝ መቅደሶች አሉ።

አልፍሬድ እስቲቬንስ (1817 – 1878) የተባሉ የታወቁ የእንግሊዝ ታላቅ ሰው ውሾችን በጣም ይወዱ ነበር። ከ61 ዓመት ዕድሜያቸው ውስጥ 50 ዓመት ሙሉ የትም ሲሄዱ ቡችላ በኪሳቸው ይይዙ ነበር።

በሕንድ አገር በአንዳንድ ግዛቶች አንዲት ሴት በታመመች ጊዜ በላይዋ ከወፍራም ጨርቅ አጎበር ይሥራላታል። ከዚያም በኋላ ሐኪም የምጣና ከአጎበሩ ውጪ ሆኖ የበሽተኛይቱን እጅ ይይዛል። በሽተኛይቱ የምትሰጠው መልስና የሐኪሙ ጥያቄ የሚተላለፈው በባልዋ በኩል ነው። ቋንቋዋ ግን አንድ ነው።

በዩጎዝላቪያ ግዛት ሞስታር በተባለ ቀበሌ የሚኖሩ የእስላም ሴቶች በክረምትም ሆነ በበጋ ከቤት ውጪ በሚያዘወትሩበት ጊዜ ግራና ቀኝ ለማየት በማያስችላቸው ጨርቅ ቢጤ ነገር ተሸፋፍነው ነው። ባጭሩ እንደዚህ እንደ ስዕሉ ሆነው ነው።

በሕንድ ፑንጃብ የተባለ አውራጃ መሐራጃ ራንጂት ሲን በ1780 ዓ.ም ተወልደው በ1839 ዓ.ም ሲሞቱ የተገነዙት ከወርቅ በተሠራ ጨረቅ ነው። ከዚህም ሌላ ለድሆች የሚዘከር ተብሎ በግራና በቀኝ ጎናቸው 1.218.750 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ በሁለት ሳጥን ተደርጎ የዘመኑ ገንዘብ ተቀምጦላቸው ነበር።

በጀርሲ ከተማ ጃከ ራስቴይን የተባለ ሰው በ1807 ዓ.ም የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ተሰቀለ እንደተሰቀለ አልሞት ብሎ ስለቆየ እንዲሰቅለው የታዘዘው ወታደር የመስቀያው ገመድ ወንጀለኛውን እንዳያንቀው ብሎ ዘሎ ከተሰቀለው

ሰየ ላይ ተንጠለጠለበት። ቢያወዛውዘውም ቢመነጭቀውም አልሞት አለ። እንዲያውም ከሁለቱ ሰዎች ክብደት የተነሳ የመስቀያው ገመድ ተበጠሰ። ከዚያ በኋላ ወንጀለኛው ምሕረት ተደረገለት።

ሌዲ ኤልጂን ከተባለች መርከብ ላይ ከሚጫወቱ ሙዚቀኞች ጋር ከረቦ መቺው ቻርልስ ሬቨረንግ ነበር። መርከቢቱ መስከረም 8 ቀን 1860 ዓ.ም ሚቺጋን ባሕር ውስጥ ሰጠመች። በመርከቢቱ ውስጥ ከነበሩት 298 ሰዎች 297 ሲሞቱ ቻርስል ብቻ ከረቦውን ታቅፎ እየዋኘ ከዳር ወጣ።

በኢንዶኔዚያ ግዛት የባታክ አውራጃ ገዥ የነበሩት መቃብር ላይ የተሠራው ምስል ያንዲት ልዕልት ምስል ነው ልዕልቲቱ ሟቹን አላገባም ብለው ስለ ነበር ሙቷ ሲሞት ምስሏ በመቃብሩ ላይ እንዲሰራለት ተናዞ ስለ ነእብር የልዕልቷ ምስል ተቀረጸለት።

በሰሜን አፍሪካ ጀርቦአ የሚሉት አውሬ አለ። ይህ አውሬ ራሱ የአይጥ፤ እግሩ የካንጋሮ፤ ጭራው የአንበሳ ነው።

በቻይና አገር በሻንጋይ አውራጃ ፁ ሐን ጂን የሚባል ሰው ነበር ይህ ሰው በመቶ አምሳ ዓይነት ዘዴ ለመጻፍ ይችል ነበር። ለምሳሌ በምላሱ፤ በክርኑ፤ በአፍንጫው፤ በጆሮውና በሌላውም አካሉ የሚነበብ ጽሑፍ መጻፍ ይችል ነበር።

ብሊቭ ኢት ኦር ኖት የተባለ መጽሐፍ ሲያትት እንዲህ ይላል። አልፍሬድ ኢግል እና ሊዮን ቼፍኔ አክስ የተባሉ ሁለት መሐንዲሶች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የባብቡር ሐዲድ ለመዘርጋት ዳግማዊ አፄ ምኒልክን ፈቃድ ጠየቁ። ንጉሠ ነገሥቱም አሳባቸውን ተቀብለው ችሎታቸውን ለመፈተን በአንድ ቤት ውስጥ አስገብተው ደጁን በዘበኛ አስጠበቁና «ጫማ መስፋት መቻላችሁን ሰፍታችሁ አሳዩኝ» አሏቸው። መሐንዲሶቹም የጫማ አሰፋፍ ባለማወቃቸው ለጥናት ብለው ያደረጉዋቸውን ጫማዎች ተልትለው ያን እያዩና በዚያ ዓይነት እየቆረጡ ሲሰፉ አድረው ነበጋታው አስረከቡ።

በፓኪስታን ግዛት ካራቺ አጠገብ የሚኖሩ የሂንዱ ሃይማኖት ቄስ በእጅ ጣቶቻቸውና በክንዳቸው ላይ አምባርና ቀለበት በማሠር እጃቸውን የማይጠቅም በሽተኛ አድርገውታል። ምክንያቱም ሲናገሩ «በእጄ ኃጢአት እንዳልሠራበት ነው» ይሉ ነበር።

በቦርኒዮ ግዛት የፑና ጎሣ ሴቶች አንድ ወንድ ለሚስትነት ካጯቸው በኋላ እጮኛቸው የተያዘ ወንድ መሆኑን ለመንገር ምልክት የሚሆን ንቅሳት ከሽፋሉ አጠገብ ከግንባሩ ላይ ይነቅሱታል።

ቻይናዊው አቶ ቻንግ ስድስት ክንድ ቁመት ስለ ነበረው ከመረኢት ቆሞ ያለ ምንም ችግር ስሙን ከጣሪያ ላይ መጻፍ ይችል ነበር።

እንግሊዛዊቷ እመት ኤሊኖር ፔርኪንስ 64 ዓመታት ሙሉ የኤሊስን ቤተሰብ ገረድ ሆነው አገልግለዋል።

ከዛሬ መቶ ዓመታት በፊት በጀርመን አገር ውሾችን ቁንጫ እንዳይዛቸው ለማባረር እየተባለ ቃጭል በውሾች አንገት ላይ ይታሰር ነበር።

ጄኔራል ከንት ኧርንስት በ1580 ዓ.ም ተወልደው በ1626 ዓ.ም ሞቱ። ጄኔራሉ በዘመናቸው የታወቁ ጀግና ነበሩ። ለሞት በሚያጣጥሩበት ጊዜ ተኝቼ አልሞትም በማለት ሙሉ የጦር ልብሳቸውን ለብሰው በታማኝ ወታደሮቻቸው ተደግፈው እየተንጎራደዱ ሞቱ።

በአፍጋኒስታን መሐከለኛ ሕንድ ድረስ አስተባብረው ይገዙ የነበረው ንጉሥ ሚሒራኩላ ሕይወታቸው ዘነ የሳቁት አንድ ቀን ብቻ ነው። ያሳቃቸውም አንድ ዝሆን ከትልቅ ገደል ላይ ተምዘግዝጎ ሲወድቅ አይተው ነው። ታዲያ መኳንንቶቹ በንጉሡ መሳቅ ተደስተው እንደ ገና እንዲስቁ እያሉ አንድ መቶ ዝሆኖች ከዚያ ገደል ላይ እየተገፈተሩ እንዲወድቁ አድርገዋል።

በቴክሳስ ኦራንጅ በተባለ አምባ ነዋሪ የነበሩት አቶ ብራውን አንገታቸው ላይ የሚያስሩት ከረባት ራሱን የሃያ ብር ኖት (የገንዘብ ወረቀት) ነበር።

የጉይስ መሥፍን ሒንሪ በተወለደ በ15 አመት ዕድሜው የፈረንሳይ አገር ጳጳስ ሆኖ ነበር። ሔንሪ በ1614 ዓ.ም ተወልዶ በ1664 ዓ.ም በአምሳ ዓመት ዕድሜው ሞተ።

በደቡብ አፍሪካ ፒትስበርግ በምትባ ከተማ አንድ ክንድ ቁመት ብቻ የሆነ ቁመት ያላቸው ሰው ነበሩ። እኒህ ሰው ከአሥሩ ሚስቶቻቸው 37 ልጆች አስወልደዋል።

የዌርተምበርግ አልጋ ወራሽ ልዑል ዊልያም፤ ከናፖሊዮን እህቶች አንደኛዋን ልዕልት ቻርል የተባለችዋን አግብቷት ነበር። ጋብቻው የተፈጸመው ሁለቱም በሌሉበት ነው። ስድስት ዓመት ሙሉ በባልና ሚስትነት ሲኖሩ አንዲት እንኳን ዓይን ለዓይን ተያይተው አያውቁም።

በቦርንዮ የያንዴክ ጎሣ ሴቶች ሩዝ የሚቀቅሉት በሸንበቆ ውስጥ እያደረጉ ነው።

ማርያ ጊንኒግ የተባለች በእንግሊዝ አገር በዘመንዋ ብርቅና ድንቅ የነበረች ቆንጆ በ1733 ዓ.ም ተወልዳ በ27 ዓመት ዕድሜዋ በ1760 ዓ.ም ሞተች። ሐኪሞች የሞተችበትን ምክንያት መርምረው ውጤቱን ሲገልጹ «ለውበትዋ መጠበቂያ ብላ ልዩ ልዩ ቅባትና ሌላም መዋቢያ ነገሮችን በብዛት በማድረግዋ የመተንፈሻ ሕዋሳቶችዋ በመደፈናቸው ነው» ብለዋል።

የአሬጎን ሕንዳውያን የቺኖክ ጎሣ ባላባት የሚታወቀውና የሚመረጠው በግንባሩ ደፍጣጣነት ነው። የባላባትነት ዝርያ ያለው ልጅ ሲወለድ ግንባሩ እንዲደፈጠጥ በእንጨቶች መሐል ተጣብቆ ሦስት ወይም ስምንት ሳምንት ድረስ ይቆያል።

በእንግሊዝ አገር ኬንስትስፎርድ በተባለ ቀበሌ ይኖሩ የነበሩ የአቶ ጆን ዊንድሃም ሚስት ሞቱና ተቀበሩ። ለሊት አትናዌል የተባለ ሰው ሴትዮዋ

ከጣታቸው እንዳደረጉት የተቀበረውን ወርቅ ለመውሰድ ሲታገል የሞቱት ሴትዮ ጮኸው አስጣሉት።

የትቤት መነኮሳት ከረቦአቸውን የሚጠፍሩበት በሰው ቆዳ ነው።

የቀጭኔ አንገት አጥንቶች ሰባት ናቸው። የዳክዬ አንገት አጥንቶች ግን 23 ናቸው።

ከ3000 ዓመታት በፊት በግሪክ አገር የአቴንስ መቅደሶች ቁልፍ ረጅምና ከባድ በመሆኑ ቀሳውስቱ መቅደሱን ቆልፈው በሚሄዱበት ጊዜ ቁልፉን በትከሻቸው ላይ ተሸክመው ነበር የሚጓዙት።

በቲቤት ያክ የሚሉት አውሬ አለ። ራሱ የላም፤ ቀንዱ የበሬ፤ ጭራው የፈረስ፤ ኮቴው ደግሞ የአሣማ ነው። ከሁሉ የተውጣጣለት አውሬ ነው።

በቻይና አገር በቼንዩአንቴን አውራጃ ያሉ ሴቶች ከባላቸው ተፋተው እንደገና ሌላ ባል ለማግባት በሚፈልጉበት ጊዜ ጠጉራቸውን የእባብ ቅርጽ አድርገው ይሠሩታል።

እንዲህ የሚያደርጉትም ባል የሚፈልጉ መሆናቸውን ሲገልጹ ነው።

በኢንዶኔዚያ ውስጥ ሱዳን በተባለ አገር አንድ ሰው ሞቶ ወደ ቀብር በሚሄድበት ጊዜ ሬሳው ወንዝ ወይም ባሕር ማቋረጥ ወይም ባሕር ማቋረጥ አለበት። ያ በብዙ ተሸካሚዎችና አጃቢዎች የሚጓዘው ሬሳ ውሀውን ሲሻገር መጥፎ መናፍስት ውሀውን ፈርተው ይቀራሉ የሚል እምነት አላቸው።

በብራዚል ሕንዶች አንድ ሰው ወይም የቤቱ ጌታ በሞተ ጊዜ የሚቀብሩት በቤታቸው ውስጥ ነው። የዚያ ቤት ተረካቢ ወይም ወራሽ አባወራ የሚሆን ሰው የሚተኛው የተንጠለጠለ መኝታ አበጅቶ ልክ በመቃብሩ አቅጣጫ ነው።

ኢጋስቶን ፏኛ በፈረንሳይ አገር ቢየርን የተባለችውን አውራጃ 41 ዓመታት ገዝቷል። ጋስቶን ከመንትያው ወንድሙ ተመርጦ የነገሠው በአስተኛኘቱ ነው። በ1174 ዓ.ም መንትዮቹ ወንድማማቾች በሚያድጉበት ቤት ከሁለቱ አንዱን

ለንጉሥነት የሚመርጡ ሽማግሌዎች ተልከው ገቡ። ጋስቶን እጁን እንደምንም ጥሎት ተኝቷል። ወንድምየው ግን ጨብጦ ተኝቷል። ሽማግሌዎቹ ይህን ስላዩ «ጨባቹ ኃይለኛ ነው፤ ይሄኛው ግን የሰላም ሰው ነው» ብለው ጋስቶንን አነገሡት።

በአፍሪካ ውስጥ ሐንጃ የሚባል ጎሣ አለ የዚህ ጎሣ ሴቶች ያዘሉትን ልጃቸውን ከእንቅልፌ ሳያስነቁ ለብዙ ሰዓት የባህላቸውን ጭፍራ መጨፈር ይችላሉ።

በኔፓል አንዳንድ ጎሣዎች አንዲት ሴት ልጅ ባል ለማግባት መድረስዋን የሚፈትኑት አንድ ሕጻን ልጅ በቅርጫት ውስጥ አድርገው ያሸከሟትና የሒማልያን ተራራ 32 ኪሎ ሜትር ያህል በእግርዋ እንድትወጣ ያድርጉዋታል። መውጣት ካልቻለች ባል ማግባቷ ይቀራል ማለት ነው።

አን ወተር ሐውስ የተባለች ስድስት ዓመት ዕድሜዋ በእንግሊዝ አገር ማክለስ ፊልድ በተማለ አምባ አምስት ብር የሚያወጣ ሐር ሰርቃ በመገኘትዋ በ1818 ዓ.ም በስቅላት ተቀጥታለች።

በኢንዶኔዚያ፤ ጋምቤንግ በተባለ አውራጃ ለለቅሶ ኀዘን የሚገለጽበት እንዲህ እንደስዕሉ በአስደናቂ ሁኔታ ተጣጥፎ በመጨፈር ነው። የእንቁራሪት ጭፍራ ይሉታል።

በእንግሊዝ አገር ግሪንስበርግ ከተማ የአቶ ዎልተር ሬድል ማን በግ በጀርባው ላይ ሣር በቅሎበት ለሕዝብ ታይቷል።

ባዳሆሜ በእባብ የሚያመልኩ ጎሣዎች አሉ። የጎሣው ማንኛይቱም ሴት በማንኛውም ጊዜ እባብ ብታገኙ በአንገትዋ ላይ ጠምጥማ በአቅራቢዋ ወዳለው የእባብ መቅደስ እባቡን ማድረስ አለባት።

የታንጋኒካ ወጣቶች ሲያጌጡ ጠጉራቸውን ልክ እንደሳላ ቀንድ ገትረው ይሠሩታል።

የፈረንሳዩ ንጉሥ ኽንሪ ፫ኛ አንቶኔት ደ ፓንስ የተባለችውን ለማግባት በ1590 ዓ.ም የፍቅር ደብዳቤ ጽፎ ላከላት። ደብዳቤውን የጻፈው የራሱን ደም እንደ ቀለም አድርጎ ነው።

በ1683 ዓ.ም ተወልደው በ1746 ዓ.ም የሞቱት የስፓኙ ንጉሥ ፩ኛ በብርዱ በክረምቱ ወራት ሲተኙ አንዲት ነጠላ ቢጤ ለብሰው ብርድ እንዲገባ መስኮቱ ሁሉ ተከፍቶ ነው። በሞቃቱ በበጋ ወራት ደግሞ መስኮቱ ሁሉ ተዘግቶ 12 ብርድ ልብሶችን ደራርበው ለብሰው ነው።

የአብርሃም ሊንከንና የጆን ኤፍ ኬኔዲ ታሪክ ተመሳሳይ ቢጤ ነው። ሊንከን በ1860 ዓ.ም ለአሜሪካ ፕሬዝዳንትነት ተመረጡ። ከኔዲ ደግሞ በ1960 ለአሜሪካ ፕሬዚደንት ተመረጡ። ሁለቱም የተገደሉት በማጅራታቸው በጥይት እየተመቱ ነው። የሁለቱም ሥልጣን ተረካቢዎች ጆንሰን ይባላሉ። የሊንከን ሥልጣን ተረካቢ አንድሪው ጆንሰን የተወለዱት በ1808 ዓ.ም ነው። የኬኔዲ ሥልጣን ተረካቢ ሊንደን ጆንሰን በ1908 ዓ.ም የተወለዱ ናቸው። የአብርሃም ገዳይ ጆን ዊልኪዝ ቡዝ በ1839 ዓ.ም የተወለደ ነው። የሁለቱም ገዳዮች የተገደሉት ከፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ነው። የሊንከን ልዩ ጸሐፊ ኬኔዲ ይባል ነበር። የኬኔዲ ልዩ ጸሐፊ ደግሞ ሊንከን ይባል ነበር። የሊንከን ልዩ ጸሐፊ ፕሬዚደንቱ ወደ ተገደሉበት ወደ ቴያትር ቤቱ ለንዳይሄዱ ከልክሏቸው ነበር። የኬኔዲ ልዩ ጸሐፊም ፕሬዚደንቱ ወደ ተገደሉበት ወደ ዳላስ እንዳይሄዱ መክሮአቸው ነበር ጆን ዊልኪስ ቡዝ በቴያትር ቤት ውስጥ አብርሃምን ገድሎ ወደ ብረታ ብረት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሆኖ ኬኔዲን ገድሎ ወደ ቴያትር ቤት ሸሸ። ሟቾቹ ፕሬዝዳንቶች ሊነከን አብርሃምና ኬኔዲ የቤተሰብ ስሞቻቸውን በፈረንጅኛ አጻጻፍ ሰባት ሰባት ፊደሎች አሉባቸው። LINCOLN KENNEDY ሥልጣን ተረካቢዎቹ አድረው ጆንሰንና ሊንደን ጆንሰን የስሞቻቸው ፊደላት የያንዳንዳቸው 13 13 ናቸው። ገዳዮቹ

ጆን ዊልኬዝ ቡዝ እና ሊ ሐርቬይ ኦስዋልድ በያንዳንዳቸው 15 አሥራ አስምት ፊደላት አሉባቸው።

በአሜሪካ አገር በብሩክሌይን ገበሬ የሆኑት አቶ ዮሴፍ ፉልኮ ከእርሻቸው እንዲህ እንደስዕሉ የሚመስል ድንች አፍርተዋል።

ሐንስ ሾን የተባለ የታወቀ የጀርመን ግጥም ደራሲ በ1824 ዓ.ም መጋቢት 1 ቀን ሲሞት በኑዛዜው መሠረት ዛፍ ተፈፍልሎ ሬሳው ከዛፉ ውስጥ ተደረገ። ከጊዜ በኋላ ግን የመቃብር አፉን ገጥሞ በሬሳው ላይ ደፍኖ እስከ ዛሬ አለ።

የፍጋኒስታን ንጉሥ የነበሩት አልዝኒ (970 – 1030) የማዕረግ ወይም ቅጽል ስማቸው ቫሊ እንዲባል ከሊፍ ካደን ቢላህ የተባሉት ከሊፋ የተባሉት ከሊፋ አዘዙ። ቫሊ ማለት ጌታ ወይም አሽከር ማለት ነው። ለሁለቱም ይሆናል። ንጉሡ ይህን ስም በመጥላት ቫሊ የተባለው ስም አንድ አ ተጨምሮበት ቫአሊ ተብሎ እንዲለወጥ አደረጉ።

ሐርሐራ በሕንድ አገር የቪጃንጋርድ ንጉሥ ነበሩ። ዳግማዊ ሐሪሐራ አሥራ ሁለት ሺ ሚስቶች ነበሩዋቸው። ሁሉም ከሕንድ ቆነጃጅት የተመረጡ ውቦች ነበሩ። ዳግማዊ ሐሪሐራ ሀብታም ንጉሥ ነበሩ። አንድ ሺ ዝሆኖች ከአርባ ሺ ፈረሶች ጋር ነበሩዋቸው። የዕለት ገቢያቸውም በዛሬው የኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር አንድ ሚሊዮን ብር ነበር። ሐሪሐራ በ12.000 ሚስቶቻቸው ላይ ፓርታል የምትባል ልጅ ፍቅር ያዛቸው። ፓርታል በጎረቤት መንግሥት አገር ሙድኩል በተባለች ከተማ የምትኖር ናት። ሐሪሐራ ልጅቱን በግዴታ ለማግባት ብለው ከጎረቤታቸው አገር ንጉሥ ፌሮዝ ሻህ ቱግላግ ጋር ጦርነት ገጠሙ። በዚህም ጦርነት ሐሪሐራ ድል ሆኑና በጦርነቱ ላይ ሞቱ። ሐሪሐራ ፓርታልን ቢያገቡ ኖሮ የሚስቶቻቸው ቁጥር 12.001 ይሆን ነበር።

ጀርመናዊው ቶማስ ሻዊከር በ1540 ዓ.ም ሽዋቢሽ በተባለ ቀበሌ ሲወልድ ሁለቱም እጆቹ ፈጽሞ አልተፈጠሩም ነበር። የእጆቹ ብቻ ሳይሆን ወገቡ ትብጦ ከጭኖቹ ጋር አብሮ የተያያዘ በመሆኑ ቶማስ እንደ ሰው

ለመቆምም ሆነ ለመቀመጥ አይችልም ነበር። ቶማስ በእግሩ ጽሕፈት መጻፍ ለምዶ በብዕር ያልጣሉ በዘመኑ ተወዳዳሪ ያልተገኘለትና በዓለም የተደነቀ ጸሐፊ ነበር። ቶማስ በ1602 ዓ.ም ሞተ።

በቤልጂንግ አገር ላይከን በተባለ ከተማ ባለው የልዑላን መናፈሻ ውስጥ ሁለት ዛፎች ከበቀሉ በኋላ የዛፎቹ መጋጠም በትክክል የቤልጂግ ንግሥት ሉይስን ምሥል አወጡ። ምሥሉ የወጣውና የታወቀው ንግሥቲቱ ከሞቱ በኋላ በ1849 ዓ.ም ነው።

በእንግሊዝ አገር እስከዛሬ ድረስ ጠንቋዮች የሚሠሩባቸው ጠጠር መሣይ ነገሮች አሉ። በጠጠሩ ላይ የሚሠራው ሽልምልም በአይጥ በርግብና በዳጉንቸር ደም ነው።

በሕንድ አገር ቲልቫክራንት የሚባለው የሃይማኖት በዓል አለ። በዓሉ የሚውለው እንደእኛ ዘመን አቆጣጠር የታኅሣሥ ፪ ፫ እና ፬ ቀን ለሦስት ቀናት ነው። በነዚህ ሦስት ቀናት አምስት ምዕመናን ሶናር በተባለ ወንዝ ውስጥ ይታጠባሉ። ወንዙ የሚገኘው በደቡብ ሕንድ ሐታ ከተባለ ከተማ አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ነው። እያንዳንዱ ምዕመን ምግቡን ይዞ ከውሀው ውስጥ ይገባና ከዚያው ከውሀው ውስጥ (ሥር) ሆነው የያዙትን ምግብ ይበላሉ።

ወይዘሮ ዶሮቲ ፎርድ ባል ሊያገቡ ከቄስ ዊልያም ስትሪት ጋር ተስማሙ። በእንግሊዝ አገር በሳውት ፖል ቀበሌ ነዋሪ የነበሩት ዶሮቲና ዊልያም ሞቱ። ሚቹም ቄስ ዊልያም ለዘመድ አዝማድ በሕልም እየታዩ የእጮኛቸውን ጉዳይ እያነሱ ስላስቸገሩ ካልተጋቡ የሟቹ መንፈስ አያርፍም ተባለና የቄስ ዊልያም ሬሣ ከነ ሣጥኑ ከተቀበረበት ወጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተወሰደ። በቤተ ክርስቲያኑም ቆመው ከቄሱ ፊት በመሐላ ጋብቻውን ኅዳር 27 ቀን 1667 ዓ.ም ፈጸሙ። ከዚያም በኋላ ሙሽራይቱና ሬሳው ሙሽራ ታጅበው ወደ ቤት ሂዱ። ሬሳው በሣጥን ውስጥ እንዳለ ለዘጠኝ ወር ያህል በቤት ከተቀመጠ በኋላ 1668 ዓ.ም ነሐሴ 31 ቀን እንደ ገና ተቀበረ። ዶሮቲም ከጋብቻው ነፃ ሆኑ።

በሰሜን አውስትራሊያ አንድ ሐይቅ አለ። የዚያ ሐይቅ ስም ካርዲቪሊዋራኩራኩሬኤፖርላዱ ይባላል።

በመካከለኛው ሕንድ ብሂል የተባለ ጎሣ አለ የዚያ ጎሣ ሰዎች በባል እና በሚስትነት ሲኖሩ የሚሳሳሙት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። በመሳሳሚያቸው ቀን ባልዮው በአፉ ቅጠል ይዞ ወደ ሚስቱ ይጠጋል። ሚስቲቱ የቅጠሉን አንደኛውን ጫፍ በከንፈርዋ አጣብቃ ትይዛለች። ከዚያ በኋላ ባልዮው በአፉ የያዘውን እስቲገጥም ድረስ ይጠጋል፡ ከዚህ ቀን በቀር በጋብቻ ዘመናቸው መሳሳም የለም።

በዋሽንግተን ነዋሪ የነበረው አቶ ከርትዝ ፔተርስ የአየሩ ሁኔታ ከዜሮ በታች በሆነ ቅዝቃዜ ውስጥ የብርድ መከላከያ ለብሶ የእጅ ሹራብ አድርጎ፤ ዓይኑን ጨፍኖ በአንድ ደቂቃ 184 ቃላት በታይፕ ጽፏል።

አብዱል ሐሰን አለ በ16 ዓመት ዕድሜቸው በ1021 ዓ.ም የግብጽ ከሊፋ ሆኑ። በካይሮ የሚገኙ ቆነጃጅት ለግብዣ እንዲጠሩ አድርገው ተጠሪዎቹ ምርጥና ድንቅ የሆነ ልብሳቸውን እየለበሱ ወደ ከሊፋው ግብዣ ሄዱ። ከሊፋው ግብዣውን ካዘጋጁበት መስጊድ ደጃፍ ሲቆሙ እያንዳንዷን ሴት በፈገግታና በደስታ እየተቀበሉ ቆዩ። 2660 ሴቶች በአዳራሹ ገብተው አድራሹ ሲሞላ የአዳራሹ በሮችና መስኮቶች በሙሉ እንዲዘጉ አዘዙና ተጉ። ወዲያው የተዘጉት በርና መስኮቶች በግንብ እንዲደፈኑ አዘው ገንቢዎች በሚያቸኩል ገንብተው ጨረሱ። ይህ ሲደረግ በአዳራሹ ውስጥ ያሉ ሴቶች ጩኸትና ልቅሶ የካይሮን ከተማ ረብሿት ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአዳራሹ ውስጥ ጩኸት ጸጥ አለ። አዳራሹ በታሸገ በስድስት ወሩ እንዲከፈት ከሊፋው አዘዙ። አዳራሹ ተከፍቶ የ2660 ሴቶች አጽም ተጠርጎ ወጣ።

በሆላንድ ውስጥ ጎይስ በተባለ ቀበሌ አቶ ጃኩቡስ ቫን ቤይሬንድ ዛፍ ተከለ። ዛፉ ካደገ በኋላ ቅርንጫፉ ጫፍ ላይ የተካዩን የአቶ ካኩቡስን መልክ የመሰለ ቅርጽ አወጣ።

የኮርሲካ ደሴት በኢጣልያ አገር በጄኖአ አውራጃ ትገዛ በነበረበት ዘመን የደሴቲቱ ግብር አስከፋይ ዳኮርቴ የተባለ ሰው ካርይዶኔ የተባለውን ገበሬ ግብር እንዲከፍል ጠየቀ። ገበሬው ከግብሩ ገንዘብ አንዲት ተሙን ጎደለችበት። ግብር አስገቢው ገበሬውን አሠረው። የደሴቲቱ ሰዎች ለገበሬው አግዘው ገበሬው እንዲፈታ የጄኖአን መንግሥት ጠየቁ መንግሥቱ አይፈታም ስላለ ጦርነት ገጥመው ስከ1725 ዓ፣ም እስከ 1769 ዓ.ም ድረስ አርባ አራት ዓመታት ሙሉ ያለማቋረጥ ተዋጉ። በዚህ ጦርነትም 80.000 ሰዎች ሞቱ። በጦርነቱም ስፔይን ጀርመን፤ ቡልጋሪያና ፈረንሳይ ገብተውበት ከተዋጉ በኋላ ደሴቲቱን ፈረንሳይ በኃይል ስለወሰዳት ጦርነቱ ሊቆም ቻለ።

በኢንዶ ቻይና ለአማልክት መቅደስ መብራት እንዲሆን ከሰም የሚሠራው ጧፍ እንደዚያ ማዶው ስዕል እየተጠማዘዘ ነው።

ቶማስ ማይስቸበርገር የተባለ የታወቀ አውስትራሊያዊው ተራራ ወጪ 17.771 ጫማ ከፍታ ያለውን ምንትብላንክን፤ 15.216 ጫማ ከፍታ ያለውን ሞንቴሮዛን፤ 14.780 ጫማ ከፍታ ያለውን ማተርሆርንን 13.645 ጫማ ከፍታ ያለውን ጆንግፋራኡን 13.080 ጫማ ከፍታ ያለውን ማይጂ የተባሉትን ተራራዎች በመውጣት የተደነቀ ሰው ነበር። በይበልጥ በጣም የሚደነቅበት እነኚህን ሁሉ ተራራዎች በጣም የሚደነቅበት እነኚህን ተራራዎች የወጣው ከእንጨት በተሠራ እግሩ ነበር።

ለንደን ከተማ ባእልው ኒውጌት በተባለው ወህኒ ቤት ውስጥ ወንጀለኛይቱ ሜሪ ግሪን በ1819 ዓ.ም መጋቢት 22 ቀን በተፈረደባት መሠረት ተሰቀለች። ማታ ሬሳዋ ለዘመዶችዋ ተሰጠ። ዘመዶችዋ ሬሳውን ከቤት ሲወስዱ ከተሰቀለችበት ገመድ በወረደች በሃያ ደቂቃ ውስጥ ሟችቷ ነቃች። ዘመዶችዋ ሸሽገው እንዳትታወቅ ስምዋን ለውጠው 15 ዓመት ከቆየች በኋላ እንደ ገና ሞታ ተቀበረች።

በኢጣልያ አገር አስኮሊ ያለው የቅዱስ አሚድዮ ቤተ ክርስቲያን በሚያማምሩ ጌጦች እየተቀረጸ ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ነው።

በአሜሪካ አገር በፍሎሪዳ አውራጃ ላርጎ በተባለ ቀበሌ ዶክተር ጂ አ. ማክ ኪ የተባሉ ሰው ከቀፎ ማር ሲቆርጡ በቀፎው ውስጥ ንቦቹ የሠሩት ፫ ትልልቅ የማር መስቀል ተገኝቷል።

በሕንድ አገር ታሪክ ውስጥ ዝነኛ የሆነው ዘፋኝ ታንክሴን ከታላቁ ንጉሠ ነገሥት አክባሬ ፊት አንዲት ዘፈን ዘፍኖ ስምንት ሚሊዮን 112.500 በዛሬው የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ የሚመነዘር ገንዘብ ተከፍሎታል።

በእንግሊዝ አገር በብሪጅኖርዝ አንድ ካቴድራል በ1651 ዓ.ም በነፋስን አደጋ ከፍተኛ አደጋ ደርሶበት ተሰባብሮ ተወለጋገደ። ይወድቃል ተብሎ ሲጠበቅ 305 ዓመት ሙሉ እንደተሰባበረና እንደተወላገደ ቆይቷል።

በብራዚል ያሉ ጓጉንቸሮች ከዓይናቸው አጠገብ ሁለት ቀንዶች አሉዋቸው። ሲጮሁ ደግሞ ልክ እንደ ውሻ ነው ኃይለኞች ከመሆናቸውም የተነሣ ነክሰው ፈረስ መግደል ይችላሉ።

የጥንት ሮማውያን ባንዲት በየአር ላይ በተዘረጋች ገመድ ዝሆን እንዲሄድባት እያደረጉ አሠልጥነው ለትርኢት ያቀርቡ ነበር።

በአፍሪካ ውስጥ ዮርባ የተባለ ጎሣ አለ። የጎሣው ሴቶች እየኮሩ መናገር አይፈልጉም ድንገት እንዳይናገሩም በጥርሳቸው ሚስማር ይይዛሉ።

በፈረንሣይ አገር ቻርትሬስ በተባለ ቀበሌ አንድ ከስብርባሪ ስሃን የተሠራ ቤት አለ። ቤቱ የተሠራው ሬይሞን አሲዶሬ በተባለ ሰው ነው። ቤቱ ብቻ ሳይሆን የቤቱ ውስጥ ዕቃ ሁሉ የተሠራው በስብርባሪ ስሃኖች ነው። ሬይሞንድ ይህን ቤት ለመሥራት የፈጀበት ጊዜ ሃያ ሦስት ሺ ሰዓት ነው። ለቤቱና ለዕቃው የሰበሰበቸው ስብርባሪ ሰሃኖች ደግሞ አንድ ሚሊዮን ናቸው።

የቤትን አሠራር ነገር ካነሳን ዘንዳ የካንዳው አናጢ አቶ ጆርጅ የእንጨት ቤት ከመሥራት ብሎ የጠርሙስ ቤት ሠርቷል። ዱንካን አጠገብ ባንኮቨር በተባለ ደሴት የሚኖረው አቶ ጆርጅ ከቤቱ ጓሮ የሚጣለው ጠርሙስ እየበዛ ስላስቸገረው ግንብ ልገንባው ብሎ እየሰበሰበ ገነባው። ከዚያ በኋላ የሚጣለው ጠርሙስ አልበቃ ስላለው በየመጠጥ ፋብሪካና በየጎረቤቶቹ ዘንድ እየዞረ ጠርሙስ በመለመን የሚኖርበትን የራሱን ቤት ጠርሙስ በመደርደር ብቻ ሠራው። ለዚህም ለቤቱ ሥራ የፈጀበት ጠርሙስ ብዛት አንድ መቶ ሰማንያ ሺ ነው። ቤቱንም የሠራው ልክ እንደ ጥንታዊ ቤተ መንግሥት አስመስሎ ነው። የአበባ መትከውያውን ሁሉ የሠራው በሰበሰበው ጠርሙስ ነው።

በኢጣልያ አገር በአኩዮላ፤ ጴጥሮስ የተባለ ሰው የቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠራ። በዘወትር ጸሎቱ «ይቺን ቤተ ክርስቲያን በጳጳስ ለመጎብኘት አብቃት» ይል ነበር። በኋላ የጸሎቱ መልስ ተገኘ። በ1294 ዓ.ም ራሱ ጴጥሮስ አቡነ ስለስታይን ፭ኛ ተብሎ ጵጵስና ተሾመና በሠራት ቤተ ክርስቲያን ቀደሰባት።

ይህ ልጅ በተወለደ በአሥራ ሰባት ወሩ በፒፓ ትንባሆ ያጨስ ነበር። ልጅ የተወለደውና የሚኖረውም በእንግሊዝ አገር ኖርማንባይ በተባለ ቦታ ነው።

በ1960 ዓ.ም በማኒላ ከተማ ሁለት ራስ ያለው አንድ ወንድ ልጅ ተወልዶ ነበር።

በኢጣልያ አገር ሮጅዮኢሜል በተባለ ቀበሌ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አለ። የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ የተጀመረው በ1536 ዓ.ም ነው። ቤተ ክርስቲያኑን ሥራ የጀመረው ሚኬል ዲሬቺ ሥራውን ካጋመሰ በኋላ በወር የሚከፈለው ደሞዝ አንድ የወርቅ ቤሳ በዛሬው በኛ ብር ሂሳብ ሁለት ብር ከአምሳ ሳንቲም በመሆኑ ደሞዜን ካልጨመራችሁ አልሠራም በማለቱ ታሠረ። በእሥር ቤት እንዳለም ሞተ። ያን ጅምር ቤተ ክርስቲያን የሚጨርሰው ጠፍቶ እስከ ዛሬ ማለት 460 ዓመት ሙሉ በግማሽ ሥራው እንደሆነ ይቀደስበታል።

በቻይና አገር በስዝቹኢን አውራጃ ቸንግ ኪንግ በተባለ ከተማ አንድ ራሰ ቀዳዳ ሰው ነበር። ይህ ሰው በራሱ ቀዳዳ ውስጥ በእሳት የተለኮሰ ሻማ ያኖርና ማታ ማታ በመንገድ ላይ በመዘዋወር ለመንገደኞች ያበራል። ራሱ ላይ ወደ ውስጥ የተሠረጎደው ቀዳዳ እንዴት እንደጎደጎደ አልታወቀም። በቻይና የአሜሪካ ቆንሲል የነበሩት ሮበርት ስሚዝ፤ የአሜሪካ ባሕር ኃይል ሌተና ኮማንደር ዋርድ ዳቪስ እና የአሜሪካ የባሕር ኃይል ዶክተር ካቬኔይ የሰውየውን የራስ ቀዳዳ መርምረውታል። ዶክተሩ ካቬኔይ በሰጡት መግለጫ «.....የራሱ ስርጉድ በኦፕራሲዮን የተጠገነ ይመስላል።......» ብለዋል። የአቀዳደዱ እርግጠኛ ታሪክ ግን አልታወቀም።

በስፔይን የኮርዶባ ተወላጅ የሆኑት አቶ ሣላሚ አብደል መሊክ በ1050 ዓይነት መጽሐፍት ጽፈዋል።

በእንግሊዝ አገር በኦክስፎርድ ውስጥ ባለው የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን አንድ ደወል አለ ደወሉ 8800 ኪሎ ያህል ይመዝናል ይህ ደወል ከ1284 ዓ.ም ጀምሮ በየዕለቱ ማታ ማታ 101 ጊዜ ይደወላል። በመጀመሪያ ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ሲከፈት ለመጀመሪያ ጊዜ ትምህርት የጀመሩት 101 ተማሪዎች በመሆናቸው ለመታሰቢያ ተብሎ ነው።

በዌስት ኢንግላንድ ይኖሩ የነበሩት እንግሊዛዊቷ ወይዘሮ ሄስተር ቴምፕል 5 ወንዶች እና 10 ሴቶች ልጆች ወልደዋል። እኚህ ወይዘሮ በ1656 ዓ.ም በ87 ዓመታቸው ሲሞቱ ከመሞታቸው 2 ዓመት ቀደም ብሎ 700ኛውን የልጅ ልጃቸውን የጆን ኔልሰንን መወለድ አይተዋል።

የታወቁት ግጥም ገጣሚ ኢጣልያዊው ፍሬንቼስኮ ማሪያ ግራፖልዶ ባንድ ጊዜ በሁለት ቋንቋ፤ በሁለት እጆቻቸው እየጻፉ ሁለት ዓይነት ግጥም መግጠም ይችሉ ነበር።

በቱክሳስ ነዋሪ የነበሩት ኮሎኔል ዊልሰን በ94 ዓመት ዕድሜያቸው የልጅነት ጊዜ ጥርሳቸው እንዳለ ነበር። ዊልሰን ዕድሜያቸውን ሙሉ ጥርሳቸውን ፍቀውት ወይም ታክመውት አያውቁም።

በእንግሊዝ አገር የታወቀው ተጫዋች (ኮሜዲያን) ጆን ሊስተን በ1807 ዓ.ም እሑድ መጋቢት 22 ቀን ማርቲን ቤተ ክርስቲያን የአይሪሽዋን ዘፋኝ ወይዘሪት ቲረርን ሲያገባ ልክ አራት ሰዓት ተኩል ሲሆን «በዚች ቀንና ሰዓት ብሞት ታላቅ ደስታዬ ነበር» ብሎ ተናገረ። 39 ዓመት ከሚስቱ ጋር ከኖረ በኋላ በ1846 ዓ.ም መጋቢት 22 ቀን እሑድ ዕለት ልክ አራት ሰዓት ተኩል ሲሆን ሞተ። የተናገረው ቃል ሞላለት።

በ1880 ዓ.ም በአሜሪካ አገር በኦሀዮ ይኖሩ የነበሩት ወይዘሮ ፋኒ ሚልስ እግራቸው (ጫማቸው) 36 ኢንች ርዝማኔ ነበረው። ይህም ማለት አንዱ ጫማቸው (መርገጫ እግራቸው) ብቻ የሁለት የጤናማ ሰው እግሮች ተቀጣጥለው ያህል ነበር ማለት ነው።

በኒውዮርክ ከተማ ኬኔት ፓትስ የተባለ ልጅ ክርስትና ሲነሳ የላከ ሰው ልብስ ከ67 ዓመት በፊት ቅድመ አያቱ ክርስትና ሲነሱ ለብሰው የነበረው ልብስ ለብሶ ነው።

በኒው ዮርክ ከተማ የሚኖሩት የአቶ ፍራንክ ጂ ሉቢ ፊርማ እንዲያ እንደስዕሉ ነበር።

በፈረንሳይ አገር በ1719 ዓ.ም ሉዊስ ካርዲያክ የተባለ ልጅ ተወለደ። ልጁ በተወለደ በሦስት ወሩ ፊደላትን ለይቶ ማንበብ ቻለ። በሦስት ዓመት ዕድሜው የላቲን ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ቻለ። በአራት ዓመት ዕድሜው እንግሊዝኛ፤ ጀርመንኛና እብራይስጥ አወቀ። በስድስት ዓመት ዕድሜው በሂሳብ፤ በታሪክና በጂኦግራፊ ሊቅነት ተመረቀ። በሰባት ዓመት ዕድሜው በ1726 ዓ.ም ሞተ።

ቪኩና የተባለች አውሬ አለች። በአግድሞሽ ዝላይ ሃያ ጫማ ርቀት ድረስ ትዘላለች። በዚህ በዝለላ ተወዳዳሪ የሌላት ናት። ግን በመንገድዋ ላይ የወደቀ ወይም የተጋደመ ገመድ ካገኘች ፈጽማ ተራምዳው አታልፍም።

የሞሮኮ ሡልጣን የነበሩት ሡልጣን አብዱል ሐሰን በ1291 ዓ.ም ተወልደው በ60 ዓመታቸው በ1351 ዓ.ም ሲሞቱ 1862 ልጆች ነበሩዋቸው።

በደቡብ ጆርጂያ ሁለት ራስ ያለው አሣነባሪ ተጠምዶ ተይዟል።

1.639.262.295.081.967.213.114.754.098.360.655.747.704.918.032.787 እነኚህን ሁሉ ቁጥሮች በ71 ለማባዛት ከባድ ሥራ ነው። አጭሩ መንገድ ከመነሻው ላይ 1 ቁጥር ጨምሮ መጨረሻው ላይ 7 መጨመር ነው።

በደቡብ አሜሪካ ኳስኳሬ የሚባል ወንዝ አለ። የወንዙ ውሀ የሚፈሰው ወደ ሁለት አቅጣጫ ነው። የወንዙ ውሀ ወደ አርኒኮ ሲፈስ ይቆይና በአርኒኮ ዝናብ ሲዘንብ ውሀው ተመልሶ በዚያው በሄደበት ወንዝ አማዞን ይወርዳል። በአማዞን ዝናብ ሲጥል ደግሞ እንደ ገና የወንዙ ውሀ ወደ አርኒኮ ይመለሳል። የወንዙ ውሀ የሚወርድበት አንድ አቅጣጫ የለውም።

በዓለም የታወቀው ታላቁ ስዕል ላይ ዚአክሲስ የሳለውን ስዕል እያየ ሲስቅ በዚያው ሞተ።

# ትልቅ እንቁላል የሚወልድ አሣነባሪ ብቻ ነው።

በቦሄሚያ ግዛት ዎታዋ በተባለ ቀበሌ በያመቱ በአካል ላይ መርፌ ሰክቶ የመቆየት ውድድር ይደረጋል በ1928 ዓ.ም በተደረገው ውድድር ባግሮ የተባሉ የነገዱ ባላባት (ንጉሥ) 3200 መርፌዎች ሰክተው 31 ሰዓት ሙሉ በመቆየት አሸናፊ ሆነዋል።

በኒውዮርክ ከተማ ጆፍሪ ሮሰንበርግ የተባሉ ሰው ፋዚ የተባለች ድመታቸው በዕድሜዋ 150 ግልገሎች ወልዳለች።

በኮሪያ በወንጭፍ እንቁላል ይገዛል።

ጂኦቶ ዲ ቦንዶኔ የተባሉ የ14ኛው መቶ ታላቁ ስዕል ላይ እጃቸውን ምንም ነገር ሳያስደግፉ ባንድ ጊዜ ማዞር የማይዛነፍ ትክክለኛ ዙርያ ክብ መስመር መሥራት ይችሉ ነበር። ቦንዶኔ ኢጣሊያዊ ናቸው።

በቻይና አገር ባካንቶን ከተማ ቁንጫ የሚይዙ ውሾች ውድድር ተደርጎ ነበር። ቺንግ የተባለ ውሻ በአራት ሰዓት ውስጥ 21.000 ቁንጫዎች ይዞ አሸናፊ ሆንዋል።

በኢንዲያና ፖሊስ እውሮች መኪና እንዲነዱ ይፈቀድላቸው ነበር። በመኪናው ላይ ግን «ይህን ካሚዮን የሚነዳው እውር ሰው ነው» የሚል ጽሑፍ ይጻፍበታል።

የታወቀውና ዝነኛው የሁንጋሪያ ቫይለኒስት ወይም ማሲንቆ መቾ አርባ ስምንት ወንዶች ልጆች ነበሩት። አርባ ስምንቱም ልጆቹ የታወቁ ቫይለን ተጨዋቾች ሆነዋል።

ቻንግ ቷንግ የተባለ የቻይና መነኩሴ ዕድሜያቸውን ሙሉ ፑቱሻን በተባለ መቅደስ ሲያገለግል ኖርረ። የመሞታቸው ጊዜ ሲደርስ «.....በሬሳዬ ላይ የማያፈረስ መድኃኒት (መሚ) አድርጋችሁ በእጄ መቅረዝ አሲዛችሁ በመቅረዙ ላይ ሻማ እያበራችሁ በገለገልኩበት መቅደስ ውስጥ አቁሙኝ» ብሎ ተናዞ በመሞቱ 1690 ዓ.ም ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በዚያች መቅደሱ ውስጥ የቻንግ ሬሳ መብራት እያበራ ቆምዋል። ሻማው ባለቀ ቁጥር ይለወጣል። በዓለም ያለው የሬሳ መብራት አብሪ ቻንግ ብቻ ነው።

በአሜሪካ አገር በኦሀዮ ከተማ በፖርትክሊንተን ቀበሌ አንድ ልጅ ተወለደ። ልጁ እንደተወለደ በደረቱ ላይ ROY የሚል ጽሑፍ ስለተገኘ ስሙ ሮይ ተባለ።

በዓለም ካሉት አበባዎች ሁሉ ትልቁ የሚገኘው በሱማትራ ግዛት ነው። የአበባው ዙርያ ክብ ሰባት ጫማ ተኩል ሲሆን ክብደቱ 7 ኪሎ ነው።

# የሞተ ሰው እንደገና ይወለዳል?

በ1926 ዓ.ም በሕንድ አገር በደልሂ ከተማ አንዷት ልጅ ተወለደችና ስምዋ ሻንቲ ዳቪ ተባለ። ሻንቲ በተወለደች በ3 ዓመትዋ ስለ ባልዋና ስለ ልጆችዋ ማውራት ጀመረች። ይህ ነገር እየተደጋገመ በመሄዱ እናትዮዋ ተቸግራ አንድ ቀን «የምን የባልና ነገር ነው የምታወሪው? » አለቻት።

ሻንቲ አንገትዋን ደፋ አደረገችና «ባሌ ኬዳርናት ይባላል፤ እኔና ባለ የምኖረው ሙታ በሚባል አገር ነበር። አንዱ ወንዱ ልጄም ዛሬ የሚኖረው ከአባቱ ጋር ነው። እኔም የሞትኩት እሱን ስወልድ ነው» አለቻትና የቤትዋን ሁኔታና ሥርዓት ምንጣፉ ሁሉ ሳይቀር ዘርዝራ ነገረቻት።

ሻንቲ እብድ ነች ተባለችና ከሐኪም ዘንድ ተወሰደች። ከሐኪሙም ዘንድ ሂዳ ብትጠየቅ ለእናትዋ ያወራቻቸውንና ሌላ ጨምራ ለሐኪሙ ነገረችው። በተለይ ሐኪሙን ያስደነገጠው «እኔኮ በ1925 ዓ.ም በወሊድ ምክንያት የሞትኩት ሉዝር ነኝ» ብላ ነገረችው። በደልሂ ከተማ ከመወለድዋ አንድ ዓመት በፊት ማለት ነው።

ሕመምዋም ሆነ ምንዋ ሳይታወቅ የሻንቲ ዕድሜ ሰባት ዓመት ሞላ። ብዙ ሐኪሞች እየተሰበሰቡ ይሄን እንቆቅልሽ ለመፍታት ሞከሩ። አልቻሉም። በስምንተኛው ዓመቷ አጎትዋ ፕሮፌሰር ኪሼን ቻድ ጉዳዩን ለማጥናት ወሰነ።

ፕሮፌሰር ኬሼን ልጅቷ በነገረችው አድራሻ መሠረት ደብዳቤ ጽፎ ልጅቷ ባሌ ለምትለው ሰው ወደ ሙትራ ከተማ ደብዳቤ በፖስታ ቤት ላከ። ደብዳቤው ላይ በ1925 ዓ.ም በወሊድ የሞተች ሉዝር የምትባል ሚስት ነበረችህ ወይ? የሚል ጥያቄ ላከ። የሉዝር ባል የነበረው አቶ ኬዳርናት ወደ ፕሮፌሰሩ በላከው ደብዳቤ ሴቲቱ የመጀመሪያ ሚስቱ እንደነበረች እና እስዋ ከሞተች እስካሁን ሌላ ያለማግባቱን ገልጾ ጻፈ።

ከዚህ በኋላ ፕሮፌሰሩ የሻንቲን አባትና ቤተሰቦች ሰብስቦ በጉዳዩ ተወያየ። ከሙትራ ከተማም ከአቶ ኬዳርናት ቤት አንድ ሰው እንዲመጣና በጉዳዩ እንዲወያዩ ተላላከ።

የሻንቲ ዕድሜ ዘጠኝ ዓመት ሞላ። አንድ ቀን ከእናትዋ ጋር በወጥ ቤት ስትሠራ የውጪው በር ተንኳኳ። ሻንቲ በሩን ልትከፍት ሮጣ ሄደች። ሳትመለስ ብትቆይ እናትዋ ወደ ውጪው በር ብትሄድ ሻንቲ ካንድ የማይታወቅ ሰው ጋር ስትነጋገር አየቻት። ወዲያው ሻንቲ ወደ እናትዋ ዞር ብላ «እማዬ! የድሮው ባለቤቴ ለዚህ ሰው አጎቱ ነው። የሚኖረውም በሙትራ ከተማ ነው። ቤቱ እኛ ከምንኖርበት ቤት ብዙም አይርቅ» አለቻት።

እንግዳው ከቤት እንዲገባ ተደረገ። ጥቂት እንደቆየ የሻንቲ አባት ከውጪ መጣ። ከእንግዳው ሰውዬ ጋር ተገናኙና ወሬ ጀመሩ። እንግዳው ሰውዬ ለሻንቲ

አባት ሲያወራ ልጅቱን ፈጽሞ እንደማያውቃት ገልጾ የምትናገረው ግን ሁሉም እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ተናገረ።

ከዚህ በኋላ የሻንቲ አጎት ፕሮፌሰር ኪሼን ቻንድ በምክሩ ተጨምሮ ልጅቷ ሳታውቅ አቶ ኪዳርናት ተጋብዞ ከነልጁ ወደ ደልሒ እንዲመጣ፤ መጓጓዣውን ሁሉ እንደሚከፍሉለት ስምምነት ተደረገ። ከጥቂት ቀናት በኋላ አቶ ኬዳርናት ወደ ደልሒ መጣ። ሻንቲ ካለችበትም ቤት ደረሰ። ሻንቲ አቶ ኬዳር ናትን ገና ስታየው ጮኸች። ከደስታ ብዛት የተነሳም አለቀሰች። ካቶ ኬዳርናት ጋር ወደ መጣውም ልጅ ዘንድ ሮጣ ሄዳ ባንገቱ ላይ ተጠመጠመች። ታቅፋ ልታነሳውም ሞከረች፤ ግን ያል ልጅ ባንድ ዓመት ዕድሜው ስለሚበልጣት ልታነሳው አልቻለችም። በወሊድ የሞተችበት ልጅዋ መሆኑንም ተናገረች። ወሬውም በሕንድ ጋዜጦች ላይ ዋለ።

የመላው የሕንድ ጋዜጦት አሳታሚዎች ማኅበር ፕሬዚዳንትና የሕንድ ፓርላማ አባል የሆኑት አቶ ዴሽ ባድኑ ጉፕታ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሆነው ጉዳዩን በጥንቃቄ ለማጥናት ወሰኑ። በራሳቸው አላፊነትም ልጅቱ እኖርበት ነበር ወዳለችው ወደ ሙትራ ከተማ እድትወሰድ ወሰኑ። ከልጅቷም ጋር የሻንቲ ወላጆች፤ አቶ ጉፕታ አቶ ታራ ማቱራ የሚባል ጠበቃና የታወቁ ሰዎች አብረው እንዲሄዱ ተደረገ።

ጉዞው በባቡር ቀጠለ። ከሙትራ ከተማ ሲደርሱ ከባቡር ወርደው በሁለት ሰረገላ ሆነው ወደ ከተማው መሐል ተጓዙ። ሻንቲ ያለችበት ሰረገላ ከፊት ቀደመ። ሠረገላ ነጂው ሻንቲ እንዳሳየችው ወይም እንዳዘዘችውና በምታሳየው መንገድ እንዲነዳ ተደረገ። በቀጥታ መንገዱን እየመራች ከመሞትዋ በፊት ከምትኖርበት ሠፈር አደረሰችው።

ከቤቱ አጠገብ ሲደርሱ ሻንቲ «ይሄውና ቤታችን» ብላ ጮኸች። «ግን እኔ የነበርኩ ጊዜ ቀለሙ ቢጫ ነበር። አሁን ነጭ ቀብተውታል» አለች። በዚያ ሻንቲ በተናገረችው ቤት ያሉት ሰዎች ሻንቲንና አጃቢዎችዋን ከቤት እንዳይገቡ ከለከሉ። ከኋላ የቀረው ሰረገላ እንደ ደረሰ አቶ ኬዳርናት (ሳትሞት በፊት ባልዋ

የነበረው) ከሰረገላው ብቅ ሲል የቤቱ ሰዎች ተቀበሉት። እነኛ ከቤት እንዳይገቡ የከለከሉት አቶ ኬዳርናት ከሚችቱ ሚስቱ ከወይዘሮ ሉዝ ካሁንዋ ሻንቲ የወለዳቸው ልጆቹ ናቸው። ቶ ኬዳርናት ትልልቆቹን ልጆቹን ጠርቶ «ይቺን ሴት አታውቋትም» ቢላቸው ልጆቹ ይቺን የአሥር ዓመት ልጅ የማያውቋት መሆናቸውን ገለጹለት።

የቀጠለው ጉዞ ወደ ጥንት እናትዋ ቤት ሆነ። ከዚያ ቤት ሲደርሱ ሻንቲ እማዬ እማዬ እያለች ሮጣ ከቤት ብቅ ባለችው አሮጊት ላይ ተጠመጠመች። በልጃቸው ሞት የተጎሳቆሉት እናት በሻንቲ ጩኸት ድንግጥም አላሉም። ሻንቲ ግን ሞታ እንደ ገና የተወለደች የጥንቷ ልጃቸው ሉዝ ነበረች። ሻንቲ በሕይወት በነበረችበት በድሮው ጊዜ አብረው እንዴት እንደ ነበሩ እየዘረዘረች ብትነግርም አሮጊቷ «ዋ እቴ የኔይቱ ጥርኝ አፈር ከሆነች ቆይታለች» ይሉ ጀመር። የምትላቸው ነገር ሁሉ ግን እውነት በመሆኑ ይደነቁ ነበር።

በዚያው በአሮጊቷ ደጅ እንደሆኑ አቶ ጉፐታ ልጅቷን ሻንቲን «በዚህ ሠፈርስ ምን የተለወጠብሽ ነገር አለ« አላት። ሻንቲ በእጅዋ ጠቁማ «ከዚያጋ የውሀ ጉድጓድ ነበር። ዛሬ ግን የለም» አለች። እውነቷን ነው። ጉድጓዱ አደገኛ ተብሎ ከተደፈነ ቆይቷል።

አቶ ኬዳርናትም ከመሞቱ በፊት የልጆችህ እናት ሚስትህ ነበርኩ የምትለውን የአሥር ዓመቷን ልጅ ሻንቲን ጠየቀ «ሚችቷ ሚስቴን ሉዝን ከሆንሽ ስንጋባ ያደረኩልሽ ቀለበት ታሪክ እንዴት ነው? » አላት። ሻንቲም «አንተ እኮ ቀለበቱ የጠፋ መስሎሃል፤ እኔ በወሊዱ ምክንያት ድንገት በመታመሜና በመሞቴ ነው እንጂ ቀለበቱን ያስቀመጥኩበትን ቦታ እነግርህ ነበር። አሁንም ካስታወስከው ከድሮ ቤታችን ጓሮ ከጥጋቱ በምንቸት ውስጥ ተደርጎ ተቀብሯልና ሂድና አውጣው» አለችው። ተቆፍሮ ምንቸቱ ቢወጣ ሻንቲ እንዳለችው ከጥቂት ቤሳዎች ጋር ቀልበቱ ከምንቸት ውስጥ ተገኘ።

የሻንቲ ታሪክ ረጅም ነው። ባጭሩ ይብቃን። ሻንቲን የድሮ ባልዋ አቶ ኬዳርናት እንደገና መልሶ ሊያገባት ነበር ግን ልጆቹ (የእሷው ልጆች) ፈጽሞ ዓይንዋን አናይም ስላሉ ጋብቻው ቀረ።

በ1958 ዓ.ም ዋሽንተን ፖስት የተባለው ጋዜጣ ሻንቲ ጋር ተነጋግሮ የሰጠችውን መልስ አትሞት ነበር። ከጋዜጣው እንደተገኘው ሻንቲ በደልሂ ከተማ በመንግሥት መሥሪያ ቤት በጸሐፊነት ተቀጥራ መሥራቷንና ዕድሜዋም 32 ዓመት መድረሱን ጽፏል።

በጊኒ የፉታዣሎን ሴቶች ሲያጌጡ ጠጉራቸውን ያበጥሩና በተበጠረው ጠጉራቸው ላይ መስተዋት አሥረው በፀሐይ ውስጥ እያብለጨለጩ ይሄዳሉ።

በደቡብ አሜሪካ በአማዞን ሸለቆ ያሉ ካራያ ኢንዲያንስ የተባለ ጎሣ ሰዎች ሲነጋገሩ ከንፈራቸው ፈጽሞ አይነቃነቅም። በከንፈራቸው ፈንታ የሚነቃነቀው አፍንጫቸው ነው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ431 ዓመት ተወልደው በ367 ዓመት የሞቱት ዲዮንሲዮስ ጢማቸውን የሚቆረጡት በመቀስ አልነበረም ዲዮንስዮስ በኢጣልያ አገር ሲሲሊን 38 ዓመታት ገዝተው የነበሩት ናቸው። ጠጉር ቆራጮቻቸው በእሳት የፋመ ከሰል ይዘው በእሳቱ እያንጨረጨሩ ጠጉራቸውን ያስተካክሉላቸው ነበር።

በደቡብ አሜሪካ በፓራጓይ ውስጥ በካይፒፔንዲ ሸልቆ ካኔ (ቻኔ) ኢንዲያንስ የተባለ ጎሣ ሰዎች ውሀ አይጠጡም። የሚጠጡት ከበቆሎ የሚሠሩትን ጠላ ነው።

በሕንድ ውቅያኖስ መሐል ባለችው ኬርጉሌን በተባለችው ደሴት ያሉ ዝንቦች ክንፍ የላቸውም።

በሜክሲኮ ባህረ ሰላጤ አጠገብ ሚኒሙዲ የተባለች የሁለት ዓመት ልጅ ለመጫወቻ የገዙላት 30 የላስቲክ ፊኛ (ባስረውላት ስትጫወት) ነፋስ ይዟት

ወደ ሰማይ ወጣ። ከመሬት 50 ሜትር ያህል ወደ ባህሩ ይዟት ሲሄድ ወደ ላይ ደግሞ ሃያ ሜትር ያህል ራቀች ብዙ ሰዎች ለወሬ ተሰበሰቡ። ከተሰበሰቡት መሐል ጆርጅ መንፌ የተባለ የኮሎራዶ ሰው ጥይት ተኩሶ ጥቂት ፊኛዎችን አፈነዳ። ልጅቷ ወደ ላይ መጓዝ ቀረ። እንደ ገና ተኩሶ ግማሹን ሲያፈነዳ ልጅቱ በሰላም ከቅዱስ ዮሴፍ ደሴት ላይ አረፈች።

በ1630 ዓ.ም ተወልዶ 1697 ዓ.ም የሞተው ፈረንሳዊው ጂን ደ ሳንትዊል የታወቀና የተከበረ ትጥም ገጣሚ (ደራሲ) ነበር። ጂን ግጥሙን የሚጽፈው በወረቀት ላይ ሳይሆን በዛፍ ቅርፊት ላይ ነበር። ግጥሙን ፈጽ፣ፐ በወረቀት ላይ ጽፎ አያውቅም። ከዛፍ ቅርፊት ላይ የተሰበሰበው የጂን ግጥም ዛሬ በኒውዮርክ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ሦስት ታላላቅ ቮሊውሞች (መጻሕፍት) አሉ።

በቱርክ አገር የቱርክ መርከበኞች ከእንጨት የሚሠራ የመርከባቸውን ቅርጽ በባርኔጣቸው ላይ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ወጥቶ ነበር።

ፍራንሲስ ኸንሪ ኤገርተን ውሾቻቸውን ልብስ እያለበሱ ምግባቸውን በየቀኑ በጠረጴዛ ላይ ከውሾቹ ጋር ይበሉ ነበር። በናፖሊዮን ዘመን የሮማ ልዑል የነበሩት እኚህ ሰው በፓሪስ ከተማ ከነበረው ከታላቁ ሆቴል ደ ኖይለስ የውሾቹና የእሳቸው ምግብ በየቀኑ ይታዘዝ ነበር። ልዑሉ በዓመት ሃያ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ገቢ ነበራቸው።

በደቡብ አሜሪካ በፔሩ የሚኖሩ ካምፓ ኢንዲያንስ የተባለ ጎሣ ሰዎች ዓይናቸው የሚያውቀው የግልብጥ ነው። ለምሳሌ አንድ የቆመ ሰው የሚያዩት ተዘቅዝቆ ነው።

በኮንጎ ግዛት ባንዛ ሳንጋቦንዳ የተባለ ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ሰዎች አረቄ መጠጣጥ ይወዳሉ። የዚህ ጎሣ አለቃ ወይም ባላባት በሞት ጊዜ በሕይወቱ ሳለ ጠጥጦ ያጋባው ባዶ ጠርምሙስ በመቃብሩ ላይ ይደረደራል።

የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት አብርሃም ሊንከን፤ ክርስቶስ በተወለደበት ቀን (የገና ዕለት) ተወለዱ። የአናጢ ልጅ ናቸው። አርብ ቀን ተገደሉ።

በካምቦዲያ አንዲት ሴት በባልዋ ላይ ስትወሳልት ከተገኘች በጉንጭዋ ላይ የወንድ ስዕል ይሳልባታል።

በ1762 ዓ.ም የተወለደው ፒየር ጂን ጋራት የተባለው ፈረንሳዊ ዘፋኝ አንድ ጊዜ በጆሮው የሰማትን ዘፈን ያለ ምንም ስህተት መልሶ ይዘፍናት ነበር። ከዚህ ሌላ ማንኛውም የሙዚቃ መሣሪያ ሲጮህ ከሰማ እንደ ገና ያንኑ የሙዚቃ ድምፅ መልሶ በቃሉ ለማሰማት ችሎታ ነበረው። ፒያኖ ሲጫወቱ ከሰማ መሶ ያንኑ ፒያኖ ሙዚቃ ድምፁን ልክ እንደ ፒያኖው አድርጎ ይጫወታል። ሌላውንም የሙዚቃ መሣሪያ ሁሉ በድምፁ ይጫወተው ነበር። ፒየር በፓሪስ የኦፔራ ዘማሪ ነበር። የሞተው በ1823 ዓ.ም ነው።

ፓኦ ሴኡ ያ የተባለች ቻይናዊት በውበትዋ እጅግ የተደነቀች ቆንጆ ነበረች። የቻይና ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ግርማዊ ዩ ለዚች ቆንጆ ሲሉ እቴጌይቱን ሚስታቸውን ፈተው ፓኦን አገቡ። ፓኦ ግንባርዋ የማይፈታ ፈገግታ የማይታይባታ ወይዘሮ በመሆንዋ ቋጣራ ግንባራውና ለማስፈታ ንጉሡ ብዙ ደከሙ። የሀገሪቱ ቀልደኞች እየተሰበሰቡ እንዲያጫውቷት ተደረገ። ሙዚቀኞችም በየቀኑ የምትወደውን ዘፈን እንዲያሰሙዋት ታዘዙ። ፓኦ ምንም ፈገግ ልትል አልቻለችም። በመጨረሻው ንጉሡ «ንግሥቲቱን ፈገግ ላደረገ ሰው አንድ ሺ የወርቅ ገንዘብ እሰጣለሁ» ብለው አወጁ። ሺው የወርቅ ገንዘብ በአሁኑ የኢትዮጵያ ብር ምንዛሪ 8.750.000ን ብር ነው። ከዚህ አዋጅ በኋላ ካኦ ሺ ፉ የተባለ የፍርድ ሚኒስትር በማጭበርበር ፈገግ አሰኛት።

በኒውዮርክ አውራጃ በብሮክላይን ከተማ ይኖሩ የነበሩት የአቶ ጴጥሮስ ናፖሊታኖ ውሻ በፀሐይ ጊዜ ጥቁር መነጥር ሳያደርግ መሄድ አይችልም ነበር።

ከበግ ጠጉር ከሚሠራው ክር ይልቅ ከብረት የሚሠራ ክር ቶሎ ይቃጠላል።

ዎልተር ኒልሰን የተባሉ አሜሪካዊ ሦስት ሜትር ያህል ርዝመት ባላት ባለ አንድ እግር ብስክሌት 3386 ማይልስ ተጉዘዋል። የኒልስን ጓደኛ «በዚች በባለ አንድ እግር ብስክሌት አሜሪካን ባለ አንድ እግር ብስክሌት አሜሪካን በአምስት ወር አትዞርም» ብለዋቸው ተወራረዱና የመጀመሪያ ጉዞአቸውን ከኒውዮርክ ከተማ ጀመሩ። ከዚያ በ17 ቀናት አሜሪካን ዞረው ተመለሱ።

የስፔይን ንግሥት የነበሩት ንግሥት ማሪያ ሉይስ በአርባ ዕድሜያቸው ጥርሳቸው በሙሉ ረገፈ። 625.000 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ወጪ አድርገው በረገፈው ጥርሳቸው ምትክ ከአልማዝ የተሠራ ጥርስ አስተክለዋል።

የምዕራብ ሳክሶንስ ገዥ የነበሩት ንጉሥ አልፍሬድ ምግባቸውን ይሠሩበት የነበረው ጠረጴዛ ዛሬም ሊንግ በተባለች የእንግሊዝ ከተማ ውስጥ ያገለግላል። ዕድመኢው 1050 ዓመት ሆኖታል።

እስካሁን ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ስዕል «የሚሲሲፒ ትርኢት» የተባለው ነው። የስዕሉ ርዝመት አራት ኪሎ ሜትር ከስምንት መቶ ሜትር ነው። ሰዓሊው በ1815 ዓ.ም ተወልዶ በ1819 ዓ.ም የሞተው ጆን ቫንቨርድ ነው። የስዕሉ ሥራ በ1840 ዓ.ም ተጀምሮ በስድት ዓመት አለቀ።

በሕንድ አገር በፑንጃብ አውራጃ በባሁ ቀበሌ ሼህ ጋዚ ካሜል የተባሉ ሰው ነበሩ። በ1635 ዓ.ም ሐጃር በተባለ ቀበሌ ጦርነት ተነሳና ሼሁ በፈረሳቸው ሆነው ዘመቱ። ከጦርነቱ አንድ የጣላት ሰይፍ የሼሁን አንገት በጥሶ ጣለው፤ ፈረሳቸውን የሼሁን ሬሳ ተሸክሞ እየጋለበ 26 ኪሎ ሜትር ርቀት ካለው ከሼሁ ቤት አደረሰው። ዛሬ በዚያ በሼሁ ቤት አንድ ምስጊድ ተሠርቶ ብዙ ሰዎች ይጸልዩበታል።

በኢራን ግዛት ሻህሩብ በተባለ ቀበሌ የቃሲም ክህን መቃብር አለ። በዚያ መቃብር አጠገብ ጉንዳኖች የሚሄዱበትን መንገድ ማሰናከል በጥብቅ ክልክል ነው። ቃሲም ክህን ሳይሞቱ በፊት በልብሳቸው ላይ አንዲት ጉንዳን አግኝተው

ያቺን የባዘነች ጉንዳን ቤትዋን ፈልገው ከቤትዋ ለማስገባት አንድ ሺ ማይል ተጉዘው ስለነበር ለእሳቸው መታሰቢያ ነው።

በፈረንሳይ አገር ሴይላክ በተባለ ቀበሌ የሚኖሩ ሰዎች ቀን ሥራ ሲሠሩበት የዋሉት ጠረጴዛ ማታ መሳቢያው እየወጣ ለቤተሰቡ መኝታ ይሆናል።

በጀርመን አገር ስችዋርዝዋልድ በተባለ ቀበሌ ይኖሩ የነበሩት አቶ ጆርጅ ሜየር አንዲት ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ሥራውን አስጀምረው ገንዘብ ስላነሰ ሃያ ዓመት ሙሉ ርዳታ እየለመኑ አሠርተው የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ አለቀ። የቤተ ክርስቲያኑ በር ለመጀመሪያ ጊዜ ለጸሎት የተከፈተው አሠሪው አቶ ጆርጅ ሞተው ለፍታታቸው ነው።

እንግሊዛዊው ዝነኛ ቋንቋ አዋቂ የነበሩት ኤድዊን ኖሪስ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ፖርቱጋልኛ ውደማአሪኛ ወደ እስፓንኛ ወደ አረብኛ ወደ አክራኛ ወደ እኔይቱ ወደ አቲጃኛ ወደ ቡልጋሪያኛና ወደ ኢጣልያኛ በአጭሩ በአሥራ አንድ ቋንቋ ተርጉመውታል። ኤድዊን በ1795 ዓ.ም ተወልደው በ77 ዓመታቸው በ1872 ዓ.ም ሞቱ።

# እንቁራሪት የምትሰማው በዓይኗ ነው።

ስር ሪቻርድ ሜይትላንድ የስኮትሽ ግጥም ገጣሚ ጠበቃና የሴቶች ልብስ አቃቂር አውጪ (ተቺ) ነበር። ሪቻርድ በ1496 ዓ.ም ተወልዶ በ1586 ዓ.ም እስኪሞት ድረስ ዓይኑ የማያይ እውር ነበር።

በእንግሊዝ አገር ቦው በተባለ ቀበሌ አንድ የፈረስ ጫማ መሥሪያ ቤት አለ። የፈረስ ጫማው መሥሪያ የተቋቋመው በ1398 ዓ.ም ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ 1880 ዓ.ም ድረስ ማለት 482 ዓመታት ሙሉ በዚያ ቤት

ያለማቋረጥ የፈረስ ጫማ ሲሠራበት ኖርዋል። ቤቱን ያቋቋሙት ምስኪኑ ቶዜሬ ሲሆኑ የእሳቸው ምስኪን ትውልዶች እየወረሱ ሠሩበት።

የቱርኩ ቀዳማዊ ሡልጣን አህመድ በ1611 ዓ.ም በፋርስ ላይ ለመዝመት የጦር አዋጅ አወጁ። የጦርነቱ መነሻ የሡልጣኑ ሦስት ሺ ሚስቶች የሚለብሱት ሐር ጨርቅ ከፋርስ አገር ለማግኘት ብለው ነው።

በጃቫ እንደወፍ የሚበሩ እንቁራሪቶች አሉ። እግራቸውን እንደክንፍ አድርገው ይጠቀማሉ።

በሜክሲኮ ግዛት ሞንትሬይ በተባለ ከተማ ይኖሩ የነበሩት አቶ ፓቢይ ሳላስ በ51 ዓመት ዕድሜያቸው ሃምሳ ኪሎ ክብደት ያለውን ብረት በአንድ እጃቸው ይዘው በ15 ደቂቃ ከ10 ሰከንድ መቶ ጊዜ መረኢት እያስነኩ ወደ ላይ መልሰዋል።

በአማዞን ወንዝ ውስጥ የሚገኘው የዚህ ዓይነት ዓሳ ዘር እንቁላሉን የሚጥለው (የሚወልደው) ከውሀ አጠገብ ካለ ዛፍ ላይ ወጥቶ ነው።

ሰር ቶማስ ብስቤን በእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ውስጥ ሰባ ዓመት ሙሉ አገልግለዋል። ሰር ቶማስ በ1860 ዓ.ም 87 ዕድሜያቸው ሲሞቱ ነፍሳቸው የወጣችው በ1773 ዓ.ም ከተወለዱበት አልጋ ላይ ተኝተው ነው። በዚያ አልጋ ላይ የተወለዱና የሞቱ ዕለት ብቻ ተኙበት።

የፈረንሳይ ንጉሥ የነበሩት ሄንሪ በ1503 ዓ.ም ሲወለዱ ሄንሪ የተባለ ለማኝ ከውጭ ሆኖ ይለምን ነበር። ወዲያው የለማኙ ስም ተጠይቆ የሕፃኑ ስም በለማኙ ስም ሄንሪ ተብሎ ተጠራ። ንጉሥ ሄንሪ የሞቱት በ1555 ዓ.ም ነው።

በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ አቶ ቪቶ ዶሉክ በመንገድ ሲሄዱ በሰማይ የምትሄድ ርግብ እንቁላል ወልዳ ሳይሰበር ከባርኔጣቸው ላይ አርፏል።

በስኮትላንድ አገር ሶልትኮትስ በተባለ ቀብሌ ይኖር የነበረ ሮበርት ሚሌር የተባለ ልጅ በአሥር ዓመት ዕድመኢው መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር በእጅ ጽፎ በ120 ቀን ጨርስታል።

በኦንታርዮ የሚኖሩት አቶ ጆን እስፐራይ ከዘር የወረሱት አንድ አሮጌ ሰዓት አላቸው። ከሰዓቱ ሁለት እጆቻቸው ቆጣሪው ብቻ ሥራውን ይሠራል። የሰዓቱ ዕድሜ 550 ዓመት ነው።

በጃፓን አገር የሰው ማመላለሻ ጀልባዎች የሚሄዱት በሰባት ዋናተኛ ሰዎች እየተጎተቱ ወይም እየተሳቡ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ ያለው የቱርካና ጎሣ ወጣት ወንዶች በታችኛው ከንፈራቸው ላይ ከባድ የኳስ ብረት ያሥራሉ። ምክንያቱም ስያወዱ በግድ ሁልጊዜ ፈገግታ እንዲኖራቸው ብለው ነው።

እንግሊዛዊቷ የፊዝፎርድ ነዋሪ የነበረችው ወይዘሮ ሜሪ ፊዝ 16 ዓመታት ዕድሜ ሳይሞላት ሦስት ባሎች አግብታ ፈታለች።

በእንግሊዝ አገር በኒውሀም ይኖሩ የነበሩት እመት ጄን ኬይት በ1780 ዓ.ም ሲሞቱ ዕድሜያቸው 133 ዓመት ነበር። እመት ጄንን ጦረው የቀበሩዋቸው ሦስት ልጆቻቸው ናቸው። ጄን ሲሞቱ የሦስቱ ልጆቻቸው ዕድሜ 109 110 እና 111 ዓመታት ነበር።

በሕንድ አገር በደልሂ አንድ መቅደስ አለ። መቅደሱ የተሰራው በአውሬ ምስል ነው። የመቅደሱ መግቢያና መውጫ በአውሬው ምስል አፍ ማልሱ እየተረገጠ ነው።

ጆን ስሚዝ አገጫቸውን በጡጫ በመደብደብ ብቻ ማንኛውንም ዓይነት ሙዚቃ መጫወት ይችሉ ነበር። እኒህ ሰው በለንደን ከተማ የመንገዱ ሙዚቀኛ በሚል ቅጽል ስም የታወቁ ነበሩ።

በአሜሪካ አገር በማሳቹቴስ አውራጃ ኒውተን የሚሉት ድልድይ አለ። ድልድዩ አጠገብ አንድ ሰው ሲጮህ የድምፁ ማስተጋባት አሥራ ሰባት ጊዜ ይሰማል።

በየቀኑ ሦስት ኮፒ ብቻ የሚታተም ጋዜጣ በቪየና ነበረ። በሦስት ኮፒ እትመት ብቻ ለሦስት መቶ ዓመታት ቆይቷል።

በሕንድ አገር ያሉ የካራቫስ ጎሣ ሰዎች አንድ ሰው በወንጀል ሲከሰስ ቅቤ የተሞላ ድስት እሳት ላይ ተጥዶ ሲንተከተክ ተከሳሹ ጣቱን በቅቤው ውስጥ እንዲጨምር ያደርጋሉ። ጨምሮ ካወጣው በኋላ ጣቱ በሊጥ ይታጀላል። ቅቤው የተነከረው ጣቱ ከታጀለበት ሲፈታ ቆዳው ከተላጠ ሰውየው ወንጀለኛ መሆኑ ይታወቃል።

የሩሲያ ወታደሮች መሪ የነበሩት ማረሻል ሴቭሮቭ በየዕለቱ ጧት ጧት እንደ አውራ ዶሮ በመጮ፤ ወታደሮቻቸውን ይቀሰቅሱ ነበር። ሱቭሮቭ በ1720 ዓ.ም ተወልደው በ1800 ዓ.ም ሞቱ።

በፈረንሳይ አገር በፓሪስ ከተማ ይኖሩ የነበሩት ባሮን ደ ማሺ በየቀኑ በክረምትም ሆነ በበጋ ያለማቋረጥ ካፌ ደሎዥ ከተባለ ቡና ቤት ደጃፍ ላይ ባለው ጠረጴዛና ወንበር 42 ዓመታት ተቀምጠዋል።

በ1541 ዓ.ም የስፔይን ንጉሥ ቻርል ቀዳማዊ በፓልማ ደ ማሎክ ካቴድራል ውስጥ ለጥቂት ደቂቃዎች የተቀመጡበት ወንበር እስከ ዛሬ ድረስ 428 ዓመታት ሙሉ ከዚያች ሥፍራ አልተነሳም።

በካናዳ ግዛት በአንታሪዮ ቀበሌ አንዲት አውቶሞቢል ከዛፍ ጋር ብትጋጭ የአውቶሞቢሉዋ መለያ ቁጥር (ታርጋ) በዛፉ ላይ ታትሞ ቀረ።

በስኮትላንድ ቶርጊሌ በተባለ ቀበሌ ከዛሬ 150 ዓእምታት በፊት ቄስ ፊናሌ ሙንሮ ሰዎችን ሰብስበው ሲሰብኩ የቆሙበት መሬት እስከ ዛሬ ሣር አልበቀለበትም።

የካሊፎርኒያ ሰዎች የገንዘብ ወይም መያዣ ቦርሳቸው የሚሠራው ከእንጨት ነው። በእንጨቱ ቦርሳ ላይ እንጨቱ እየተቀረጸ የሰው ምስል ይበጅበታል። ምስሉ የሚሠራው የቦርሳውን ውስጥ ዕቃ ከሌባ እንዲጠብቅ ነው ይላሉ።

በኢጣልያ አገር ቡሳ በተባለ ቀበሌ የካቲት 23 ቀን 1887 ዓ.ም የመሬት መንቀጥቀጥ ደርሶ አንዱ ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበር ሆኖ ጠፋ። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩት 300 ሰዎች ሲሞቱ መስሐፍ ቅዱስን ለሕዝብ ያነብ የነበረው ቄስ ብቻ ምንም ሳያገኘው ዳነ።

በሀንጋሪ ዋና ከተማ በቡዳፔስት አንድ የታላቅ ሰው ሐውልት አለ። ሐውልቱ የቆመለት ሰው በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታሪክ ሠርቶ ሐውልቱም በዚያው ዘመን ቆመ። አሁን ያ ሐውልት የቆመለት ሰው ተረስቶ ያ ሐውልት የማን እንደ ሆነ ማንም ሰው አያውቀውም።

በፖርቱጋል ውስጥ አልጋርቬ በሚባል ቦታ በሰው አጥንት የተሠራት መቅደስ አለ።

የሩማንያ ሰዎች የቁርጥማት በሽታ በያዛቸው ጊዜ አንድ የሰለጠነ ድብ በጀርባቸው ላይ እንደመሰላል ያደርጋሉ። የድቡ በጀርባ ላይ መመላለስ ከቁርጥማት ያድናል ብለው ያምናሉ።

በጀርመን አገር ኤርፌንስቱን በተባለ ቀበሌ መለኪያ በመሰለ ድንጋይ ቅርጽ ላይ የተሠራ ታላቅ ቤት አለ። ቤቱ የተሠራው በጀርመን አገር በጠጪነቱ እውቅ በነበረ ሰው ነው።

በቱርክ ሡልጣን የነበሩት ዳግማዊ መሐመድ አንድ ቀን ምግባቸውን በልተው ፍራፍሬ ቀረበላቸው። ወደ ውጪ ወጣ ብለው ሲመለሱ ከፍራፍሬዎቹ አንድ ከርቡሽ (ውሀ የሚወጣው ዱባ) ጠፋ። በዚያ የነበሩት 14 አሽከሮቻቸውን በልተውት እንደሆነ ቢጠይቁ ያለመብላታቸውን

ገለፁላቸው። ቀዳጅ አስጠርተው የአሥራ አራቱንም አሽከሮቻቸውን ሆድ እየቀደዱ መረመሩ።

ዳግማዊ ሡልጣን መሐመድ በ1415 ዓ.ም ተወልደው በ1491 ዓ.ም ሞቱ።

በኢጣልያ አገር ፖርቶ ቬኔሬ የተባለው ከተማ በ1131 ዓ.ም ለጀኖአ የተሸጠው ባርባ ሳንቲም ነው።

በእንግሊዝ አገር ያበሪ በተባለ ቀበሌ ባለው የማዕድን ሥፍራ በ1852 ዓ.ም ታኅሣሥ 6 ቀን የማዕድኑ ድንጋይ ተንዶ ቶማስ ሮጀርስ የተባለውን ሰው ገደለው። በዚያች ቦታ ድንጋይ እየተናደ የገደለው ቶማስን ብቻ አይደለም። የቶማስን አባት፤ አያትና ቅድመ አያት ጭምር ነው የሞቱትም ልክ በያሙቱ ነው።

በሕንድ አገር ቪዳ የተባለው ነገድ ሕግ አንዷት ሴት 18 ጊዜ ባል ለዋውጣ ማግባት ትችላለች ይላሉ።

በአፍሪካ ያሉ የሶምባ ነገድ ሰዎች አንዷት ሴት ልጅ ለጋብቻ ስትደርስ አንድ ጎጆ ይሠራል። ባንድ ሰው ቤት ስምንት የደረሱ ልጆች እንዳሉ የደረሱ ልጆች እንዳሉ የነዚህ የደረሱ ልጆች መኖር የሚታወቀው በግቢው ውስጥ ባሉት ስምንት ጎጆዎች ነው።

በኢንዶኔዝያ ውስጥ ቲሞር በተባለች ደሴት የሚኖሩ ሰዎች የውሀ መቅጃ ስልቻቸውን የሚሠሩት ከቅጠል ነው።

በፖርቱጋል ግዛት ናዛሬ በተባለች ቀበሌ ያሉ አሣ አጥማጆች ሁለት የዕቃ መያዣ ኪስ አላቸው። አንዱ ኪስ ከልብሳቸው ላይ ሲሆን አንደኛው ደግሞ ከቆባቸው ላይ ነው።

በሰሃራ በረሃ በለሊት የሚጓዙ መንገደኞች ፋኖስ አብርተው በግመሎቻቸው አንገት ላይ አንጠልጥለው ይጓዛሉ።

በፈረንሳይ አገር ሬሚሬሞት በተባለ ቀበሌ በ1764 ዓ.ም የተሠራ ቤተ ክርስቲያን አለ። ቤተ ክርስቲያኑ እስካሁን የተቀደሰበት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያኑን የሠራው ሰው «በመቶ ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የቤተ ክርስቲያኑ በር ተከፍቶ እንዲቀደስበት» ብሎ በማዘዙ ነው።

በኬንያ ሕፃን ልጅ በዕድሜዋ አንዳንድ ዓመት አንዳንድ ሎቲ በጆሮዋ ታንተለጥላለች።

በ1737 ዓ.ም ተወልደው በ1820 ዓ.ም የሞቱት አቶ ፍራንሲስ ቦልተን በበጋም ይሁን በክረምት ባርኔጣቸውን የሚያደርጉት ከውስጡ በረዶ እየሞሉ ነው። ቦልተን የሚኖሩት በእንግሊዝ አገር ብሩህብሪጅ በተባለ ቀበሌ ነበር።

በ1958 ዓ.ም በብራዚል ውስጥ የሳአፖሎ ከተማ ነዋሪዎች የከተማውን ምክር ቤት እንደራሴ ሲመርጡ አምሳ ሺ ሰዎች አንድ አውራሪስ ለእንደራሴነት መርጠዋል።

በምዕራብ አፍሪካ የቱቡስ ነገድ ሰዎች በፍርድ ሸንጎ የሚሟገቱት ዳኛው፤ ከሳሹ ተከሳሹና ምስክሮቹ በአንድ ምንጣፍ ላይ ዙርያውን ተኝተው ነው።

ሎድዊንግ ዌበር የተባለ በአውስትራሊያ አገር ሮቺዝ በተባለ ቀበሌ የአንድ መጋዘን ዘበኛ በሰማንያ ዓመት ዕድሜው አምሳ ኪሎ የሚከብድ በወይን ጠጅ የተሞላ በርሚል ከመሬት አንስቶ ወደ አፉ በማስጠጋት ይጠጣ ነበር። ይህ ሰው በሰማንያ ዓመት ዕድሜው አሥራ ሁለት ሺ አምስት እምቶ ጋሎን ወይን ጠጅ ጠጥቷል።

ከዛሬ 150 ዓእምት በፊት በፈረንሳይ አገር ይኖሩ የነበሩ ታላላቅ ሰዎች በዝናም ጊዜ በመንገድ ላይ ሲሄዱ ለመብረእቅ መከላከያ በዣንጥላቸው ላይ ሽቦ ያሥሩ ነበር።

በግሪክ አገር ማይኮኖስ በተባለችው ደሴት ባለው ሆቴል ራታቸውን ሲበሉ የሚሄዱ ሰዎች ሁሉ ጫማቸውን አውልቀው እግራቸውን በውሀ ውስጥ

ዘፍዝፈው ይመገባሉ። ሆቴል ቤቱ ያለው በባሕር ዳር በመሆኑ ማንኛውም ተመጋቢ እግሩን ውሀ ውስጥ ሳያኖር አይመገብም።

በናይጄሪያ ካና በተባለ ቀበሌ የሚኖሩ ሰዎች ቤታቸውን የሚሰሩት ልክ የግብጹን ፒራሚድ አስመስለው ነው።

በጀርመን አገር ስቱንፉርዝ የምትባል ቀበሌ አለች። በቀበሌዋ የሚታየው ተክል ጽጌረዳ ብቻ ነው። በቀበሌዋ 12 ሚሊዮን የጽጌረዳ ዛፍ አለ።

በአንታርቲክ የወፈረው በረዶ ቢቀልጥና ቢፈስ ውቅያኖሶች አሁን ካላቸው ልክ 300 ጫማ ከፍታ

በአንታርቲክ የወፈረው በረዶ ቢቀልጥና ቢፈስ ውቅያኖሶች አሁን ካላቸው ልክ 300 ጫማ ከፍታይ ጨምራል።

በሶማልያ አገር አንዳንድ ውሀ የሚቀዱበት ዕቃ የሚያበጁት ከግመል ጨጓራ ነው።

ቲቲአን የተባለው ዝነኛ ስዕል ላይ ስዕሉን የሚስለው በብሩሽ ሳይሆን ቀለሙን በጣቱ እየነከረ በመቀባት ነበር። ቲቲአን በ1477 ዓ.ም ተወልዶ በ1576 ዓ.ም ሞተ።

በ1889 ዓ.ም ተወልደው በ1908 ዓ.ም የሞቱት የፖርቱጋሏ ንግሥት አሜሊ አንድ ቀን ከባሕር ዳር ቆመው ሲመለከቱ አንድ አሣ አጥማጅ ከባህሩ ውስጥ ሲሰጥም አዩ። ንግሥቲቱ ከነልብሳቸው ከባሕሩ ውስጥ ገብተው በመዋኘት አሣ አጥማጁን ከባህሩ ውስጥ አውጥተው ከሞት አድነውታል።

በአሜሪካ አገር በፔንሲልቫኒያ አውራጃ ኮንማፍ ከተባለ ወንዝ አጠገብ ጆንታውን የተባለች ከተማ ነበረች ይቺ የእንዱስትሪ ከተማ በ1889 ዓ.ም ግንቦት 31 ቀን ኃይለኛ የውሀ ማጥለቅለቅ ደረሰባት። የውሀው ኃይል ነቅሎ የወረወረው ዛፍ በቀጥታ ከዶክተር ዚሜርማን ቤት ውስጥ ገብቷል።

በፈረንሳይ አገር በ1903 ዓ.ም ለሰካራሞች በየቀኑ ዲስኩር ይደረግላቸው ነበር። የሚያስደንቀው ለሰካራሞቹ መቀመጫ የተበጀው ሣጥን ነው።

ከኒውዮርክ ከተማ 33 ማይል ርቃ በምትገኝ ባታቪያ በተባለች ቀበሌ የካቲት 18 ቀን 1885 ዓ.ም ባቡሮች ተጋጭተው አንደኛው ባቡር ከአንደኛው ባቡር ጎታች ላይ ወጥቶበታል።

በጀርመን አገር ቦግን በተባለ ቀበሌ አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ። ለዚህ ቤተ ክርስቲያን በያመቱ በበዓሉ ቀን አንድ ሻማ ይሰጣል። ሻማው 17 ኪሎ ክብደት እና 10 ሜትር ረጅም መሆን አለበት። ሻማው ዓመቱን ሙሉ ሲበራ ቆይቶ በዓመቱ የበዓሉ ዕለት ያልቃል ከዚያም አዲሱ ሻማ ይተካና ይበራል።

በ1849 ዓ.ም ወይዘሪት ሱዛን ባርቶን የተባለች ሴት በኒውዮርክ ከተማ ባርነም አሜሪካን ሙዝየም ውስጥ ለሕዝብ ልትታይ ቀርባ ነበር። የሱዛን ክብደት 288 ኪሎ ነበር። ቁመትዋ ሦስት ክንድ ተኩል፤ ክንዷ ዙርያ ክቡ 33 ኢንች ተኩል፤ የደረትዋ ስፋት 69 ኢንች፤ የዳሌዋ ውፍረት 87 ኢንች ነበር።

## ኤሮፓውያን በአዞ የሚሳብ ጋሪ ለልጆቻቸው ይሠሩ ነበር።

በሲያም ውስጥ ባንጉሳኡ በተባለ አምባ በ1811 ዓ.ም ሚያዝያ 15 ቀን የተጣበቁ መንታ ልጆች ተወልደዋል። ልጆቹ የተጣበቁት ከትከሻቸው ጀምሮ ቁልቁል እስከ ዳሌያቸው ነው ልጆቹ ተወልደው ማደግ እንደጀመሩ አንዱ ቸንግ ተባለ። ሁለተኛው ደግሞ ኢንግ ተባለ። እንደ ተጣበቁ አደጉ። በተወለዱ በ32 ዓእምታቸው በ1843 ዓ.ም በሚያዝያ ወር እንደተጣበቁ ሁለት ሚስቶች አገቡ። አንደኛይቱ ሣራ ስትባል ሁለተኛይቱ ደግሞ አድላይድ ትባላለች።

እነዚህ የተጣበቁ ሰዎች ከነዚሁ ሚስቶቻቸው 22 ልጆች አስወለዱ። አንደኛው አሥር ልጆች ሲያስወልድ አንደኛው ተጣባቂ ደግሞ 12 ልጆች አስወለደ። እነዚህ ተጣባቂዎች 62 ዓመት ኖረው በ1874 ዓ.ም ጥር 17 ቀን አንደኛው ተጣባቂ ሞተ። ያ በሞተ ከሦስት ሰዓት በኋላ ሁለተኛው ተጣባቂ ወንድምየው ሞተ።

የተጣበቁ ሰዎችን ነገር ካነሳን ዘንዳ አና እና ቢሊ ግሬይ የተባሉም ሴቶችም ተጣብቀው ተወልደዋል።

በ1717 ዓ.ም በኤሮፓ የአሳማ አፍንጫና አፍ ያላት ሴት ተወልዳ ነበር።

በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ውስጥ ሦስት እግሮች ያሉት ልጅ ተወልዶ አድጓል።

በኢንዶ ቻይና በቶኪን አንድ በገደል ላይ የተንጠለጠለ መቅደስ አለ። መቅደሱ ሦስት ፎቆች አሉት። መቅደሱ ከገደሉ ጋር አልተያያዘም። ከሥሩ አሥራ ሁለት ምሰሶዎች ተደርገውለት ከመሬት ሃያ ሰባት ሜትር ርቆ በመሐል ቦታ ተንጠልጥሎ የቆመ ነው።

በሕንድ አገር ሙንድራ በተባለ ቀበሌ ለአንድ ሐርቫይ ለተባለ ቅዱስ ሰው የተሠራ ሐርቫይ በሕይወቱ በነበረ ጊዜ ድመቱን በጣም ይወድ ነበርና የመታሰቢያው ቤተ መቅደስ ሲሠራ ቁንጮው በሙሉ የተከበበው በድመቷ መዳፍ ቅርጽ በተሰሩ ሐውልቶች ተከቦ ነው።

የባቫሪያው ንጉሥ ዳግማዊ ሎድዊግ በቤተ መንግሥታቸው ሥር ዋሻ አስቆፍረው ዋሻውን በውሀ ካስሞሉ በኋላ በጀልባ መንሸራሸሪያ አድርገውት ነበር። ንጉሡ በዚህ የዋሻ ውስጥ ባሕር ላይ የሚንሸራሸሩበት ጀልባ የተሠራው በሙሉ ከንጹህ ወርቅ ነው።

ከዛሬ ስድስት መቶ ስልሳ ሦስት ዓመት በፊት የትራፊክን ደንብ ያወጡት ፓፓ ቦኒፌስ ስምንተኛ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል። በያመቱ ወደ ሮማ የሚሄደው

ምዕመን እየበዛ በመሄዱ በአንዲት ድልድይ ላይ ለመሻገር የሕዝቡ ትርምስ ስላስቸገረ ሕዝቡ በዚያች ድልድይ ላይ እንዴት አድርጎ በሥነ ሥርዓት ለመተላለፍ እንደሚችል በ1300 ዓ.ም ደንብ አውጥተው ሰጡ።

በ1756 ዓ.ም ተወልደው በ1832 ዓ.ም የሞቱት ወይዘሮ ሐና አዳምስ በአሜሪካ አገር በማሳቹሴትስ ውስጥ በብሮክሌይን ይኖሩ ነበር። እኚህ ሴት «የአዲሲቱ እንግሊዝ ታሪክ» የሚል ጽሑፍ ጽፈዋል በዚህ መጽሐፋቸው ከአሜሪካ ሴቶች ሁሉ የመጀመሪያይቱ ደራሲ ናቸው።

በመጀመሪያ ጊዜ የተሠሩት ሰዓቶች ከባዶች ነበሩ። በዚያን ዘመን ሰዓት ያላቸው ሰዎች ሰዓቱን የሚሸከም አሽከር ቀጥረው እያሸከሙ ይሄዱ ነበር።

መቶ አለቃ ቶማስ ፉሳ በእንግሊዝ ፲፪ኛው ሬጂሜንት ውስጥ ያንድ ክፍለ ጦር አዋጊ ነበር። በ1799 ዓ.ም ሚያዝያ ፮ ቀን እንግሊዞች ከሕንድ ጋር ሲዋጉ ሴሪንግፓታም በተባለው ጦር ሜዳ መቶ አለቃ ቶማስ ተመትቶ ወደቀ። በዚያው ባለበት ሆኖ ወታደሮቹን ሲያዋጋ ውሎ ሞተ። ከሞተ በኋላ ለቀብር ሬሳው ሲነሳ አሥራ ሦስት ኪሎ የሚመዝን የመድፍ ጥይት ከባቱ ውስጥ ተወሽቆን ተገኘ። መቶ አለቃ ቶማስ ያን የሚያህል የመድፍ ጥይት ተሸክሞ ሥቃዩን ታግሶ ለታዘዘበት ተግባር ተሰዋ።

ኢቫን አስየር የተባለ የዳኒሽ ሰው አገሩን በመወከል በኦሊምፒክ አደባባይ አርባ ዓመታት ሙሉ ተሰልፏል።

በሕንድ አገር የፑንጃብ አገረ ገዥ የነበሩት ሁሴን አሊ ሻህ በሰማንያ አራት ዓመታቸው ሞቱ። እኚህ ገዥ በሃያ ሁለት ዓመታቸው የገብስ ቂጣ መባልት ጀምረው እስከ ዕድሜያቸው ፍጻሜ ድረስ ስልሳ አራት ዓመት ሙሉ ይመገቡት የነበረው የገብስ ቂጣ ብቻ ነበር። ሁሴን ኩሊ ሻህ በ1568 ዓ.ም ጀምረው እስከ 1572 ዓ.ም ድረስ ፑንጃብን ገዝተዋል። በአገራችን ገብስ ቂጣ ዕድሜ ያረዝማል የሚሉት እውነት ይሆን?

በኢጣልያ አገር ቪቼንዛ በተባለ ከተማ በ1580 ዓ.ም በአንድሪያ ፓላዲዮ የተሠራ ኦሊምፒክ ቴያትር የተባለ ቴያትር ቤት አለ። ይህ ቴያትር ቤት ጣሪያ አላቸው ቴያትር ቤቶች ሁሉ የመጀመሪያው ነው። ከዚያን ጊዜ በፊት የቴያትር ቤቶች ሁሉ ዙርያቸውን ግንብ መገንባት ብቻ እንጂ ከበላያቸው ጣሪያ አይደረግባቸው።

በስኮትላንድ አገር እስቱብሆልም በተባለው ቀበሌ የሚኖር አርኪ አርምስትሮንግ በሌብነቱ አገሪቱን ያስቸገረ ሰው ነበር። አንድ ጊዜ በጎች ሠረቀና እንዳይገደል ተፈረደበት። ይህ ሌባና የመንገድ ላይ ቀላጅ ሰው የሞት ፍርድ ሊጸናበት ከንጉሥ ጀምስ ስድስተኛ ዘንድ ቀረበ። በዚያም ንጉሡን አንድ ነገር እንዲለምን ጠየቃቸው። ንጉሡም «ለምን የለመንከው ሁሉ ይፈጸምልሃል» ብለው ቃል ገቡለት። አርምስትሮንግም «ግርማዊ ሆይ፤ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቤ እስክጨርስ ድረስ እንዳልገደል ብቻ ፍቀዱልኝ እንጂ፤ ከተፈረደብኝ ፍርድ ይማሩኝ ብዬ አለምንዎትም» አላቸው። ንጉሡም ጉዳዩ ቀላልና የጥቂት ጊዜ ቀጠሮ የሚጠይቅ መሆኑ አውቀው «ፈቅጀልሃለሁ» አሉት። አርምስትሮንግ መጽሐፍ ቅዱሱን ማንበብ ጀመረ። የሚያነበው በቀን አንዲት መስመር ብቻ ነበር። በዚህ ምክንያት የወህኒ ቤቱ ሹሞች ሂሳቡን አስልተው ይህ ተንኮለኛ ሰው በንጉሡ ፈቃድ መሠረት መጽሐፍ ቅዱሱን አንብቦ ለመጨረስ የሚወስድበት ጊዜ ሦስት መቶ ዓመታት በመሆኑ ጉዳዩን እንደ ገና ለንጉሡ አቀረቡ። ንጉሡም በዚህ ቀልደኛና ሌባ ሰውዬ ጥበብ ተደንቀው፤ ችሎት በሚያስችሉበት ጊዜ ሁሉ በችሎቱ እየተገኘ ከተቿዎች ጋር እንዲተች አድርገው የሞት ፍርዱን ሻሩለት።

በብራዚል ሱሪናም የሚሉት እንቁራሪት አለ። ይህ እንቁራሪት ባንድ ጊዜ መቶ እንቁላል ይወልዳል። እንቁላሎቹን የሚወልደው ጀርባው ላይ ባሉት ቀዳዳዎች ነው።

በፖላንድ አገር በክራኮ ዩኒቨርስቲ አንድ የዓለምን ካርታ የያዘ ግሎፕ አለ። ግሎፑ የተሠራው ከንጹህ ወርቅ የተሠራ ነው። በዓለም ካሉት ግሎፖች ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የአሜሪካ አገር (ዓለም) የተሳለእብት ይህ ግሎፕ ነው።

በጀርመን አገር በቦን ዩኒቨርስቲ «የሰላም ንግሥት» የተባለች ቅርጽ ነበረች። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ዩኒቨርስቲው በቦምብ እንዳልነበረ ሆኖ ሲተፋ ይቺ የሰላም ንግሥት የተባለች ሐውልት ብቻ ምንም ጉዳት ሳይደርስባት ባለችበት ሥፍራ እንደ ቆመች ድናለች።

# የግብጽ አገር በጎች ጆሮ የአህያ ያህላል።

የባቫሪያው ንጉሥ ዳግማዊ ማክስ ሚላን ከልጅነታቸው ጀምረው በአምሳ ሦስት ዓመታቸው እስኪሞቱ ድረስ አንድ ጊዜ እንክኗን ፈገግ ብለው አያውቁም። ምንም ቀልድ ቢነገርና ምንም መሳቂያ ቢያሳዩዋቸው እንኳን ሊስቁና ፈገግ አይሉም ነበር። ዳግማዊ ማክስ ሚላን በ1811 ዓ.ም ተወልደው የሞቱት በ1864 ዓ.ም ነው።

የንግሥት ማርጋሬት መጽሐፍ ቅዱስ ልባሱ በ4 ማዕዘን በአልማዝ የተያዘ ነእብር። ማርጋሬት ማለት በላቲን ቋንቋ አልማዝ ማለት ስለሆነ ለስማቸው መታሰቢያ ብለው መጽሐፉን በአልማዝ አስለበዱት። (1552 – 1651)

በምዕራብ ኤንዱስ ቅዱስ ፒር በሚባል ደሴት የሚከራይ ጋሪ የሚጎተው በውሾች ነው። ውሾቹ መሆን ያለባቸው ባንድ በኩል እናቲቱ ውሻ ስትጠመድ በሌላው በኩል ልጅዋ መጠመድ አለባት።

በዓለም ካሉት ገዳሞች ሁሉ የመጀመሪያው ገዳም ነው ተብሎ የሚጠራው በላይኛው ግብጽ ኩሴይር በተባለ አምባ ያለው የቅዱስ አንቶኒዮ መቅደስ ነው። ገዳሙ በ1651 ዓ.ም በቅዱስ አንቶኒዮ የተሠራ ነው።

የግራናዳው ንጉሠ ነገሥት አብደላ ኢስ ዘግሂል ከ1485 ዓ.ም ጀምረው እስከ 1491 ዓ.ም ድረስ ግራናዳን ገዝተዋል። ግራናዳ የሚገኘው በዛሬይቱ እስፔይን ውስጥ ነው። ንጉሥ አብደላ ኢስ ዛግሃል መንግሥታቸው በአምስት ሚሊዮን የዘመኑ ወርቅ ገንዘብ ሸጡ። ይህ ገንዘብ በዛሬው በኛ ብር ሂሳብ ሲመነዘር አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር ይሆናል። ይህን ገንዘብ ከያዙ ወዲያ ለየትኛው ዓለም ብዬ እጨቃጨቃለሁ ዓለሜን አይቼ በሰላም መሞት አለብኝ ብለው ዓለምን ለማየት ተነሱ። በመጀመሪያ ወደ አፍሪካ መጥተው ብዙ አገሮችን ጎበኙ። ከፌዝ ሲደርሱ የፌዝ ንጉሥ እኚህን ሰውዬ አሠራቸው። ፌዝ ወይም አረቦች እንደሚሏት ፌስ የምትገኘው ከሞሮኮ 150 ማይል ያህል ርቃ ነው። በዚያን ዘመን የታወቀች የንግድና መናገሻ ከተማ ነበረች።

የፌዝ ንጉሥ እኚህን ለገንዘብ ብለው መንግሥታቸውን የለቀቁትን ሰው ካሠሩዋቸው በኋላ ሁለት ዓይኖቻቸውን አጥፍተው ለቀቁዋቸው። ከዚህ በኋላ እኚያ ታላቅ ሰው የልመና ተግባር ጀመሩ። የሚለምኑትም በጀርባቸው ላይ በአረብኛ የተጻፈበት ሰሌዳ ተሸክመው በመዞር ነበር። በሰሌዳው ላይ ያለው ጽሑፍ በአማርኛ ሲተረጎም «ይህ ዕድል የሌለው የግራናዳ ንጉሥ ነው» ይላል። በዚህ ዓይነት ኑሮ አሥራ ሁለት ዓመት ቆይተው ሞት ገላገላቸው።

በኖቫስትያ ይኖሩ የነበሩት ወይዘሮ ሃሪስ ሮስ በዕድሜያቸው ያገቡት ሦት ባሎች ብቻ ነው። የመጀመሪያ ባላቸውን በተወለዱ 13 ዓመታቸው አገቡ። እኚህ ባላቸው ስለሞቱባቸው ካፒቴን ብሪያንድ የተባሉትን ፈረንሳዊ አገቡ። ካፒቴኑ በ1758 ዓ.ም በሉዊስበርግ ጦርነት ሞቱ። ለሦስተኛ ጊዜ ያገቡዋቸው ባል ጀምስ ሮስ የተባሉ ሰው ናቸው። እኚህ ሴት ጀምስ ሮስን ሲያገቡ ዕድሜያቸው አንድ መቶ ሁለት ዓመት ነበር። በዚህም ዕድሜያቸው የበጎ ፈቃድ አስታማሚ ሆነው ከባላቸው ጋር በሰላም ሲኖሩ በ1860 ዓ.ም በተወለዱ በ119 ዓመታቸው በግንቦት ወር ሞቱ።

በሕንድ አገር የጎንድስ ሰዎች መሬት የሚላኩበት መሣሪያ ከየትኛውም አገር የተለየ ነው። ጃሙን የተባለ ዛፍ ቅጠሉን ይቆርጡ እና በእጃቸው ጨብጠው ቅጠሉ እደረቀበት ቦታ ድረስ ይሄዳሉ። ቅጠሉ ከደረቀበት ቦታ ሲደርስ አንድ ኮስ ይላሉ። ይህም አንድ ኮስ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል።

ሲፊልድ በተባለች አገር ልዑል የነበሩት ኧርል 6ኛ እና የሲፊልድ ልዕልት ካሮሊን በአገራቸው ላይ ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ዛፎች ተክለዋል። ኧርል በ1778 ዓ.ም ሞተዋል። የኧርል ምራት ልዕልዋት ካሮሊን ደግሞ በ1830 ዓ.ም ተወልደው ሰማንያ አንድ ዓመት ኖረው በ1911 ዓ.ም ሞቱ።

በፈረንሳይ አገር በኢስሌ ከተማ አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ ቤተ ክርስቲያኑን የሠራው ኒኮላስ ደንጎይስ የተባለ ሰው በ1670 ዓ.ም ነው። የዚህ ቤተ ክርስቲያን ሰገነት ወይም ደወል ቤት 25 ሜትር ወይም ደወል ቤት ሲሆን የተሠራው ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍሎ ነው።

ኡምብሪዮም የተባለች ደሴት አለች። የምትገኘው በምዕራባዊ ደቡብ ፓስፊክ ውቅያኖስ ነው። በዚች ሰዎች ምግባቸውን የሚበሉት በኤሊ ቅርጽ ከምግቡ ውስጥ ምንም ዓይነት መርዝ ቢጨመር ይህ የመመገቢያ ሰሃን መርዙን ያጠፋዋል።

በጀርመን አገር በአይኸን ካቴድራል የቻልማኝ ሐውልት አለ። የሐውልቱ ጭንቅላት ከራሱ ከቻርልማኝ ጭንቅላት የተሰራ ነው።

በስፔይን ውስጥ የቶሎዶ ካቴድራል የተሠራው በወርቅ ነው። ይህም ወርቅ ኮሎምበስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአሜሪካ በ1943 ዓ.ም ያመጣው ነው። ወርቁንም ለካቴድራሉ ማሠሪያ የሰጡት ንግሥት ኢሳቤላ ናቸው።

27ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዊልያም ሆዋርድ ታፍት ለመጀመሪያ ጊዜ ተመርጠው የአሜሪካ ቃለ መሐላቸውን ሲፈጽሙ ክብደታቸው 332 ፓውንድ ነበር።

ንብ አስደናቂ አፈጣጠር ያላት ፍጡር ናት። አምስት ዓይኖች አሏት። አምስት የአፍንጫ ቀዳዳዎች አሏት። ክንፍዋ በአንድ ደቂቃ 11.400 ጊዜ ይርገበገባል። አንዲት ፓውንድ የምትመዝን ማር ለማግኘት 50.000 ማይል ትጓዛለች። ይህም ቢተረተር የመሬትን ዙርያ ሁለት ጊዜ መዞር ማለት ነው። የማትሰማና ቀይ አበባ ማየት የማትችል ናት።

የፈረንሳይ ንጉሥ ቀዳማዊ ፊሊፕ ታመው ሳለ ወዳጃቸው ቻሎ ማርክ እንዲድኑለት ተሳለ ስለቱም ኢየሩሳሌም ድረስ ሻማ አብርቶ ሂዶ በጌታ መቃብር ላይ አስቀምጦ በእግሩ እንደሄደ በእግሩ ለመመለስ ነበር። ንጉሡ ዳኑ። ማርክ እንደ ተሳለው የጦር ብረት ልብሱን ለብሶ፤ ሻማውን አብርቶ የኢየሩሳሌም ጉዞውን በእግሩ ጀመረ። ባሕር ሲያቋርጥ ብቻ በመርከብ ከመሳፈር በስተቀር ሌላውን መንገድ በእግሩ እየተጓዘ ሻማውን እንዳበራ ከኢየሩሳሌም ደርሶ በእግሩ ተመለሰ።

እስካሁን ድረስ የሃይማኖት ሰዎች ካደረጉት የእግር ጉዞ ሁሉ የማርክን የሚወዳደር የለም። በዚህም ተግባሩ ዘሩ በሙሉ ለፈረንሳይ መንግሥት ግብር እንዳይከፍል በመደረጉ ለብዙ መቶ ዓመታት ዘሮቹ ለፈረንሳይ መንግሥት ግብር ሳይከፍሉ በነፃ ኖረዋል።

ግማሽ ማይል ኩብ የሆነ ዕቃ የዓለምን ሕዝብ ጠቅለልሎ ሊይዝ ይችላል። በያንዳንዱ መዓዘን ግማሽ ማይል የሆነ ነገር 18.399.744.000 ኩብ ጫማ ይሆናል። ላንድ ሰው ስድስት ቻማ ርዝመት ሁለት ጫማ ስፋት ያለው ቦታ ቢደለድለው በዚያ ዕቃ ውስጥ 1.500.000.000 ሊኖሩ ይችላሉ ማለት ነው።

በአሜሪካ አገር 13 ቁጥር ገደቢስ ነው። ለምንም ነገር መለያ አይደረግም። የሆቴል ቤትም ሆነ የሆስፒታል ወይም በሌላ ነገር ላይ አይውልም ገደቢስ ነው ብለው ስለሚያምኑበት ነው ግን የአሜሪካ መንግሥት ታላቁ ማኅተም

13 ከዋክብት አሉበት።

13 ሰማያዊና ነጭ መስመር።

13 ቀስቶች አሞራው ይዟል።

13 ደመናዎች ከአሞራው ራስ ላይ

13 ፊደሎች አሞራው በአፉ በያዘው ወረቀት ላይ፤

13 ቅጠሎች በአሞራው እጅ ውስጥ፤

13 ፍሬዎች አሞራው በያዛቸው ቅጠሎች ላይ፤

13 ላባዎች በአሞራው ግራ ክንፍ፤

13 ላባዎች በአሞራው ቀኝ ክፍን፤

13 ላባዎች በአሞራው ጭራ ላይ አሉባቸው። ታዲያ እንዴት ገደ ቢስ ሊሆን ይችላል?

እኚህ የታደሉ ታላቅ ወይዘሮ ማርያ ላቲታ ራሞሊኖ ይባላሉ። በ1750 ዓ.ም ኮርሲካ በተባለች ደሴት ተወለዱ። ላቅመ ሄዋን ሲደርሱም ካርሎ ባናፖርቴ የተባለውን ሰው አገቡ። ከእኚህ ባላቸው አሥራ ሦስት ልጆች ወለዱ። አሥራ ሦስቱንም ልጆቻቸውን እግዚአብሔር ባርኮላቸው ከታላላቅ ቦታ ዋሉላቸው። አንዱ ልጃቸው ዝነኛው ፖሊዮን ቦናፓርት ነው። ጆሴፍ የተባለው ትልቁ ልጃቸው የስፔይን ንጉሥ ነገሥት ሆነ። ጀሮሜ እና ሉዊስ የተባሉት ሁለት ልጆቻቸው አንዱ የዌስትፋልያ የሆላንድ ንጉሥ ሆነ። ደግሞ የሆላንድ ንጉሥ ሆነ። የውለዱዋቸው አራቱ ልጆች ወንዶች ሁሉም ንጉሦች ሲሆኑ ከሴቶቹ ደግሞ ማርያ ኡኒቹታ ካሮሊና የኦፓል ንግሥት ሆነች። እህቷ ኤሊሳ የቶስካና ንግሥት ሆነች። ሉስኒ እና ማርያ ፓውሊን የካኒኖን የቶስካና ንግሥት ሆነች። ሉስኒ እና ማርያ ፓውሊን የካኒኖን ልዑልና የጉስታላን ልዑላን አግብተው ልዕልት ተባሉ። እነኚህ ልጆቻቸው ሁሉ የነገሡላቸው ሴት

የልጆቻቸውን የንግሥና ዘመን ሃያ ዓመታት ሙሉ ካዩ በኋላ ዕድሜ ጠግበው በተወለዱ በ86 ዓመታቸው በ1836 ዓ.ም በክብር ሞቱ።

በእንግሊዝ አገር ፊቸር ፊልድ በተባለ ቦታ በአሥራ ሁለት ሐዋርያት አምሳል 12 ዛፎች ዙርያ ክብ ሆነው ተተክለው ነበር። ዛፎቹ በያንዳንዱ ሐዋርያ ስም ተሰይመው ተተከሉ አሥራ አንዱ ዛፎች ጥሩ ሆነው ሲያድጉ በይሁዳ ስም የተሰየመው አሥራ ሁለተኛው ዛፍ ካደገ በኋላ ነፋስ መንግሎ ጣለው።

ሺቦሌት ማለት ያቅታል? ሺቦሌት ማለት አቅቷቸው 42.000 ሰዎች መገደላቸውን ያውቃሉ? ካላወቁ መስሐፍ ቅዱስዎን ያውጡ። ዘመሳፍንት ምዕራፍ 12 ቁጥር 5 እና 6 ቢያነቡ እንዲህ ይላል «የጊልዓድም ሰዎች ኤፍሬም የሚያልፍበትን የዮርዳኖስን መሻገሪያ ያዙ። የሸሹትም የኤፍሬም ሰዎች እናልፋለን ባሉ ጊዜ የጊልዓድም ሰዎች አሉዋቸው። አንተ የኤፍሬም ወገን ነህ? እርሱም መለስ አይደለሁምና እርሳቸውም አሉት አሁን ሺቦሌት በል፤ ሲቦሌትም ይል ነበር። አጥርቶም መናገር አልሆነለትም ወሰደውም በዮርዳኖስ መሻገሪያ አረዱት። በዚያም ጊዜ ከኤፍሬም 42.000 ሰዎች አለቁ።

ታላቁ የታወቁት አሜሪካዊ ፈላስፋ በኢንጃሚን ፍራንክሊን እጅግ በጣም ብሩህ አእምሮ የነበራቸው ሰው ነበሩ። ከሥራቸው ጥቂቱን ለመዘርዘር ያህል የመጀመሪያው የአሜሪካ ሥልጣኔ መሥራች ናቸው። የመጀመሪያው የአሜሪካ ፈላስፋ፤ የመጀመሪያው አሜርካ የላከቻቸው አምባሳደር፤ ሐርሞኒካ የፈለሰፉ፤ የመጀመሪያውን ተወዛዋዥ ወንበር የፈለሰፉ የመጀመሪያውን የፖለቲካ ካርቶን ያወጡ፤ በሀ ዋና ተወዳዳሪ ያልነበራቸው፤ የመጀመሪያውን የቤተ መጻሕፍት ስነ ሥርዓት ያወጡ፤ የመጀመሪያውን የሙብረቅ መከላከያ የሠሩ በፔንስቫልንያ ለአራት ጊዜ ፕሬዝዳንትነት የተመረጡ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ጋዜጣን በፖስታ መላክ እንደሚቻል ያወጡና የጀመሩ፤ (መጀመሪያውን የኤሌክትሪክ ብርሃን ያወጡ፤) የመጀመሪያውን የንግድ ማስታወቂያ ያወጡ፤

አየር እንዴት ለመመረዝ እንደሚችል ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳወቁ፤ የመጀመሪያውን የእሳት አደጋ መከላከያ ድርጅት ያቋቋሙ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የዲሞክራሲን ፓርቲ የመሠረቱ፤ የፖስታ ቤትን ይዞታና አሠራር በሚገባ ያቋቋሙ፤ የጋዝ ምድጃን የፈለሰፉ፤ በቆላ አገር ነጭ ልብስ ለፀሐይ መከላከያ እንደሚሆን ያሳወቁ፤ የፕሬዝዳንትም ሆነ የእንደራሴ ምርጫ ሥነ ሥርዓትን ያወጡ፤ የጉንፋንን አመጣጥ ያሳወቁ፤ የአየር ማመንጫን (ቬንትሌተር) ለመጀመሪያ ጊዜ የፈለሰፉ፤ የመሬት ማዳበሪያን ያወጡ ታላቅ ሰው ናቸው። እኚህ ሰው በጠቅላላው አንድ ሺ ሶስት መቶ ዓይነት ነገሮችን ፈልስፈው ለዓለም አበርክተዋል። ቤንጃሚን ፍራንክሊን በ1706 ዓ.ም ከአንድ ድሀ ቤተሰብ የተወለዱ ሰው ናቸው። ቤንጃሚን ፍራንክሊን ይቺን ዓለም ሠርተውባትና ሠርተውላት በ1790 ዓ.ም በሞት ይቺን ዓለም ተለዩዋት። ዓለምም ትልቅ ጠቃሚዋን አጣች።

አንድ ባንል ለገንዘብ አስቀማጮች በመቶ 4 ሂሳብ ወለድ ቢከፍልና ሲያድር ደግሞ በመቶ ስድስት ወለድ ቢያስከፍል የባንኩ ትርፍ ስንት እንደሆነ ያውቃል? ስንጥቅ ነው። 50% ያተርፋል።

በፈረንሳይ አገር የቬርሳልዝ መስፍን ባለቤት የነበሩት ማዳም ሬኚር በማኩረፍ ተወዳዳሪ የሌላቸው ሴት ናቸው። በ1842 ዓ.ም ከባለቤታቸው ጋር ሲጫወቱ ባልዮው «እባክሽ ዝም በይ፤ በሁሉ ነገር ጥቅል አትበይ» አሏቸው። እኚህ ሴት በዚህ ንግግር ያኮረፉ በ1872 ዓ.ም እስከሚሞቱበት ጊዜ ድረስ አንዲትም ቃል ሳይናገሩ ኖሩ። የልጃቸው ሠርግ ተደግሶ ሲበላ ሲጠጣ እንኳን እንዲናገሩና እንዲጫወቱ ባልዮውና ብዙ ሰዎች ቢለምኗቸው ፈጽሞ አልተናገሩም። ሙሽራይቱ ልጃቸው እያለቀሰች ስትስማቸው ብቻ አንድ ጊዜ ውይ ሲሉ ተሰሙ።

ዝነኛው የቻይና አጭር ፍጡር አቶ ቺ ማህ ቁመቱ 71 ሳንቲ ሜትር ነበር። የጠጉሩ ርዝመት ግን ዘጠኝ ክንድ ነበር።

አሜሪካኖች አርብ ዕለት ዕድለ ቢስ ነው ይሉታል። አርብን ሲነጫነጩ ነው የሚውሉበት። ምንም ነገር ባያጋጥማቸው እንኳን አርብን ዛሬ መጥፎ ቀን ነው ሲሉ ይውላሉ። ግን ታላቁ ፕሬዚዳንታቸው ጆርጅ ዋሺንግተን በአርብ የተከበቡ ሰው ነበሩ።

ጆርጅ ዋሽንግተን አርብ ዕለት ተወለዱ። አርብ ዕለት ሌተና ኮለኔል ተባሉ። አርብ ዕለት የቪርጂኒያ ጦር ሠራዊት አዛዥ ሆኑ። አርብ ዕለት የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ ሆነው ተመረጡ። አርብ ዕለት የአሜሪካን የባሕር ኃይል መሠረቱ። የፕሪስተን ጦርነት አርብ ዕለት ድል አደረጉ። ዮርክታውንንም ድል ያደረጉት አርብ ዕለት ነው። አርብ ዕለት የአሜሪካ መንግሥት የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ። የአሜሪካን ጦር ሚኒስቴር አርብ ዕለት መሠረቱ። አርብ ዕለት የመጀመሪያውን የካቢኔ ሹማቸውን አሌክሳንደር ሐሚልተንን ሾሙ። አርብ ዕለት የፌደራሉን ዋና ከተማ መሠረቱ። አርብ ዕለት የዋይት ሐውስ ቤተ መንግሥትን የመሠረት ድንጋይ አኖሩ። አርብ ዕለት የፕሬዝዳንትነት ሥልታናቸው አለቀ።

ከ1688 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1747 ዓ.ም ድረስ ፔርሺያን የገዙት ናዲር ሻህ ሰፊውን ግዛታቸውን ለመጎብኘት በብዙ አጀብ ታጅበው ጉዞ ጀመሩ። ናዲር ከፔርሺያ አልፈው ከአሁኑ የሕንድ ግዛትው ስጥ ሁሉ ይገዙ ነበርና በሕንድ ውስጥ በምትገኘው ናር ከምትባለው አገር ደረሱ። በዚያች አገር በመንገድ ሲያልፉ አንድ ባኑቺ የተባለ የሕንድ ገበሬ የናዲርን አጀብና የጦር ሠራዊት ፈርቶ እስኪያልፉለት ድረስ ካንዲት ዛፍ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ናዲር በዚያ ዛፍ አጠገብ ድንኳን እንዲተከልላቸውና አዳር ከዚያም እንዲሆን አዘዙ። እንዳዘዙትም ሆነ። ያ ድሀ ገበሬ ካለበት ዛፍ ሥር የናዲር ወይዛዝርት እንዲያርፉ ተደረገ። በዚህ ጊዜ ገበሬው ባኑቺ ተንቀጠቀጠ። ከመፍራቱና ከመንዘፍዘፉ የተነሳ ሲርበደበድ ሴቶቹ ቀና ብለው አዩት። ወዲያውኑ ተጯጯሁ። ናዲርም ደከሟቸው ተኝተው ነበርና ጩኸቱን ሰምተው ከመኝታቸው ተነስተው ወጡ። ከዚህ በኋላ ያ ድሀ ገበሬ

ከዛፉ ላይ ወርዶ በእንብርኩ እየሄደ ከንጉሥ ነገሥቱ ናዲር ፊት ቀርቦ የፍርሃቱን ይዘላብድ ጀመር። በዚህ ጊዜ ንጉሥ ነገሥቱ በባኑቺ ሁኔታ ስቀው ዛፉ ሥር አርፈው የነበሩትን 33 ቁባቶቻቸውን ለዚያ ድሀ ገበሬ በሚስትነት ሰጡት ከዚህም ሌላ በሕንድ አገር ያላቸውን ግዛትም ከእሳቸው ሥር ሆኖ ባኑ ማስጌጫ ያ ብዙ አልማዝና ወርቅ፤ ለማስተዳደሪያው ብር፤ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ባሮችም ጨምረው ሰጡት። እንዲህ ዓይነቱ ዕዳ ከሜዳ ይባላል ወይስ ዕድል ከሜዳ?

በአሜሪካ አገር በኒውዮርክ ከተማ የአቶ ጀምስ አስችዋርት ውሻ በጀርባዋ ላይ የጥቁር ድመት ዓይነት ስዕል ተስሎበት ተወልዷል። ይህም ስዕል እስከ ውሻው ዕድሜ ፍጻሜ ድረስ ሳይጠፋ ቆይቷል።

በ1816 ዓ.ም ተወልደው በ1891 ዓ.ም የሞቱት ሰር ጆን ሮበርት ሰን በአውስትራሊያ የኒውሳውት ዌስል አምስት ጊዜ እየተመረጡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነዋል። እኚህ ሰው 35 ዓመት ሙሉ ባለማቋረጥ ጧት ጧት ሦስት ብርጭቆ ሩም ይገዙ ነበር። ይህንንም በየቀኑ የሚገዙትን 3 ብርጭቆ ሩም አንዱን ብርጭቆ ሩም እሳቸው ይጠጡታል። አንዱን ብርጭቆ ፈረሳቸውን ያጠጡታል። አንዱን ብርጭቆ ሩም ከጫማቸው ውስጥ ከእግራቸው ላይ ያፈሱታል። እኚህ ጠቅላይ ሚኒስትር የቁርጥማት በሽታ ስለ ነበረባቸው፤ ሩሙ የእግራቸውን ቁርጥማት እንደሚያሽላቸው ያምኑ ነበር በዚህ በሰላሳ አምስት ዓመት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የገዙት ሩም ከሰላሳ ስምንት ሺ ብርጭቆ በላይ መሆኑ ነው።

በ1690 ዓ.ም የተወለዱት ጀኢን ማርቆስ በ1766 ዓ.ም ሞቱ። ልጃቸው አባቱ ከሞቱበት ቀን ጀምሮ በፈረንሳይ አገር ያለውን የሬስ የሚባለውን ጅረት አሽከሮቹ በየቀኑ ጥቁር ቅለም እንዲጨምሩበት አዘዘ። ይህ ጅረት በፈረንሳይ አገር የታወቀችውን ቡርኖይ የተባለችውን ከተማ አቋርጦ የሚሄድ ነው። ጂን ማርቆስ የሞቱበት የመስከረም ወር በሙሉ በወንዙ ላይ በየቀኑ ጥቁር ቀለም በመፍሰሱ ወንዙ በጥቁር ቀለም ተበከለ። የወንዙ መበለክም፤ ዛፎችን

ድንጋዮችን፤ እንዲያውም አንድ ጊዜ ገንፍሎ ወደ ከተማው በመግባቱ በከተማው ውስጥ ያሉትን ቤቶችና ሐውልቶችን ሁሉ በጥቁር ቀለም ስለቀባቸው የቡርኖይ ከተማና አካባቢዋ ሁሉ አንድ ወር በግዴታ ጥቁር ቀለም በመቀባት ለሟቹ ልጇን ማርቆስ ከል ለብሳ ከረመች።

የታወቀው ፈረንሳዊ ባለ ቅኔ አሶስት ብሪዜክስ ስለራሱ ሲቀኝ «እናንት ወጣቶች! በመቃብሬ ላይ አንድ ዛፍ ትከሉ! በዛፉም ላይ ወፎች ዕይሰፈሩ ሁሉ ይዘምሩልኝ» ብሎ ነበርና በ1858 ዓ.ም ሞቶ ሲቀበር ያቺን ቅኔውን አስታውሰው ቀባሪዎቹ አንድ ዛፍ ተከሉለት። በፈረንሳይ አገር በሎሬንት ባለው መቃብሩ የተተከለው ዛፍ አድጎ ወፎች በላዩ ላይ ጎጆአቸውን ሠርተው ዘወትር ይንጫጩ ጀመር።

በ1701 ዓ.ም ተወልደው በ1762 ዓ.ም የሞቱት የቻይናው ንጉሠ እንገሥት ሚንግ ሁአንግ በዓለም የሚደነቁበት አንድ የግጥም ድርሰት አላቸው። ይህ የግጥም ድርሰት የንጉሠ ነገሥቱ ሳይሆን ሊ.ታይፖ የተባለ የቻይናዊ ሰው ቅኔ ነው።

ሊ ከመጠን በላይ የወይን ጠጅ መጠጣትና ሴቶችን ያፈቅር ስለ ነበረ ሞቅ ባለውና ሴቶችን ባገኘ ጊዜ ቅኔ መቀኘት ይሆንለት ነበር። ይህንንኑ ቅኔውን በወረቀት ላይ ስለሚያሰፍረው ይህ ሲሰክር ብቻ የሚቀኘው ቅኔ የትም ባክኖ እንዳይቀር ንጉሠ ነገሥቱ የሊ ጸሐፊ ለመሆን አሰቡ። በዚህም ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ሊ የፈለገውን ያህል ወይን ጠጅ እንዲጠጣና ከአጠገባቸው እንዲሆን እያደረጉ ሊ የሚቀኘውን ቅኔ ይጽፉለት ጀመር። እኚህ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ሚንግ ሁአንግ፤ የሊን ቅኔዎች በሙሉ ጽፈው ለትውልድ በሙሉ ጽፈው ለትውልድ ስላቆዩ የዛሬው የቻይና ሕዝብ ያመሠግናቸዋል። ሊ ይሄው ስካሩ አለቅ ብሎት ሲኖር አንድ ቀን በባሕር ላይ እየተንሸራሸረ በጨረቃዋ ብርሃን ተደስቶ ሲቀኝ በባሕሩ ላይ ያለችውን የጨረቃ ምስል እስማለሁ ብሎ ሲያጎነብስ ከጀልባዋ ላይ ተገልብጦ ሞተ።

በ1607 ዓ.ም የተወለዱት ፈረንሳዊቷ ወይዘሮ ኤስልሳቤጥ በአሜሪካ አገር የሴንሊስ አገረ ገዥ የነበሩትን ሰው በተወለዱ በሃያ ዓመታቸው አገቡዋቸው እንዳጋጣሚ ሆኖ በተጋቡ ሰሞን ባልዮው ሞቱ። ባልዮው ቀናተኛ ነበሩና ሲናዘዙ «ሚስቱ ባል ሳታገባ በቆየችበት ጊዜ ሁሉ በሚከተለው አኳኋን ከሀብቴ ላይ ገንዘብ እየተነሳ እንዲከፈላት። ይሄውም በመጀመሪያው ዓመት አንድ የወርቅ ገንዘብ በሚቀጥለው ዓመት ሁለት፤ በሦስተኛው ዓመት ደግሞ የዚያ አጠፌታ፤ በአራተኛው ዓመት የሦስተኛው ዓመት ክፍያ አጠፌታ፤ እየተደረገ እንዲሰጣት» ብለው ተናዘዙ። ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ይቺን ኑዛዜ ካገኙ በኋላ 69 ዓመት ሙሉ ባል ሳያገቡ ተቀመጡ። በ1696 ዓ.ም እኚህ ሴት በሞቱበት ጊዜ ያገኙት ያንደኛው ዓመት ክፍያ ብቻ 147.573.952.314.798.506.112 የወርቅ ገንዘብ ነበር። ይህ በመጨረሻው በሚሞቱበት ዓመት ብቻ ያገኙት ያንድ ዓመት ክፍያቸው አሁን እኔ በነበርኩበት ዘመን ባለው የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ሲመነዘር አንድ ሴክስትሊዮን 842 ኳትሊዮን፤ አምሳ ኳድርሊዮን ይሆናል። ባጭሩ አንድ መኪና ሙሉ ጠጠር እንደመቁጠር ነው። የወይዘሮ ኤልሳቤጥ ሽማልጌ ባል ሲናዘዙ ሂሳቡ እንዲህ የሚመጣ አልመሰላቸውም ነበር።

በአሜሪካ አገር ቀድምቲቱ ሠልጣኝ አገር ቦስቶን ናት በአሜሪካ አገር የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን የተሠራው፤ የመጀመሪያው ነፃ ትምህርት ቤት የተከፈተው፤ የመጀመሪያው ኮሌጅ የተቋቋመው የመጀመሪያው የመርከብ ፋብሪካ፤ የመጀመሪያው ማተሚያ ቤት፤ የመጀመሪያው የአሜሪካ አገር ጋዜጣ፤ የመጀመሪያው ሆቴል፤ የመጀመሪያው የባቡር ሐዲድ መንገድ፤ የመጀመሪያው የሕዝብ መናፈሻ፤ የመጀመሪያው የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ፤ የመጀመሪያው የጋዝ መብራት፤ የመጀመሪያው ፖስታ ቤት፤ የመጀመሪያው ባንክ የተቋቋመው በዚችው በቦስተን ነው ቦስተን ከአሜሪካ ከተሞች ሁሉ ብዙውን ነገር ለመጀመሪያ የመጀመሪያይቱ ናት።

በቫቲካን ከተማ የቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር አለ። ይህ ወንበር ለሕዝብ እንዲታይ የሚፈቀደው በመቶ ዓመት ጊዜ ብቻ ነው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 1015 ዓመት ሄርሞን ኦኔል የተባለ ሽፍታ ሰው አይርላንድን ግዛቱ ለማድረግ ተነሳ። ቬኪንግ የተባለ ሌላ የሽፍታ አለቃ ድግሞ ይቺኑ አይርላንድን ግዛቱ ለማድረግ ተነሳ። እነዚህ ሁለት የሽፍታ አለቆች በዚች አገር ምክንያት ከመዋጋት ይልቅ መጀመሪያ ተጉዞ የአገሪቱን አፈር ቀድሞ የነካ ሰው ይንገሥባት ብለው ተስማሙ ከዚህ በኋላ ሁለቱም የሽፍታ አለቆች በየጀልባቸው ሆነው አለቆች በየጀልባቸው ሆነው ሠራዊታቸውን እያስነዱ ወደ አይርላንድ ጉዞ አደረጉ። ከመሬቲቱ ላይ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው የኦኔል ጀልባ ነጂዎች ደከመው የቬኪንግ ጀልባ ቀድማ ልትደርስ ሆነ። በዚህ ሁኔታ የተናደደው ኦኔል የቀኝ እጁን በሰይፍ ቆርጦ ከጀርባው ወደ መሬት በመወርወር «እጄ ቀድሞ የአገሪቱን አፈር ነክቷልና ቅድሚያው የኔ ነው» በማለት ረታ።

በአሜሪካ አገር በቴክሳስ ይኖሩ የነበሩት አቶ ሄንሪ ዚግላንድ አንዲት ወዳጃቸውን ገድለዋል ተብለው ተጠረጠሩ። በዚህ ጥሩጣሬ መሐል የሟቹ ሴት ወንድማ ቶ ዚግላንድን ለመግደል ሲጠባበቅ አንድ ቀን ካንድ ጫካ ውስጥ አግኝቶ ጥይት ተኩሶ መታቸው። እንደመታቸውም የሞቱ መስሎት አገር ጥሎ ሄደ። ጥይቲቱ ግን የአቶ ዚግላንድን ጉንጭ ጨርፋ ካንድ ዛፍ ውስጥ ተሽጉጣ ነበር። በ1913 ዓ፣ን አቶ ዚግላንድ ያንን ዛፍ ሲቆርጡ ጀመረው ስለደካማቸው ድማሚት አፈነዱበት። በዚህ ጊዜ ያቺ ጥይት በድማሚት ኃይል ተወርዋሪ አቶ ዚንግላንድ ከቅጸበት ገደለቻቸው።

በዩጎዝላቪያ ውስጥ ኤሎክ በተባለች ከተማ አንዲት ሴት አንድ መቶ ዓመት ሙሉ ያለማቋረጥ በየቀኑ በከተማው ውስጥ እየዞሩ በርበሬ ሸጠዋል።

በ1360 ዓ.ም ተወልደው በ1424 ዓ.ም የሞቱት የቻይናው ንጉሠ ነገሥት ዩንግ ሎ አንድ ሊንግ ዌን የተባለ ሰው ከፊታቸው ቀርቦ ስለ ሰደባቸው አንገቱ

በመጥረቢያ ተቆርጦ እንዲገደል ፈረዱበት። ሊንግ ዌን ወደ መቆረጫው ሥፍራ ተይዞ ሲሄድ አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች «ከንጉሡ እናማልድህና ይቅርታ ጠይቅ» ቢሉት «እኔ ንጉሡን የተናገርኩት እውነተኛውን ነገር እንጂ ስድብ አይደለምን። ይህንንም ነገር በሞቴም ጊዜ ቢሆን በደሜ እጽፈዋለሁ» በማለት ሽማግሌዎቹን እምቢ ብሎ ወደ መቆረጫው ሥፍራ ሄደ። በዚያም አንገቱን በመጥረቢያ ሲቆረጥ ከአንገቱ ላይ የወረደው ደም በቻይንኛ ቋንቋ ያንኑ ቀድሞ የተናገረውን «ፍርድ ገምድል» የሚል ቃል ተጻፈ።

ሃሮልድ ፓርክኸርስት የተባለ ሰው ሃያ ሺ ጫማ ከፍታ ካለው የአየር ላይ በፓራሹት ሲወርድ ፓራሹቱን ከመክፈቱ በፊት ክብሪትና ሲጃራ ከኪሱ አውጥቶ ያያይዛል። ጉንጩን ሳሙና ቀብቶ ጢሙን ይላጫል። ይህን ሁሉ አድርጎ እስኪያጋምስ ፓራሹቱን አይከፍትም ነበር።

የኡጋንዳው ንጉሡ ሙቴሳ እናት ንግሥት ናማሶሌ ጥርሳቸውን ከፉኛ ታመሙ። የአገራቸውን መድኃኒት አዋቂዎች አስጠርተው ቢጠይቱ «የሹማ አውራጃ ሰዎች ቢገደሉ የጥርስ ሕመምዎ ይተዎታል ያለዚያ አይድኑም» አሏቸው። ንግሥቲቱ ይህን እንደ ሰሙ ሃያ አምስት ሺ ሰዎች ከቪክቶሪያ ሐይቅ ውስጥ በማስጨመር አስገደሉ። የንግሥቲቱ ታሪክ በዚህ ሳቢያ ጥርሳቸው መዳን ያለመዳኑን አይናገርም። እነኛም መድኃኒት አዋቂዎች ነን ባዮች ከሹማ ሰዎች ጋር ጠላትነት እንዳላቸው አይገልጽም።

ወይዘሮ አሊቬቲ ቬሮኖን ፈረንሳዮች ከአልጄሪያውን ጋር በሚያደርጉበት ጦርነት ውስጥ ባላቸው ሞቱባቸው። እኚህ ሴት ባላቸውን በጣም አድርገው ይወዱ ስለ ነበር የባላቸውን የጦር ልብስና የጦር መሣሪያ በሙሉ አንግበውና ለብሰው እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ሰላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ሳያወልቁት ኖረዋል።

«እነሆ እኔ ከዚያ በፊትህ እቆማለሁ፤ በኮሬብ ድንጋይ ላይ። ደንጊያውንም ትመታለህ፤ ከእርሱው ውሀ ይወጣል ሕዝቡ ይጠጣ ዘንድ። ሙሴም እንዲህ

አደረገ። በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት።» አሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፲፯ ቁጥር ፯።
ይህ ሙሴ ውሀ ያወጣበት ድንጋይ እስከ ዛሬ ድረስ አለ። ያለው ድንጋዩ ብቻ ሳይሆን ከሥሩ የጠራ ውሀ እስከዛሬ ይፈሳል። አንድ ተመራማሪ ሰው ከዚህ ውሀ ጠጥተው እንደጻፉት «ውሀው ዛሬም ቢሆን ገና ትኩስ ውሀ ይመስላል። እሥራኤሎቹ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1491 ዓመት የጠጡት ውሀ እኔም ዛሬ ከክርስቶስ ከሦስት ሺ አራት መቶ ሃያ ሰባት ዓመት በኋላ ስጠጣው ጣዕሙ እጅግ በጣም ይጣፍጥ ነበር» ብለዋል።

የስኮትላንዱ ሰር ዊልያም ኒኮልሰን በተወለዱ በ93 ዓመታቸው ልጅ አስወልደዋል። የመጀመሪያ ልጃቸው ዕድሜ 66 ዓመት ሲሆን ሰር ዊልያም የመጨረሻ ልጃቸውን አስወለዱ። ሰር ዊልያም በ1673 ዓ.ም ተወልደው በ1766 ዓ.ም ሞቱ።

በአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የእንግሊዝ ሴቶች ምንም ዓይነት ደብዳቤ በሚጽፉት በፈረንሳዊኛ እንጂ የእንግሊዝኛ አይጽፉም ነበር። በ1899 ዓ.ም ሐምሌ 25 ቀን ወይዘሮ ጆን ፌላም የተባሉ ሴት ለፊታቸው ባላቸው ደብዳቤ ሲጽፉ በእንግሊዝኛ ቃላት በመጻፋቸው በእንግሊዝ የሴቶች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዪቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንግሊዝኛ ደብዳቤ ጸሐፊ ናቸው።

ወይዘሮ ሜሪ አን ፊትዘርበት ሞተው ሲቀበሩ የግራ እጃቸው ከመቃብሩ በላይ ውሎ በቀለበት ጣታቸው ላይ ሦስት ቀለበቶች ተደርገውበት ተቀበሩ እነኚህ ቀለበቶች የተደረጉበት ምክንያት ለሦስት ባሎቻቸው መታሰቢያ ነው ከነዚህ ሦስት ባሎቻቸው አንዱ ንጉሥ ጆርጅ አራተኛ ናቸው። ወይዘሮ ሜሪ የተቀበሩት በእንግሊዝ አገር ብሪግተን ከተባለው ቀበሌ ነው።

በ1757 ዓ.ም በስኮትላንድ አገር ቶማስ ቴልፎርድ ተወለደ። ቶማስ ቴልፎርድ የሞተው በ1834 ዓ.ም ነው። ቶማስ በአሥራ ስምንት ዓመት ጊዜ

ውስጥ 1117 ድልድዮችና አንድ ሺ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸውን መንገዶች በስኮትላንድ ውስጥ ሠርቷል።

በኢጣልያ አገር ሀቪሮና አንድ ሕንፃ አለ። በዚህ ሕንፃ ላይ ባለው በረንዳ ዡልየት ቆማ ከሮሚዮ ጋር የተነጋገረችበት ነው።

በሕንድ አገር ጉራሚ የሚሉት አሣ አለ። ይህ አሣ እንደሌሎቹ አሣዎች ሁሉ በውሀ ውስጥ ብዙ መቆየት አይችልም። ስለዚህ ከውሀው ውስጥ ራሱን ብቅ በማድረግ አየር ከሳበ በኋላ ተመልሶ ወደ ውሀው ውስጥ ይገባል። ጥቂት ቆይቶም እንደገና ይወጣና አየር ስቦ ይገባል።

ጆን ፊልዝ ደ ሮይ ደ ፍራንስ ደ ብራይ በያንዳንዱ የመጠሪያ ስማቸው ፊደል አንዳንድ ቤት መንግሥት አሠሩ። የስማቸው ፊደል 31 ነበረ። የኚህ ሰው ስም በፈረንጅኛው ሲጻፍ JEJAM FO;Z DE ROY DE FRANCE DUC BRRY ነው እኚህ መሥፍን የፈረንሳዩ ንጉሥ ቻርልስ ፭ኛ ወንድም ናቸው። መሥፍኑ በ1340 ዓ.ም ተወልደው የሞቱት በ1416 ዓ.ም ነው።

በ2300 ዓመታት በፊት በቻይና አገር በንጉሠ ነገሥት በኦ ፋንግ ቤተ መንግሥት መግቢያ በር ላይ ለሰው የተሠራው በር እንደፋካ የተድበለበለ ነው። ይህ በር የተሠራው ከማግኔት ብረት ነበር። አንድ ሰው ምንም ዓይነት መሣሪያ በልብሱ ውስጥ ደብቆ ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ለመግባት ቢፈልግ መሣሪያው ካለበት በኩል ማግኔቱ ሰውዬውን ስቦ ከግድግዳው ጋር ያጣብቀዋል።

በጊኒያ ወርቃማ ወፍ የምትባል ወፍ አለች። ይቺ ወፍ የምትገኘው የወርቅ ማዕድን ባለበት ቦታ ብቻ ነው። ወፍዋ በተገኘችበት ቦታ ሁሉ ማዕድን ቆፋሪዎች እየተከታተሉዋት መሬቱን ሲቆፍሩ ወርቅ ያገኛሉ። በዚህ ምክንያት የወፍዋን ስም ወርቃማዋ ወፍ ይሏታል።

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጃቫና የማላያ ሰዎች ለጦርነት ተሰላለፉ። የሁለቱም ጦር ሠራዊቶች የሚያስፈሩ የጦር መሣሪያዎች ይዘው ፊት ለፊት ቆሙ። የሁለቱም ወገኖች የጦር አለቆቻቸውን ትእዛዝ ይጠባበቁ ነበር። በኋላ የሁለቱም ወገን የጦር አዛዦች በአንድ አሳብ ተስማሙ። ይሄውም ስምምነት ሠራዊቱ ከሚተላለቅ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ጎሽ አቅርበው ሊያዋጉና የተሸነፈው ጎሽ ወገን እንደተሸነፈ ተቆጥሮ የተጣሉበትን የግዛት ድንበር እንዲለቅ የሚል ነበር። ሁለቱም ወገኖች ሁለት ጎሾች አቀረቡ። ጎሾቹ ውጊያ ጀመሩ። አንደኛው ጎሽ አንደኛውን እየገፋ ሲሄድ ወታደሮቹ ዝም ብለው በመከተል ውጊያውን ያበረታቱ ጀመር። በመጨረሻው የጃቫ ሰዎች ያቀረቡት ጎሽ ደክሞት ሞተ። ከዚህ በኋላ በስምምነቱ መሠረት ሱማትራ የማልያ ግዛት ሆነች። የውጊያውም ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ ሜናንግካባው ተባለ። ይህም ማለት የጎሽ ድል ማለት ነው።

የአልጄሪያ ገዢ የነበሩት ካባን ከጎረቤቶች አገር ጋር ሦስት ዓመት ሙሉ በመዋጋት የጦር ሠራዊታቸውን አደከሙት። የጦር ሠራዊቱ አዛዦች ወደ ገዢያቸው ቀርበው ጦርነቱ እንዲቆምና ከጎረቤት አገሮች ጋርም እርቅ እንዲደረግ አመለከቱ። ገዢው ግን እምቢ አሉ። ከዚህ በኋላ እኒሁ የወታደር አለቆች መክረው በገዢው ቦታ አንድ ያልታወቀ ሰው ለማስቀመጥ ወሰኑ። ይህን ያልታወቀ ሰው የሚፈልግ መልእክተኛ ላኩ። መልእክተኞቹም ወጣ እንዳሉ አንድ የተቀዳደደ ጫማ የሚጥፍ ሽማግሌ ሰው አገኙ። ሰውየው በሽምግልናው ላይ ረጅም ጢም ያለው ነበር። ይህ ነገር የሆነው በ1695 ዓ.ም ነሐሴ 5 ቀን ነው። ሰየውን ስሙን ጠየቁት። አህመድ ነኝ አለ። ከዚያም በወታደሮቹ ሁኔታ የደነገጠውን ያን ሽማግሌ በፈረስ አስቀምጠው ወደ ሠፈራቸው ወሰዱት እንደደረሱም ገዢያቸውን ከሥልጣን አውርደው ያን ምንም የማያውቀውን ጫማ ሰፊ ጀኒና ከሚባለው ቤተ መንግሥታቸው አግብተው በገዢያቸው ወንበር ላይ አስቀመጡት። ሆኖም ይህ ጫማ ሰፊ በድንገት በደረሰበት ነገር በድንጋጤ የሚሠራውን ምንም አያውቅም ነበርና አልጄሪያን ለሦስት ዓመት ከገዛ በኋላ በ1698 ዓ.ም በሐምሌ ወር ሞተ።

በሰሜን አውስትራሊያ አንድ ሐይቅ አለ። የሐይቁ ስም KARDIVILLIWARRAKURRAKURRIEAPPARLARDOO ነው።

በአውስትራሊያ አገር ኪርክሱድ ብራይት በተባለች ቀበሌ ይኖሩ የነበሩት አቶ ቢሊ ማርሻል በመቶ ዓመት ዕድሜያቸው አራት ልጆች አስወልደዋል። እኚህ ሰው የሞቱት በመቶ ሃያ ዓመት ዕድሜያቸው በ1792 ዓ.ም ነው።

በ1842 ዓ.ም ተወልደው በ1885 ዓ.ም የሞቱት እንግሊዛዊው ኰሎኔል ፍሬደሪክ ባርናባይ አንድ ቀን ዊሬደሪክ በርናባይ አንድ ቀን ዊንጋር ሲጫወቱ መኮንኖቹ እንደቀልድ «ኮሎኔል ፍሬደሪክ እኮ ፈረስ ተሸክሞ መሄድ ይችላል» አሉ። ኰሎኔሉም ይህን ቀልድ በግብር ለማሳየት ሁለት ፈረሶች በንብርቢጣቸው ይዘው ከፎቅ ቤት አውጥተው እንደ ገና አወረዱዋቸው። ይሄው ዝናቸው ለንግሥት ቪክቶሪያ ደርሶ ንግሥቲቱ ሸልመዋቸዋል። የፈረሶቹ ክብደት 325 ኪሎ ያህል ነበር።

በሜክሲኮ ከተማ ያለውን ብሔራዊ ሙዚየም ብትጎበኙ አንድ የመስዋዕት መሰዊያ የነበረ ድንጋይ ታያላችሁ። በምድር ላይ እስካሁን ይቺ መጽሐፍ እስከታተመችበት ጊዜ ድረስ ብዙ ደም የፈሰሰበት የመሰዊያ ድንጋይ ከዚያ ድንጋይ እኩል እንደሌለ ይተረካል።። ጥንታውያን የአሜሪካ ሕንዶች የነገሥቶቻቸውን የልደት ወይም የንግሥ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በዚያ ድንጋይ መሠዊያ ላይ ብዙ ሰው ይታረድና ልቡ እየወጣ ለመስዋዕት ይቀርብ ነበር። በዚያ ድንጋይ ላይ አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ሰዎች ታርደው ልባቸው እየወጣ ለመሥዋዕት ቀርቧል።

በፍሌሚሽ ቋንቋ መኪና ለማለት SNEL PAARDE FOOSZNDERS POOR WEFP ETROLIJTUIG ብለው ይጽፋሉ።

ፀሐይ በአንድ ሰከንድ 4.620.000 ቶን የሚሆን ኃይሏን ትጨርሳለች። በዚህ ሁኔታ ካላት ጠቅላላ ኃይል ከመቶ አንዱን እጅ አቃጥላ ለመጨረስ 150.000.000.000 ዓመታት ያስፈልጋታል።

# ዘጠኝ

ከቁጥሮች ሁሉ እንደ ዘጠኝ አስደናቂ የለም። ሌላውን እንተወውና ወደ ሂሳቡ እንሂድ። 123456789 ሲደመሩ 45 ይሆናሉ። አራትና አምስት ሲደመሩ ተመልሰው 9 ይሆናሉ። ማንኛውንም ቁጥር ይጻፉ። ያን ቁትር ያገላብጡና ከትልቁ ትንሹን ይቀንሱ። የሚያገኙት ውጤት ለዘጠኝ መካልፈ የሚችል ነው። ለምሳሌ ሥራውን ይመልከቱ። 6721 ጽፈዋል እንበል። ይህን የጻፉትን ቁጥር ሲገለብጡት 1276 ይሆናል። እንግዲህ ከትልቁ ቁጥር ሲገለብጡት 1276 ይሆናል። እንግዲህ ከትልቁ ቁጥር ከ6712 ላይ 1276 ቀሪው 5445 ይሆናል። ይህን ቀሪ የሆነውን 5445 ለ9 ቢያካፍሉት ያለምንም ቀሪ 605 ጊዜ ይደርሳል።

ሌላ ደግሞ፤

9 x 2 =18 አንድና ስምንት ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

9 x 3 = 27 ሁለትና ሰባት ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

9 x 4 = 36 ስድስት ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

9 x 5 = 45 አራትና አምስት ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

9 x 6 = 63 ስድስትና ሦስት ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

9 x 7 = 81 ስምንትና አንድ ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

እንዲህ እያደረጉ እፈለጉት ቁጥር ድረስ ቢያባዙት ውጤቱ ተመልሶ ያው 9 ነው። የሚሆነው። ለማስረጃ አንድ ላሳይዎት 76 x 9 = 684 ይሆናል። እነኚህን ውጤቶች ሲደምሩዋቸው 18 ይሆናሉ። አንድና ስምንት ደምነ ሲደመሩ 9 ይሆናሉ።

ሌላ ደግሞ

987654321 x 9 = 8888888889

987654321 x 18 = 17777777778

987654321 x 27 = 26666666667

987654321 x 36 = 35555555556

987654321 x 45 = 44444444445

987654321 x 54 = 53333333334

987654321 x 63 = 62222222223

987654321 x 72 = 71111111112

987654321 x 81 = 80000000001

በእነኚህ ቁጥሮች ውስጥ በየኮለሙ ያሉት ቁጥሮች እንኳ የየመስመራቸው ያለመዛነፍ ብቻ ሳይሆን ከላይ ወደታች ከታች ወደላይ ከአንድ እስከ 9 ድረስ ይሄዳሉ። በውጤቱ ላይ በስተቀኝዎ ያለውን የመጨረሻውን ኮለን ይዘው ሽቅብ ቢያነቡት ከ1 እስከ 9 ድረስ ናቸው። የግራዎን የዳር ኮነ ይዘው ቁልቁል እንዲሁ መደዳ ሆነው ያገኙዋቸዋል። የሐመሎቹም ቁጥሮች እንዲሁ ናቸው።

ሌላ ደግሞ

X 9 + 2 = 11

12 X 9 + 3 = 111

123 X 9 + 4 = 1111

1234 X 9 + 5 = 11111

12345 X 9 + 6 = 111111

123456 X 9 + 7 = 1111111

1234567 X 9 + 8 = 11111111

12345678 X 9 + 9 = 111111111

ሌላ ደግሞ

123456789 እነዚህ ቁጥሮች በ9 ሲባዙ ውጤታቸው 111111111 ይሆናል። ቆይ ይሄንንም በብዛት ላሳይዎት።

123456789 X 9 = 111111111

123456789 X 18 = 222222222

123456789 X 27 = 333333333

123456789 X 36 = 444444444

123456789 X 45 = 555555555

123456789 X 54 = 666666666

123456789 X 63 = 777777777

123456789 X 72 = 888888888

123456789 X 81 = 999999999

የዘጠኝን ጉድ ባመጣልዎት ብዙ የሚገርሞት ያገኛሉ። ግን ሲበዛ ማር እንኳ ይመራልና ያሰለችዎታል ብዬ ተውኩት ለማወቁ ያህል እስታሁን የነገርኮት ይበቃዎታል።

አንድ ሰው በመርከብ ብቻ ዓለምን ለመዞር ይችላል። ይሄውም የሚቻለው በስልሳኛው ፓራሌል በደቡብ ላቲቱድ የተጓዘ እንደሆን ብቻ ነው።

ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን በምድር ላይ የነበረው ሕዝብ ብዛት 250 ሚሊዮን ነበር። በ1600 ዓ.ም የሕዝቡ ብዛት በአጠፌታ ጨመረ። በ1850 ዓ.ም አንድ ቢልዮን ደረሰ። ከመቶ ዓመት በኋላ ሁለት ቢሊዮን በመጨመር ሦስት ቢሊዮን ደረሰ።

ለሰው ልጅ ጠላቶች ዋንኛዋ አይጥ ናት። በአሜሪካ አገር በአንድ ዓመት ጊዜ ብቻ ሁለት ቢሊዮን ተኩል ብር የሚያወጣ ጉዳት በዕቃ ላይ ያደርሳሉ። በአንድ ሺ ዓመት ውስጥ በጦርነት ካለቀው ሕዝብ ይልቅ በአይጥ ሰበብ ያለቀው ሕዝብ ይበልጣል።

እንግሊዛዊው ዊልያም ፒት በሰባት ዓመት ዕድሜው የላቲን ግሪክኛ ቋንቋዎንች አጣርቶ መናገር ቻለ። በ14 ዓመት ዕድሜው ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ገባ። በ21 ዓመት ዕድሜው የእንግሊዝ ፓርላማ አባል ሆነ። በ24 ዓመት ዕድሜው የእንግሊዝ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ። እኚህ ሰው በ1759 ዓ.ም ተወልደው በ47 ዓመት ዕድሜያቸው በ1806 ዓ.ም ሞቱ።

በዓለም ዝናው የገነነው ተረተኛው ኤሶፕ ከተረቶቹ አንደኛይቱንም አልጻፋትም። ከቃል ወደ ቃል እየተራባ ሲወራ ለመቶ ዓመታት ያህል ኖረና በኋላ አንድ ብልጥ ሰው ማስታወስሻ ያዘው። ለአንድ ሺ ዓመታት ያህል የኤሶፕ ተረቶች ከምድረ ገጽ ከሚባል ተራራ ላይ ካለው ገዳም ተረቱ የተጻፈበት ማስታወሻ ተገኝቶ ተራባ።

በ1856 ዓ.ም በግሪክ አገር አንዲት ሴት ከመንገድ ላይ ልጅ ወልዳ ሞታ ተገኘች። ልጁ በሕይወት ነበረና የአዞስ ተራራ መነኮሳት ያን ሕጻን ከነደሙ ወስደው በገዳማቸው ውስጥ አሳደጉት። የልጁም ስም ሚሃይሎ ቶሎቶስ ተባለ። ከዚያ ገዳም ሴቶች እንዳይገቡ በጥብቅ ከልክላ ይደርጋል። ተወለዱ በሰማንያ ዓመት ዕድሜያቸው በ1938 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በዓለም ታሪክ ውስጥ ሴት በዓይናቸው ሳያዩ ወይም ሴት ሴት ማለት እንዴት ያለ ፍጡር መሆንዋን ሳያዩ የሞቱ ሚሃይሎ ቶሎቶስ ብቻ ናቸው።

በእንግሊዝ አገር የሚገኘው የሉተር ዎርዝ ባንክ በ1830 ዓ.ም ለመክሰር ደረሰ። የባንኩ ሥራ አስኪያጆች መላ ፈጥረው ባንኩን ከመክሰር አድነውታል። በባንኩ ዋና በር አንድ ሰው በጋሪ የወርቅ ጊኒ ሞልቶ በአዳራሹ መሐል ጋሪውን እየገፋ እንዲያልፉ አደረጉ። ይህ ሰው በጓሮው በኩል ይወጣና ትንሽ ቆይቶ ያንኑ ጋሪ እየገፋ በአዳራሹ መሐል ያልፋል። በእንዲህ ዓይነት ጉዞ በመደጋገም መቶ ጊዜ ያህል እያለፈ ያንኑ ወርቅ ለሕዝብ ስላሳየ የሀገሩ ሀብታሞች በባንኩ እምነት አድሮባቸው ብዙ ገንዘብ ስላስቀመጡ ባንኩ እንደ ገና ሊያንሠራራ ቻለ።

ያለንባት ምድር አንድ አምስተኛዋ በልዩ ልዩ የሣር ዓይነት የተሸፈነ ነው። እነዚህም የሣር ዘሮች የዓይነታቸው ብዛት እስከ ስድስት ሺ ይደርሳል።

በእንግሊዝ አገር ፌሪንግ በተባለ ቦታ በ1892 ዓ.ም አንድ ሽቶ የያዘ ብልቃጥ ተቀብሮ ተገኝቷል። ይህ ብልቃጥ በ292 ዓ.ም የተቀበረ ነው። በተቀበረ 1600 ዓመቱ የተገኘው ይህ ብልቃጥ ሽቶ ምንም አልተበላሸም ነበር። ከዚህም ሌላ ሽታው በጣም ደስ የሚል ሆኖ ተገኝቷል።

አውስትራሊያኖች የገመድ ዝላይ ጨዋታ በታም ይወዳሉ። ከመውደዳቸውም የተነሳ ብዙ ልምምድ ሰለማያደርጉ በአንድ ደቂቃ 286 ጊዜ ገመዱን መዝለል እንደሚችሉ በ1936 ዓ.ም በተደረገው ውድድር ላይ አስመስክረዋል።

የኮሪያ አሣ አጥማጆች አሣ የሚያጠምዱት በወፍ ነው። ወፎቹ አሣ የሚመገቡ በመሆናቸው አሣ በማጥመድ የታወቁ ናቸው። ወፎቹ የያዙትን አሣ እንዳይውጡት አንገታቸው ላይ ቀለበት ይታሠርባቸዋል። ወፎቹ አሣውን ከያዙት በኋላ መዋጥ ስለማይችሉ አሣ አጥማጆቹ ሰዎች ከወፎቹ አሣዎቹን እየለቀሙ ይወስዳሉ።

## ከወፍ ዘር ጥሩ ድምፅ ያለው ወንዱ ነው።

ከጀርመን ጠቅላይ ግዛቶች አንዱ ኮለኝ ነው። ይህ ኮለኝ የሚባለው ከተማ ራይን ከተባለው ወንዝ ዳርቻ የተሠራ ነው። በ18ኛው መቶ ዘመን አንድ ኢጣልያዊ ቀማሚ በዚያ ከዚያ ከተማ ሽቶ ሠርቶ የሽቶውን ስም አዶኮሎኝ አለው። ይህ ሽቶ እስከ ዛሬ ድረስ በመላው ዓለም ዝነኛ ነው። ኢጣልያዊው ሽቶውን የሠራው በዚያ ከተማ ውሀ ስለ ነበር አዶኮሎኝ ብሎ የሰየመው የኮሎኝ ውሀ ማለቱ ነው።

በፊሊፒንስ ባያ የምትባል ወፍ አለች። ይቺ ወፍ በጨለማ መዞር ስለምትወድ ዛሬ ስትመለስ ጎጆዋ እንዳይጠፋት በጎጆዋ በር ላይና ዙርያ የሚያበሩ ትሎችን ከጎጆዋ ጋር ተብትባ ትሠራዋለች። ለሊት ትሎቹ ስለሚያበሩላትም ያለ ችግር ጎጆዋን ታገኘዋለች።

እንግሊዛዊው ሚስተር ዳንኤል ሰላምበርት በ1770 ዓ.ም ተወለደ። በ1793 ዓ.ም ክብደቱ 203 ኪሎ ነበር። በ1809 ሲሞት 334 ኪሎ ይመዝን ነበር።

በሞንትርያል ከተማ የነበረው 35 ዓመት ዕድሜ ያለው አንቶኒዮ ባርቺቪች በሰንሰለት የታበተውን አቶቡስ በትክሻው እየጎተተ ይዞት ይሄዳል። አንቶኒዮ ክብደቱ 200 ኪሎ ሲሆን ኃይሉም ያለው በግሩ ላይ መሆኑን ሊቃውንት ተናግረዋል።

ገብርኤል እስቲቮ የተባለው ይህ ሰው በስቶኮሎም ከተማ ባለው መናፈሻ በግሮናሎንድ መዋል ይወድ ነበር። ገብርኤል የተወለደው በአፍሪካ የፖርቱካል ቅኝ ግዛት ውስጥ እንው። የገብርኤል ቁመት አምስት ክንድ ከስንዝር ነው። ይህ ጓደኛው ቫሲንቶ ሆረራ ይባላ። ቫሲንቶ ፖርቱጋል ውስጥ የተወለደ ነው። የገብርኤል ጓደኛ የቫሲንቶ ቁመት አንድ ክንድ ከስንዝር ብቻ ነው። ገብርኤልና ጓደኛው አብረው ሲሄዱ የሚያያቸው ሰው ሁሉ ይስቃል። የቫሲንቶ ቁመት ከገብርኤል ቅልጥም ሥር በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ገብርኤል የሚሄደው ጓደኛውን ቫሲንቶን ተሸክሞ ነው። በስዕሉ ላይ የሚታየው ገብርኤል ቫሲንቶን ተሸክሞ ነው።

# ከባህር ዛፍ ዘር ረጃጅሞቹ ጃራህና ካሪ የተባሉት ናቸው።

320 ኪሎ ክብደት ያለው ነፃ ትግል ታገዩ ሃይስታክስ ለቁርስ የሚበላው 12 እንቁላሎች፤ ሃያ ኬክ፤ አንድ ኪሎ የአሣማ ሥጋና አንድ ጋሎን ወተት ነው። ለምሳው ሁለት ኪሎ ሥጋ፤ ሰላጣና አትክልቶችን በብዛት ይመገባል።

ሃይስታክስ በጃምቦ ጄት አይሮፕላን ለመሣፈር በተዘጋጀበት ጊዜ የአይሮፕላኑ አስተናጋጅ ስለ ምግቡ ስትጠይቀው ፎቶ ግራፉ ያሳያል።

ይቺ ልጅ በተወለደች በሃያ ሁለት ወርቃ የምግብዋ ጉዳይ አስቸጋሪ ሆነ በቀን 200 ግራም ፓልፖ ዲማንዞ፤ 200 ግራም የዶሮ ሥጋ፤ መቶ ግራም የጥጃ ሥጋ፤ አራት እንቁላል መቶ ግራም አይብ፤ ግማሽ ኪሎ ሚኒስትሮኒ ሁለት ሊትር ወተት፤ አንድ ኪሎ ሙዝ፤ መቶ ግራም ፎርማጆ የፍራፍሬ ሾርባ፤ የፍራፍሬ ጭማቂ፤ ሎሚናት የተጣራ ውሀ ናቸው። እነዚህ ምግቦች ሜርሉስ በተባለ የአሣ ዘይት ይሠሩላትና ትበላለች። ከዚህም ሌላ ቫይታሚንና ልዩ ልዩ ዓይነቶች የምግብ መድኃኒቶች በየቀኑ ይሰጡዋታል። የዚች ልጅ አባት

ኢጣልያዊው አቶ ጁልዮ ማካ ዕድሜው 33 ዓመት ነው። በወር ለልጁ ምግብ የሚያደርገው ወጪ መቶ አምሳ ሺ ሊሬ ነው። ይህ ገንዘብ በአሁኑ በኛ ገንዘብ ሲመነዘር ስድስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ይሆናል። በዚህ የተነሳ አባትዮው የቤቱን ዕቃ ሁሉ ሸጦ ጨርሷል። ስለዚሁም ጉዳይ ጋዜጠኞች ጠይቀውት ሲመልስ «ልጄን ልገድላት አልፈልግም። እስዋ ስትበላ እኔና እናትዋ ቁጭ ብለን እናያታለን፤ እኛትልልቆቹ ምሣ ራት፤ ሳንበአል ብንቀር ግድ የለንም። ለእሷ ግን ችግር ነው» ብሏል። ይቺ ልጅ የምትኖረው በሮማ ከተማ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ፲፱፻፹፩ ዓ.ም መግቢያ ገደማ ላይ የፓኪስታንዋ ወይዘሮ ኑን ጀሀን ሁለት ራስ ያለው ወንድ ልጅ በካራቺ ሆስፒታል ውስጥ ወልዳለች። ሁለት ራስ ሲኖረው የቀረው አካሉ እንደማንኛውም ሰው ጤነኛ ፍጡር ነው።

በግራ ያለችው አንቶኒያ ትባላለች። የዚች ልጅ ዕድሜ 13 ዓመት ሲሆን ክብደቷ 175 ኪሎ ነው። ከቀኝ በኩል ያለችው እህቷ ማርያ ትባላለች። የዚች ዕድሜ ደግሞ 21 ዓመት ሲሆን ክብደቷ ግን 250 ኪሎ ነው። እነኚህ እህትማማቾች የሚኖሩት ከናሪ በተባለች ደሴት ነው። ኑሮቸው የደስታ ነው። ብቻ የሚያበሳጫቸው ነገ እንደ ሌሎቹ ሴቶች እነሱን ወደ ናይት ክለብ የሚወስዳቸው ጎረምሳ ማጣታቸው ነው።

በቼኮዝሎቫኪያ አገር ሀራቾቭ በተባለች ተራራ ላይ ባለች አምባ አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ። የቤተ ክርስቲያኑ ደወል የተሰራው ከመስተዋት ነው። ይህን ደወል የሠራው ጁልየስ ክሊንገር የተባለ ሰው በ1916 ዓ.ም ነው። ይህ ከመስተዋት የተሠራ ደወል ርዝመቱ 51 ሳንቲ ሜትር ሲሆን ክብደቱ 12 ኪሎ ያህል ይሆን ነበር። መደወያው ከጠንካራ እንጨት የተሠራ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው በ1902 ዓ.ም ነው።

በለንደን ከተማ በቅዱስ ጄምስ መናፈሻ ሥፍራ ያሉትን አእዋፋት 25 ዓመት ሙሉ በመመገብ የታወቁት ወይዘሮ ካቴሊን ላርክ ማን የተባሉት ሴት

በወፍና በሰው ታሪክ ውስጥ አስደናቂ ተግባር ፈጽመዋል። በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ወፎች ዘወትር በየቀኑ ከስምንት ሰዓት ተኩል እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እኚህ ሴት ይመግቡዋቸዋል። የሚመግቡዋቸውም አይብ ሲሆን አይቡን በአፋቸው እየያዙ ሲያንጋጥጡ ወፎቹ ከከንፈራቸው ላይ አይቡን እየለቀሙ ይወስዳሉ። ሴትዮዋ ገና ከዚያ አካባቢ ሲደርሱ ወፎቹ በራሳቸው ላይ በማረፍ ምግባቸውን እንዲሰጡዋቸው ያንቋርራሉ። ይህ የምታዩት ፎቶ ግራፍ እንዴት እንደሚመግቡ ነው።

ሴርዊክ በተባለች ደሴት አንድ ልጅ ከባሕር ሲጫወት ድንገት ከባሕሩ ውስጥ ወደቀ። ልጁ ራሱን ለማዳን እየተንፈራገጠ በባሕሩ ውስጥ ብዙ ርቆ ሄደ። ከዳር ሆኖ ይመለከተው የነበረ ፈርስ ማንም ሳያዘው ከባሕሩ ውስጥ ገብቶ እየዋኘ ሂዶ የልጁን ልብስ በጥርሱ ነክሶ በማውጣት ከሞት አድኖ ለወላጆቹ አብቅቶታል።

በበርማ ያሉ ሻን የተባሉ ነገዶች አጥራቸውን የሚያጥሩት በስዕሉ ላይ እንደሚታየው አድርገው ነው። እንዲህ የሚያደርጉትም መጥፎ መንፈስ ሊገባ ሲል ተብትቦ ይይዘዋል የሚል እምነት ስላላቸው ነው።

ፓስፊክ ጎድዊትዝ የሚሏቸው ወፎች የበጋውን ወራት በሲቤሪያ ያሳልፉና ክረምት ሲመጣ ወደ ኒውዚላንድ ይመጣሉ። ይህም የሚበሩት ርቀት 9600 ኪሎ ሜትር ነው። 3200 ኪሎ ሜትር የሚበሩት በውቅያኖስ ላይ ብቻ ነው።

ጊልበርት ሮሜ የተባለ ሰው የፈረንሳይን ሬቮሊስዮን አስነስተሃል ተብሎ ተከሰሰና በ1794 ዓ.ም በሞት እንዲቀጣ ተፈረደበት። ወደ መግደያው ቦታ ሂዶ ፊቱን አንገቱንና ልቡን በጥይት ተደበደበ። ከዚያ በኋላ ሬሳውን ላንድ ወዳጅ እንዲቀብረው ሰጡት። ጊልበርት አልሞተ ኖሮ ከወዳጁ ቤት አገግሞ ድኖ ከዚያ በኋላ 35 ዓእምት ኖሮ በእግዚአብሔር እጅ ሞተ።

ውሀ ከውሀነቱ ወደ እንፋሎት በተለወጠ ጊዜ በፊት ከነበረበት ቦታ 1700 ጊዜ የበለጠ ቦታ ይይዛል።

የወፎችን እንቁላል የሚውጡ እባቦች አሉ። እነዚህም እባቦች እንቁላሉን ሳያፈርሱ እንዲሁ እንዳለ ስለሚውጡት ለወፎች እጅግ ጠንቀኞች ናቸው። እነዚህ እባቦች ወፎቹን እንቁላል እንደሚያደርጉት በሚቀጥሉት ፎቶ ግራፎች እንመልከት።

በፈረንሳይ አገር ሊዮንስ ላ ፎርት በተባለ ቀበሌ አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ የቤተ ክርስቲያኑ ዕድሜ አሁን 238 ዓመት ሆኖታል። በዚህ ዘመን ሁሉ የቤተ ክርስቲያኑ ደወል የሚደወለው በየቀኑ 33 ጊዜ ነው። ይህም ክርስቶስ በምድር የኖረበትን ዘመን መታሰቢያ በማድረግ ነው።

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሕንድ የጦር ዝሆኖች ወደ ጦርነት የሚሄዱት የብረት ልብስ እየለበሱ ነበር።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኮሎምቢያ አንድ ሕፃን ሲሞት ወደ ቀብር የሚሄደው ጊታር በሚመቁ ሙዚቀኞች ታጅቦና ሬሳው በአንድ ረጅም ሳንቃ ላይ ተቀምጦ ነበር።

በአፍሪካ ውስጥ በኡጋንዳ ያሉ ቡንዮር የተባለ ጎሣ ሰዎች የሙዝ ጠላ ይጠምቃሉ። በአንድ ሰፊ ገንዳ ውስጥ የተቀቀለ ሙዝ ሣር፤ ውህና የሙዙን ግንድ በአንድነት ያደርጉና ያንን በእግራቸው ለአንድ ሰዓት ያህል ይረግጡታል። ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ከድነው ያኖሩትና ይጠጣል። የዚህ የሙዝ ጠላ ሥራ በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ጥሩ አልኮል ይፈጥርና ሊጠጣ ይቻላል።

ከአንበሳ ይልቅ የጅብ ጥርስ ጠንካራ በመሆኑ አንበሳ በጥርሱ ሊሰብረው የማይችለውን አጥንት ጅብ በጥርሱ ይሰብረዋል።

በ1741 ዓ.ም ተወልደው በ1822 ዓ.ም የሞቱት የቱርኩ አሊ ፓሻ አርባ ዓመት ሙሉ በነበራቸው የግዛት ዘመን ሰላሳ ሺ ሰዎች ገድለዋል። ግን በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ አንዲት አበባ በቆረጡ ጊዜ በኃዘን እያለቀሱ «ጌታ

ሆይ በሠራሁት ኃጢአት ይቀር በለኝ» እያሉ ይጸጸቱ ነበር። ሰው ሲገልዱ ግን ምንም አይጸጸቱም።

ሰሎሞን በተባሉት ደሴቶች የውሻ ጥርስ የመገበያያ ገንዘብ ነው።

መጀርመን አገር ያለው ብራውንፌልስ የተባለው ቤተ መንግሥት ሶልምስ በተባሉ ነገሥታት ዘሮች ሌላ ዘር ጣልቃ ሳይገባባቸው 722 ሙሉ ይዘውት ኖረዋል።

የሕንድ አገር አሣ አጣምጆች አሣ በሚያጠምዱበት ወንዝ ወይም ባሕር ላይ የሚሄዱት ሁለት ግንዶች አብረው አሥረው በላያቸው ላይ ተቀምጠው ነው።

በ1615 ዓ.ም ተወልደው በ1712 ዓ.ም የሞቱት ወይዘሮ አን ቦርዴል አቶ ጆርጅ ዴኒስን የተባለውን ሰው ሲያገቡ የወይዘሮዋ አባት «ለልጄ በክብደቷ ልክ ወርቅ ሰጥቻለሁ» ስላሉ ወይዘሮ አን ተመዝነው 65 ኪሎ ስለከበዱ 65 ኪሎ ወርቅ ወስደዋል።

በ1967 ዓ.ም ኅዳር 13 ቀን በተደረገው የቅርጫት ኳስ ውድድር ጆሪ ማርኪኔስ የተባለ ተጫዋች ከሰላሳ ሜትር ርቀት የወረወራትን ኳስ በቅርጫቱ ውስጥ ጨምረዋል።

በሰሜን ቺሊ ውስጥ ባሉት መንደሮች በአብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች አስተማሪ የላቸውም። የመንደሩ ፖሊሶች ለጥበቃ በሚዘዋወሩበት ጊዜ በየትምህርት ቤቱ እየገቡ ያስተምራሉ።

በ1200 ዓ.ም ተወልዶ በ1275 ዓ.ም የሞተው ኡልሪች ቮን ሊተንስቴን የተባለው ጀርመናዊ በደረሳቸው የግጥም ድርሰቶቹ እስከ ዛሬ ድረስ በጀርመን አገር የተከበረ ሰው ነው። ኡልሪች ማንበብም ሆነ መጻፍ አይችልም ስለነበር የግጥም ድርሰቱን የደረሰው አንድ ጸሐፊ ቀጥሮ እሱን በማጻፍ ነበር።

በስፔይን የተከበሩ የነበሩት ስዕል ሳይ ሉዊስ በ1502 ዓ.ም ተወልደው በ1568 ዓ.ም እስኪሞቱ ድረስ በየቀኑ ከቆዳ የተሠራ ልብሳቸውን ለብሰው አራት ሰዓት ሙሉ በመኝታቸው ላይ እየተኙ ሞትን ይጠብቁ ነበር።

ባርቶሞሚዮ የተባሉ የፖርቱጋል ሰው ጥፋት አጥፍቶ ለፍርድ በመርከብ ተይዞ ሲሄድ ከውቅያኖስ መሐል ላይ መርከቧ ስትደርስ ከመርከቡ ላይ ዘሎ በመውረድ አምልጧል። በርቶሞሚ ሚዮ መዋኘት ፈጽሞ አይችልም ነበርና ሊያመልጥ የቻለው በመርከቡ ላይ የነበሩ ሁለት የወይን ጠጅ ጠርሙሶች ይዞ በመውረዱ ጠርሙሶቹ እንዳይሰጥም ረድተውት በሰላም ከዳር ደርሷል።

በአፍሪካ ያሉ የማላይ ጎሣ ሰዎች መሐል ጦረኛ የሆኑት አንድ ጥበበኛ ወይም ጀግና ሰው ሲሞት የሟቹን ጠጉር ላጭተው በራሳቸው ላይ በጭቃ አጣብቀው ያደርጉታል። ይህም የዚያን የሟቹን ሰው እውቀት ወይም ጀግንነት ያወርሰናል ብለው ስለሚያምኑ ነው።

በስፔይን ውስጥ አልፑጃራ በተባለች ቀበሌ ዳቦ በዱቤ የሚሸጡ ሰዎች አንድ አገዳ ይይዛሉ። በዚህ አገዳ ላይ ሰውየው የወሰደው ዳቦ ልክ በወሰደበት ጊዜ ሁሉ አንዳንድ ጭረት ይደረግበታል። አንዱ ጭረት አንድ የዱቤ ዳቦ ማለት ነው። ይህም አገዳ ሁለት ይሆንና አንዱ በሻጩ እጅ ሲቀመጥ አንዱን ዱቤ ገዢው ይዞ ይሄዳል። ሲገዛ ሲመጣም ይዞት ይመጣል።

ተቀን መቁጠሪያን ያሳተመው የመጀመሪያው ሰው ቬኑስ ፍላቡስ የተባለ ሮማዊ ሰው ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት 304 ዓመት ላይ ይህ ሰው በሮማውያኖች ዘንድ እንደሚስጢር ይጠበቅ የነበረውን የቀን መቁጠሪያ በግልጽ ጽፎ ለሕዝብ እንዲደርስ አደረገው።

በ146 ዓ.ም ተወልደው 211 ዓ.ም የሞቱት ሴፕቲሙስ ሴቬሩስ የተባሉ ሰው የሮማውያን ንጉሠ ነገሥት ተብለው በተመረጡበት ጊዜ ለአሥራ ሁለት ሺ ወታደሮቻቸው ለያንዳንዱ አምሳ ሺ ሴስቴር ገንዘብ ሰጡዋቸው። ይህ ገንዘብ በዛሬው የኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር $64.410.000 ይሆናል።

በአፍሪካ የሚኖሩ ሽሉክ የሚባለው ጎሣ ሰዎች የሚወዱትን ከብት ዓይነት ቀለም በፊታቸው ላይ በመቀባት መልካቸውን ከከብቱ ፊት ጋር ተመሳሳይ ያደርጉታል።

የስዊድኑ ንጉሥ ቻርለስ ፲ኛ በስቶኮልም ከተማ ሲሞቱ ለብሰውት የነበረው ልብስ ለሕዝብ ይታያል። ንጉሡ ሲወድቁ ልብሳቸውን ጭቃ ነክቶት ስለነበረ ጭቃው እስከ ዛሬ ድረስ አምለት ከ250 ዓመታት በኋላም በልብሱ ላይ እንዳለ ሆኖ ይታያል።

በኬንያ ተራራማ ቀበሌዎች የሚኖሩ ሊቲ ጋንትስ የሚባለው ጎሣ ሰዎች መሐል እንዳንዶቹ ጀግንነታቸውን የሚያስመሰክሩት በእሳት ግሎ እሳት የመሰለውን ጦር ወይም ሰይፍ በመላሳቸው በመላስ ነው።

በኒውጀርሲ ውስጥ ብሎሚንጋድል በተባለች ቀበሌ እሳት ተነስቶ የእሳት አደጋ መከላከያ ተተራ። መኪናው አደጋውን ለመከላከል ወደቃጠሎው ቦታ በሚበርበት ጊዜ በራሱ በመኪናው ላይ እሳት ተነስቶ ቃጠሎ ጀመረው። የመኪናው ሾፌር ፍራንክ ሚለር የሚቃጠል መኪናውን ሳያቆም እንዲው እንደበረረ ከተጠራበት ከቤት ቃጠሎው ቦታ ደርሶ ቤቱን መኪናውም አብረው ተቃጠሉ ይህ ነገር የሆነው በ1913 ዓ.ም ነው።

ጀርመናዊው ስዕል ሳይ ሄርማን ጎልድ ሽሚት በፈረንሳይ አገር በፓሪስ ከተማ ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ ተቀምጦ ከጓደኛው ጋር ሲጫወት በአንዲት አነስተኛ ቴሌስኮፕ በቡና ቤቱ መስኮት ወደ ውጪ ሲመለከት ከዚያ በፊት ሰው ያላገኛቸውን ከዋክብት በማግኘቱ እስከ ዛሬ ዝናው የገነነለት ሰው ሆንዋል። ሄርማን ያገኛቸው ከዋክብት 14 ናቸው። ሄርማን በ1802 ዓ.ም ተወልዶ በ1866 ዓ.ም ሞተ።

በስፔይን ውስጥ ሳንታንደር በእትባለች ቀበሌ አጠገብ ጋንዳራ የተባለ ፏፏቴ አለ። የፏፏቴው የውሀ አወራረድ ልክ የፈረስ ቅርጽ ያለው ሆኖ ነው።

ማርኩስ ደ አንቶኔል የተባለው የታወቀ የፈረንሳይ ደራሲ ከማጅራቱ ላይ ቀዝቃዛ ሰሃን ሳያደርግ መጻፍ አይችልም ነበር። ማርኩስ በ1747 ዓ.ም ተወልዶ በ1817 ዓ.ም ሞተ።

በሕንድ አገር በሂልማያ ቀበሌ ካሣኡሊ የተባለው ጎሣ ሴቶች ልጆቻቸውን የሚያስተኙት ከአሸንዳ በሸንበቆ በሚወርድ ውሀ የልጆቻቸውን ራስ በማስመታት ነው። ልጁን እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ ውሀው የልጁን ራስ ከመምታት አያቋርጥም።

በካሊፎርኒያ ይኖሩ የነበሩት ወይዘሮ ሚያራ ብሩክስ ዌልሽ የተባሉ ሴት ሦስት መጽሐፍት ጽፈዋል። ሦቱንም መጻሕፍት የጻፉት የመጻፊያ ታይፓቸውን በጣታቸው ሳይነኩ በሁለት እርሳሶች ላይ ባሉ ላስቲኮች ወይም ላፒሶች በመምታት ነው። ይህም ሥራ አላፈጥን ብሎአቸው ሦስቱን መጻሕፍት በታይፕ መትተው የጨረሱት በሃያ ዓመት ጊዜው ስጥ ነው። ወይዘሮ ሚያራ በ1878 ዓ.ም ተወልደው በ1959 ዓ.ም ሞቱ።

በ1800 ዓ.ም የተወለደችው ኤልሳቤጥ ራንድሌስ የተባለች የዌልስ ተወላጅ በሁለት ዓመት ዕድሜዋ የበገና ድርደራን ከማንም ሰው አብልጣ በመጫወቷ በነገሥታቶች ዘንድ እየቀረበች ታሰማ ነበር።

በስዊዘርላንድ ይኖሩ የነበሩት ወይዘሮ ክርስቲያን አልመር የተባሉ ሴት ዕድሜያቸውን ሙሉ ተራራ ወጥተው አያውቁም ነበር። ከባላቸው ጋር የአምሳ ዓመት የጋብቻ በዓላቸውን ሲያከብሩ 12.166 ጫማ ከፍታ ያለውን ወተርሆርን የተባለውን ተራራ የሰባ ዓመት ዕድሜ በሆኑት ባላቸው መሬንት ወጥተዋል።

በካንቦዲያ ዝሆኖች እንደ አውቶቡስ የሚያገለግሉ ናቸው። በአንድ ጊዜ አሥራ ሁለት ሰዎችን ያጓጉዛሉ።

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እቦን ይኖር የነበረ ጀርመናዊው ክሌመንስሾን ላፐ ዘጠኝ ሴቶች ልጆች ነበሩት። እነዚህን ልጆቹን የሚያገባ ባል ሲመጣ የመጀመሪያይቱ ትልቋ ልጅ ሳትዳር ትንንሾቹን አልድርም በማለቱ አንደኛውም ልጁ ሳትዳር ቀርታለች። ትልቂቱን ልጁን ደግሞ የሚጠይቅ ባል ለጊዜው አልተገኘም። ነበር።

የፈረንሳዩ ንጉሥ ሉዊስ 11ኛ ከእስፖርት ሁሉ የሚወዱት ጨዋታ ሁለት አይጦች ሲጣሉ ማየት ነበር። ለዚሁም ተብሎ የአይጦች መጣልያ አንድ የእስፖርት ሜዳ ተዘጋጅቶ ነበር። ንጉሥ ሉዊስ በ1423 ዓ.ም ተወልደው በ1483 ዓ.ም ሞቱ።

በጀርመን አገር ሐምበርግ የተባለችው ዝነኛ ከተማ በ1842 ዓ.ም በእሳት ተያይዛ እንደልነበረች ሆና ጠፍታ ነበር። የዚያን ጊዜ ቤት ያጣውን ሰው ለማሳረፊያ ተብሎ ከተሰሩት ጊዜያዊ ሕንፃዎች አንዱ እስከ ዛሬ ድረስ ለአንድ መቶ ሰላሳ ዓመታት ለሕዝብ መኖሪያ ሆኖ ቆይቷል።

አልዩት ሐምፍሬ የተባለ የእንስሳት ጋሪ ሦስት ግመሎችን ወደኋላቸው መሄድ አስለምዷቸው ግመሎቹ ወደ ኋላ የመሄድ ትርኢት ለሕዝብ ያሳዩ ነበር።

በአሜሪካ አገር በማይፊልድ ከተማ ባለው ማፐልውድ በተባለው የመቃብር ሥፍራ የአቶ ሄንሪ ውልድሪጅ መቃብር በ16 ሐውልቶች ያጌጠ ነው። እነዚህም ሐውልቶች የውልድሪጅ ቤተሰቦች፤ ፈረሱ፤ ሁለቱ ውሾቹ አንዲት ቀበሮ እና አንዲት አጋዘን ናቸው።

በማሌዝያ፤ በሳራዊክ ያሌ ሴርባስ ዲያክ የተባለው ጎሣ ሴቶች ሃያ ኪሎ የሚከብድ የብረት ቀለበት በወገባቸው ላይ በማድረግ ያጌጣሉ።

በባሊ ያሉ ሰዎች ቤተ መቅደሳቸውን የሚሠሩት በዛፍና በዛፎች መሐል በዛፍ ላይ አድርገው ነው።

በጥንት ዘመን የካምቦዲ ነገሥታት ሰረገላቸው የሚሳበው በሁለት ሰዎች ነበር። እነኚህ ሁለት ሰረገላ ጎታች ሰዎች ፈረስ እንዲመስሉ በፈረስ ቅርጽ የተሠራ ባርኔጣ በራሳቸው ላይ ይደረግላቸዋል።

በብራዚልና በብሪቲሽ ጊኒያ ወሰን ላይ የሚኖሩት ዋይ ዋይ የተባለው ጎሣ ሰዎች ረጅም ሪዝ ያላቸው ለመምሰል አፍንጫቸውን ቀደው ለመሰል አፍንጫቸውን ቀደው ሁለት የዶሮ ላባ ያደርጋሉ።

በሜልቫል ዘመን የብረት ልብስ ለብሰው የሚዋጉ ጦረኞች ለሊት በሚጓዙበት ወይም በሚዋጉበት ጊዜ ከፈረስ ኮርቻቸው ጋር የተያያዘ ረጅም መብራት ይዘው ነው።

በፓስፊክ ባለችው ቶንጋ በተባለች ደሴት ለፍቅረኞች የተዘጋጀ አንድ የፖስታ ቴምብር አለ። ይህ የፍቅር ደብዳቤ የሚላክበት የፖስታ ቴምብር የልብ ቅርጽ የሆነ ነበር።

በ1577 ዓ.ም ተወልዶ በ1619 ዓ.ም የሞተው የታወቀው ኢጣልያዊው ስዕል ሳይ ክሪስቲፋኖ አሎሪ ማንኛውንም ስዕል ይሠራና መጨረስ ያቅተዋል። ከዚያም ያን ጅምር ስዕሉን ለጓደኞቹ ያሳይና እንዴት አድርጎ እንደሚጨርሰው ይጠይቃል። ሰዎቹ ይነግሩትና እነሱ በነገሩት መሠረት ስዕሉን ይጨርስ ነበር። እንጂ አንዱንም ስዕሉን በራሱ አሳብ ጀምሮ አልጨረሰም።

የእንግሊዝ ንጉሥ ነገሥት ጀምስ አራተኛ አንድ ጊዜ የእራት ግብዣ አድርገው ግብሩ ተበልቶ ካለቀ በኋላ ፍራፍሬ በሚታደልበት ጊዜ የፍራፍሬ ማደያዎቹ ሰሃኖች በሙሉ ወርቅ እየተሞሉ ለተጋባዡ ሁሉ አንዳንድ ሰሃን እንዲታደለው አድርገዋል።

በአሜሪካ አገር በኢዋ አውራጃ ኮርክሺንቪል በተባለ ቀበሌ የሚኖሩት አቶ ኧርንስት ብራንገር በተወለዱ በሰባ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው አሥር ኪሎ የሚመዝን ድንጋይ በጀርባቸው አዝለው በሁለት ጣቶቻቸው ብቻ ከእንጨት ላይ በመንጠልጠል መላውን አካላቸውን ወደ ላይ መሳብ ይችሉ ነበር።

ባፊጂ ደሴት ያሉ ሴቶች ባል ለማግባት በሚፈልጉበት ጊዜ ጠጉራቸውን ወደ ኋላ ጎንጉነው ጉንጉኑ በአንዱ ትከሻቸው ላይ ብቻ እንዲወርድ ያደርጉታል። እንዲህ አድርጋ የምትሄድ ሴት ባል እፈልጋለሁ ማለቷ መሆኑን መንገደኛው ሁሉ ያውቀዋል።

ኤንሪኮ ታዞሊ የተባለ ኢጣልያዊ በ1852 ዓ.ም በአውስትራሊያ አገር ታሠረ። በእዚያው በእሥር ቤቱ ውስጥ እንደሆነ ለወዳጅ የሰላምታ ደብዳቤ የሚጽፍበት ወረቀትና ቀለም በማጣቱ ከአካሉ ላይ ደሙን አፍስሶ በመሐረቡ ላይ ጽፎ ላከላት።

በ1860 ዓ.ም የበርማው ንጉሥ ሚንዶን ለንግሥት ቪክቶሪያ ከንጹህ ወርቅ የተሠራና በላዩ ላይ በአልማዝ ፈርጥ ያጌጠ ጽዋዕ ሥጦታ ቢልኩላቸው ንግሥቲቱ ለንጉሡ ስጦታ ሲመልሱ «ስለላክልኝ የአበባ ማስቀመጫ አመሰግናለሁ» የሚል ቃል ብቻ ላኩ።

የጥንት ሮማውያን ከረቦ ቆዳው የሚጠፈረው በተኩላ ቆዳ ነበር። ምክንያቱም ከአራዊት ሁሉ የተኩላ ድምፅ በኃይል ስለሚጮህ ከረቦውም ይጮሃል ብለው እያመኑ ነው።

በካሊፎርኒያ ውስጥ ሪቨርሳይድ በተባለች ቀበሌ ይኖሩ የነበሩት አቶ ክላርኔስ ኢ ቶርፔ የሚባሉት ሰው በካርቶን አሳሳላቸው የታወቁ ነበሩ። የሚስሉትም በአንድ ጊዜ ሁለት ካርቶኖችን ሲሆን አንዱን በእግራቸው እየሳሉ የአንዱን ደግሞ በእጃቸው ይስሉ ነበር።

በእንግሊዝ አገር ያለው የቦስተን ቤተ ክርስቲያን የፎቅ መውጫ 365 ደረጃ ነው። 52 መስኮቶች አሉት። ቤተ ክርስቲያኑ በ12 ምሰሶዎች ተደግፎ የቆመ ነው። እንዲህ ሆኖ የተሠራበት ምክንያት ደረጃዎቹ በቀን መስኮቶቹ በዓመት ውስጥ ባሉት ሳምንታት፤ ምሰሶውቹ በዓመት ውስጥ ባሉት ወሮች ተተምነው ነው።

በፖርቱጋል ውስጥ ሴራ ዳ እስትሬላ በተባለ ቦታ እግዚአብሔር የፈጠረው የሰው ቅርጽ ያለው ድንጋይ አለ።

በጀርመን አገር በሄድልበርግ ዩኒቨርስቲ አስተማሪ የነበሩት ፕሮፌሰር ግራደንቂዝ የማስታወስ ችሎታ አልነበራቸውም አንድ ቀጠሮ ሲኖራቸው ወይም የግብዣ ጥሪ ካለባቸው ለራሳቸው ደብዳቤ ይጽፉና አድራሻቸውንም ለራሳቸው አድርገው ፖስታ ቤት ይጨምሩና ደብዳቤው ከፖስታ ቤት ሲደርሳቸው ጉዳዩን ያስታውሱ ነበር። ፕሮፌሰር ግራደንዊዝ በ1860 ዓ.ም ተወልደው በ1935 ዓ.ም ሞቱ።

በአሳም ውስጥ ሳታም በተባለች ቀበሌ አንድ ሰው ሞቶ ከተቀበረ በኋላ በመቃብሩ ላይ ቅርጫት ሙዳይ ወይም ማሰሮ ይንጠለጠልበታል። አንዱ እንጥልጥል ነገር ሰውየው በሕይወት በነበረ ጊዜ የገደላቸው ከሆነ ሟቹ የገደለው አንድ ሰው ብቻ ነው ማለት ነው።


በኒውጊኒያ ውስጥ ሚንድምቢት በተባለች አምባ የሚኖሩ ጀግኖች ዘንግ ይይዛሉ። በሚይዙት ዘንግ ላይም ክሮች ይንጠለጠላሉ። የሚንጠለጠሉት ክሮች አንዱ ክር የሚናገረው ጀግናው ዘንጉን የያዘው ሰውየ በጦርነት የገደላቸውን ሰዎች ልክ ነው። አንድ ክር የሚደረገው አንድ ሰው ገድያለሁ ለማለት ነው።

በ1907 ዓ.ም በብራዚል በአንድ ጫካ ውስጥ አንድ ባቡር ለሥራ የሚያገለግል ነው ተብሎ ተጣለ። ከሰላሳ ዓመት በኋላ በባቡር ጭስ መውጫ አንድ ዛፍ በቅሎ ተገኘ።

በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ያማና የተባለው ጎሣ ሰዎች አንድ ሰው ሲሞት ኀዘናቸውን የሚገጽሉት ፊታቸውን በእጃቸው ጥፍር እየቧጠጡ ነው። የቧጥጠውም እንዲያው ዝም ብሎ ሳይሆን ቦታው ከዓይን ሥር ሆኖ እንባ የወረደበት እንዲመስል አድርገው ነው።

ስፔይን ውስጥ ሞንቴሄርሞስ በተባለው ቀበሌ የሚኖሩ ሴቶች ባል የለኝም የሚለው ምልክታቸው በጠጉራቸው ላይ መስተዋት ማድረግ ነው። በዚያ ሳቢያ መስተዋቱን አይቶ ባል የሌላት መሆንዋን ያውቀው ጀግና ሲያገባት መስተዋቱን ከቦታው ያነሳል።

በመሐከለኛው አውስትራሊያ አራንዳ የሚባል ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ጎረምሶች ከትልቅ ሰው ደረጃ መድረሳቸውንና ጉብዝናቸውን የሚያስመሰክሩ በጭራሮ የተያያዘ እሳት ሲነድ በላዩ ላይ ለጥቂት ደቂቃ በመተኛት ነው።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታችው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)

2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)
9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY